
# ኢማም ሁሴይን

## እና

# የአሹራ ቀን



# መግቢያ

وَلاَ تَحْسَبَنَّ الَّذِينَ قُتِلُواْ فِي سَبِيلِ اللّهِ أَمْوَاتًا بَلْ أَحْيَاء عِندَ رَبِّهِمْ يُرْزَقُونَ

*« እነዚያን በአላህ መንገድ የተገደሉትን ሙታን አድርገህ አትገምታቸው። በእርግጥ እነርሱ እጌታቸው ዘንድ ሕያዋን ናቸው፤»*(አሊ-ዒምራን :169)

(ኢማም ሁሰይን ቢን ዓሊን (ዐ.ስ) በኢስላማዊ ታሪክ ውስጥ የላቀ ቦታ እንዲኖራቸው የሚያደርጉ ባለ ብዙ ፈርጅ ገድሎች አሉዋቸው። ኢስላማዊ ፍትሕን ለማስፈን፣ጭቆናንና ጨቋኞችን፣የሰው በሰው ብዝበዛና አገዛዝን በመቃወም ያደረጉት ትግል የአዲስ ኢስላማዊ የትግል ምዕራፍ ከፋች ከመሆኑም በላይ የሳቸውን የኢስላማዊ አብዮትና እንቅስቃሴ መንገድ ለሙስሊም ህዝቦች በሙሉ የተበሰረበት በየትኛውም ጊዜና ቦታ በሚኖሩ ሙስሊሞች ልብና ህይወት ውስጥ የሚኖር የፍትህ ትግል አርአያ ነው። በተለይ በኢስላማዊ ትግል (ጅሃድ) መስክ ያበረከቱት አርአያ ፍፁማዊ ቆራትነትና የከፈሉት መስዋእትነት በ ዘላለማዊነት በሙስሊሞች ዘንድ የማይዘነጋና ከትውልድ ትውልድ እየተላለፈ ከዘመናት አድማስ ከአድማስ እየተሸጋገረ የሙስሊሞችን መለኮታዊ ተልእኮ አላማ፣የህይወት ትርጉም መብትና ግዴ የሚያወሳ ገድል ነው። በኢማም ሁሰይን (ዐ.ስ) የተለኮሱ የፍትህ ችቦዎች አሁንም ሙስሊሙ ኡማ ከገባበት የጃሒሊያ ጭለማ ይወጣ ዘንድ ብርሃን የሚፈነጥቁለት ናቸው።

ኢማም ሁስይን (ዐ.ሰ ) የያዚድ ቢን ሙዐዊያን የግፍ አገዛዝ ሲጋፈጡ የተነሳሱበት ብዙ ተጨባች ምክንያት አሉ፡እነዚህ ሐማኖታዊ፣ፖለቲካዊና ማህበራዊ ክስተቶች፣ የፍትህ ድምፃቸውን እንዲያስሙ አደረጋቸው:: ከሁሉም በላይ ግን የኢስላማዊ መርሆዎችና የሸርአ ሕግጋቶች ፤መጣስና መተላለፍ ዋናው ነበር:: አላህ (ሱ.ወ) የደነገጋቸውና ነቢዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የተገበሯቸውና ኢማም ሁስይን (ዐ.ሰ) በሙስሊሞች ህይወት ውስጥ ህያው ሆነውዲኖ ሩ የፈለጉ እነዚህ መሰረታዊ ኢስላማዊ እሴቶች በጥቂቱ::

1- ለሕዝብ አስተያየት ተገቢውን ትኩረት በመስጠትና በሙስሊሙ ዑማ ሁለንተናዊ ጉዳዮች ላይ ህዝቡን የማማከር ባህል (ሹራ) እንዲዳብር

« በነገሩም ሁሉ አማክራቸው ...وَشَاوِرْهُمْ فِي الأَمْرِ... »(ኣ.ሊ-ዒምራን 3:159)

2- የአላህ (ሱ.ወ) መመሪያዎችና ህግጋት ከምንም በላይ ሊከበሩ ይገባል:: የአንድ መሪ ስልጣንና ተግባር ህጋዊነት የሚገመገምበት መመዘኛዎችም ናቸው::

«በሰዎች መካከል በውነት ፍርድ፣ ...فَاحْكُم بَيْنَ النَّاسِ بِالْحَقِّ...»(ሷድ:26)

«በመካከላቸውም አላህ ባወረደው ሕግ ፍርድ ...فَاحْكُم بَيْنَهُم بِمَا أَنزَلَ اللّهُ...»(አል-ማኢዳህ 48)

3- በህዝቦች መሃከል ፍትህና ሪትዕ ሰብአዊ እኩልነት ማስፈን እያንዳንዱ ሰው በእኩል ደረጃ ለኢስላማዊ መብቶችና ግዴታዎች ተጠቃሚና ታዛዥ እንዲሆን ማስቻል::

إِنَّ اللّهَ يَأْمُرُكُمْ أَن تُؤدُّواْ الأَمَانَاتِ إِلَى أَهْلِهَا وَإِذَا حَكَمْتُم بَيْنَ النَّاسِ أَن تَحْكُمُواْ بِالْعَدْلِ إِنَّ اللّهَ

نِعِمَّا يَعِظُكُم بِهِ إِنَّ اللّهَ كَانَ سَمِيعًا بَصِيرًا

"አላህ አደራዎችን ወደ ባለቤቶቻቸው እንድታደርሱ ያዛችኋል:: በሰዎችም መካከል በፈረዳችሁ ጊዜ በትክክል እንድትፈርዱ (ያዛችኋል)፤ አላህ በርሱ የሚገሥጻችሁ ነገር ምን ያምር! አላህ ሰሚ ተመልካች ነው::" (አል-ኒሳእ:58)

4- አንድ መሪ በአላህና በመልእክተኛው የተጣለበትን ሐላፊነት በአግባቡ ለመወጣት በቂ ችሎታና ብቃት ሊኖረው ይገባል::

የአላህ መልክተ ኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:: «ሰዎችን በተገቢ ታምቻቸው እንድንሰይም አላህ አዞናል::»

5- የሀብትን ስርጭት በሚዛናዊነት ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ማዳረስ

مَّا أَفَاء اللَّهُ عَلَى رَسُولِهِ مِنْ أَهْلِ الْقُرَى فَلِلَّهِ وَلِلرَّسُولِ وَلِذِي الْقُرْبَى وَالْيَتَامَى وَالْمَسَاكِينِ وَابْنِ السَّبِيلِ كَيْ لَا يَكُونَ دُولَةً بَيْنَ الْأَغْنِيَاء مِنكُمْ وَمَا آتَاكُمُ الرَّسُولُ فَخُذُوهُ وَمَا نَهَاكُمْ عَنْهُ فَانتَهُوا وَاتَّقُوا اللَّهَ إِنَّ اللَّهَ شَدِيدُ الْعِقَابِ

« አላህ ከከተሞች ሰዎች (ሀብት) በመልክተ ኛው ላይ መለሰው (ሀብት) ከናንተ ውስጥ በሀብታሞቹ መካከል ተዘዋዋሪ እንዳይሆን ለአላህና ለመልእክተኛው ለዘመድና ባለቤትም አባትሰ ለሌላቸወ ልጆችም ለድሆችም ለመንገደኛም (የሚሰጥ) ነው:: መልክተ ኛው የሰጣችሁን (ማንኛውንም) ነገር ያዙት:: ከርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ:: አላህንም ፍሩ፣አላህ ቅጣት ብርቱ ነውና::» (አል-ሐሽር 7)

ኢማም ዒሊም እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል::

«የዓላም ሀብት ሁሉ የግል ንብረቴ በሆነ ኖሮ ለሚገባቸው በሚስኪኖችና ለድሆች መሃከል በእኩል ባከፋፈልኩ ነበር:: ግን ንብረትነቱ የአላህ ሲሆን ምን ማድረግ እችላለሁ?» ብለዋል::

6- አንድ ህዝብ መሪው (አሚር/ኢማም) የሚከተላቸው፣ፖሊሲዎች ላይ ሂስ መሰንዘር መምከር፣መወያየት፣አቅጣጫዎችን የመጠቆም መብት ሊኖረው ይገባል::

የአላህ መልእክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) በአጽንኦተ የሰተናገሩት

وَلْتَكُن مِّنكُمْ أُمَّةٌ يَدْعُونَ إِلَى الْخَيْرِ وَيَأْمُرُونَ بِالْمَعْرُوفِ وَيَنْهَوْنَ عَنِ الْمُنكَرِ وَأُوْلَئِكَ هُمُ الْمُفْلِحُونَ

ከናንተም ወደ በጎ ነገር የሚጠሩ በመልካም ሥራም የሚያዙ ከክፉ ነገርም የሚከለክሉ ሕዝቦች ይኑሩ:: እነዚያም እነሱ የሚድኑ ናቸው::(አሊ-ዒምራን 104)

« ከ ጂሃድ ሁሉ የላቀው በጨቋኝ መሪ ፊት ገሳጭ ቃል መናገር ነው::»

ኢማም ሁሰይን (ዐ.ስ) በወቅቱ የተከሰተውን ፖለቲካዊና ማህበራዊ ቀውስ ተገንዘቡ:: ምንጩን አጠኑ ሙስሊሙን እ'ማ ንወክላለን ብለው ስልጣን ላይ

የተቆናጠጡ መሪዎች ኢስላማዊ መመሪያዎችን እየተላለፉ ያሰ ኛቸውን የመሰላቸውን መስራት መጀመራቸውን ተረዱ:: ፍትህ ሲጓደል፣ሙስሊሞች ሲበደሉ፣ኡማው ከብዙ አቅጣጫዎች በሚሰነዘሩ ጥቃቶች ሲፈረካከስ እያዩ ዝምታን ለመምረጥ አላስቻላቸውም:: ከውድቀት ለመታደግና ኢስላማዊ እሴቶችን ለማንሰራራት፣የተዘነጉ ነብያ ዊ ፍላጎትን መልሰው ነፍስ ሊዘሩበት አሰቡ:: የተጣለባቸው ሐይማኖታዊ የመሪነት ሐላፊነታቸውን በአግባቡ ለመወጣት ቆርጠው ተነሱ:: በዙሪያቸው የተኮለከሉ ተከታዮቻቸውን ይዘው ወደ ትክክለኛው የኢስላማዊ ፍትህ ብርሃን ለመምራት አንድ ውሳኔ ላይ ደረሱ:: ስለዚህም በነበረው ጨቋኝ አገዛዝ ላይ ዐመፁ::

የርሳቸው አብዮታዊ ተጋድሎ በመለኮታዊ አስተምሮቶች የተሞላ ነው:: በአላህ (ሱ.ወ) መንገድ ላይ ውድ ህይወትን ጨምሮ የገዛ ሀብትን፣ ጊዜን፣ ዕውቀትን፣ ቤተሰብን፣ ክብርን ሁሉንም ለአላህ ውደታ አሳልፎ መስጠትን ያስተምራል:: ጭቆናን፣ ጭካኔን ፣ ሽብርተኝነትን፣ እንድንቃወምና እንድንዋጋ ይገፋፋል:: ኢማም ሁሰ ይን የመንገድ ርቀት ሳይበግራቸው፣ የበረሃውን አድማስ አቋርጠው፣ ቀን ከምሽት አደባልቀው በመጓዝ፣ ለአላህ (ሱ.ወ) ቃል የበላይነት ሲሉ ሁለመናቸውን አሳልፈው ሰጡ:: የተጎናፀፉት የሹሃዳነት ደረጃ በተለይ በዚያ ቀውጢ ፖለቲካዊ ቅጽበት በመምጣቱ ለተቀረው ትውልድ በጭለማ ባህር መሃል የቆመ መንገድ ጠቋሚ ብርሃን ዓይነት ነው:: እሳቸው የለኮሱት የሕይወት ብርሃን መንገድ ለጠፋቸው ሚሊዮች ዕጅ ለገሳቸው የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የልጅ ልጅ ፍትሕ ለማምጣትና ጭቆናን ለማስቆም በወሰዱት አስፈላጊ ዕርምጃ በሙስሊሞች ምድራዊ ታሪክ ውስጥ ዘላለማዊ የትግል መዘክር አኖ ሩ:: ለፈጣሪያቸው ለራሳቸውና ለተከታዮቻቸው ቃል ገቡ:: በመጨረሻም ከልጆቻቸው፣ ከቤተሰቦቻቸው፣ ከብዙ የነቢዮ ዘመዶችና ተከታዮቻቸው ጋር ሆነው ለሸሂድነት በቁ:: የከርበላ ምድር በተቆራረጡ የሹሃዳ አካል ተሞላች:: የንጹሃን ደም አሸዋውን አቀለመው:: የኢማም ሁሰይን ጭንቅላት ጨካኞች ተቀንጥሶ ወደ ዲማሽቅ ተወሰደ:: ሴቶቻቸው ተማርከው ለግዞት እን ደ ባሪያ በረሃውን አቋርጠው ተነዱ:: ኢማም ሁሴይን (ዐ.ሰ) ጂሃድ ሲያውጁ የሚከተለውን ሁሉ ገምተው ነበር:: ይሁን እንጂ ህልም ተፈርቶ . . . ሆነና የግድ ጭቆናን መዋጋት ነበረባቸው በሕይወት ሳሉ ነቢያዊ ሱንና ሲነድ ለማየትና፣ ዝምታ ለመምረጥ አልፈቀዱም:: በጊዜው ለነበሩ ሁኔታዎችና ክስተቶች አልበገሩዋቸውም ይልቅ ውኔያቸውን አደነደኑት እንጂ::

ይህ የሙስሊም ዑማ ዘንድ ተወዳጅ መሪ የነበሩት የመሩት ኢስላማዊ እንቅስቃሴ ብዙ መንፈሳዊ፣ ሞራላዊ ግብረገባዊ፣ ፖለቲካዊ ገጽታዎችን የተላበሰ ነው:: የ ርሳቸው ወርቃማ ገድል ዮሪክ ገጾችን የሞላ የባለ ብዙ አስተምሮት ምንጭ ነው :: በዚህች አጭር ጹሑፍ ውስጥ ይህንኑ ታሪክ ቀንጭበን ለአንባቢያን ለማቅረብ ሞክረናል::

ይህ ታላቅ ኢስላማዊ አብዮት እንቅስቃሴ በሁሉም ሙስሊሞች ዘ ንድ በውል ሊጠና፣ ሊዘገብና ሊዘከር ይገባል፡፡ በዓላማችን የተጨቆኑና የተናቁ፣ ክብራቸውን፣ ነጻነታቸውን፣ ሀገራቸውን ያጡ አያሌ ህዝቦች ወደ ነፃነት ለሚያደርጉት ትግል ሊያሻቸው ያለው ብቸኛ ጎዳና ታላቁ ኢማም ሁሴይን የተከተሉት ሆኖ እናገኛለን፡፡

በመጨረሻም አንባቢያን ከመጽሐፍ ጠቃሚ ዕውቀትና ሂዳያ እዲያገኙበት እንዲያደርግለን አላህን እንለምናለን፡፡

አላህ ሰሚና አዋቂ ነውና !

## ሁሴይን አብዮተኛው፡

ከርበላ . . . ከርበላ . . . የጎራዴዎች መንደር

ከርበላ . . . የማይሟጠጥ የደም ምድር

ከርበላ . . . በ ዘመናት አድማስ የማይከስም ቃል

ከርበላ . . . የስቃይ የሲቃ ልሳን !

ከርበላ አያልፍም ፤ በታሪክ አድማስ ላይ ጸሐዩም አይጠልቅም፡፡ በነጻነት ፈላጊዎች ሁሉ አዕምሮ የማይፋቅና በጨቋኞች ደባ የማይደበዝዝ ህያው ቃል ነው፡፡

በከርባላ ሰማይ ስር የተንጣለለው የደም ደመና ዘነበ፡፡ ሹሃዶችንና አብዮተኞችን ዘር አበቀለ፡፡ ፍርሃት ያልተፈጠረበት የኢማም ሁሰይን ድምጽ ዛሬም ከአል-ቱፋፍ ሸለቆ ተነስቶ በዘመናት ጆሮ ውስጥ ያቃጭላል፡፡ እንደ አውሎ ነፋስ አይሎ ጨቋኞችን ያሸብራል፡፡ የደም እሳተ ጎመራ ሆኖ ዙፋኖቻቸ ውን ያነቃንቃል፡፡ በሙዕሚኖች ልብ ውስጥ የጂሃድና የአብዮተኝነት መንፈስ ይጭራል፡፡ ድምፃቸው አሁንም ህያው ነው፡፡

«በአላህ እምላለሁ እን ደተዋረደ ሰውእጄን አልሰጥም፤ እንደ ባሪያም አልሸሽም!»

ሁሴይን (ዐ.ሠ) በርግጥ ማን ነበሩ? የዚህ ታላቅ ሰው ስብዕና ልዩ የሚያደርገው ምን ነበር? ባጭሩ ኢማም ሁሴይን (ዐ.ሰ) የታላቁ የአላህ መልዕክተ ኛ ነብዩ ሙሐመድ (ዐ.ሰ.ወ) ተወዳጅ ሴት ልጅ የፋጢማ ቱ ዛህራና የአጎት ልጅ አሊ ቢን አቢጧሊብ ቢን አብዱል ሙጠሊብ ቢን ሐሺም የአብራክ ክፋይ ናቸው፡፡

ሸሂድ ሁሴይን (ዐ.ሰ) በሸዕባን ወር 5ኛ ቀን 4ኛ ዐመተ ሂጅራ በመዲና አል-ሙነወራህ ተወለዱ፡፡ ሁሴይን ብለው ስም ያወጡላቸው ራሳቸው ነብዩ (ዐ.ሰ.ወ) ነበሩ፡፡

ሁሴይን በሃቢዩ (ዐ.ሰ.ወ)፣ በልጃቸው ፋጡማ (ረ.ዐ) ና በአሚሩል ሙዕምኒን ዓሊ (ዐ.ሰ) እንክብካቤ ስር አ ደጉ፡፡ ከነቢዩ (ዐ.ሰ.ወ) ነብያዊ ፈለግን፣ ኢስላማዊ መመሪያዎችንና የአላህ ደጋጎችን የአኗኗር ዘይቤን ኢስላማዊ ፍትሓዊነትንእውነተ ኛ ነትን በጥልቀት ቀስመዋል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ዐ.ሰ.ወ) ሁሴይንን በጅጉ አብልጠው ይወዱአቸው ነበር፡፡ ከዚህም የተነሳ ብዙውን ጊዜ ተሸክመዋቸው ይዙሩ የነበሩ እንደነበር ሲራቸው (ታሪካቸው) ተዘግቧል፡፡ በሰሐቦቻቸው ዘንድምእንዲህ ብለው ይናገ ሩ እንደነበር ተዘግቧል፡፡

«አላህ ሆይ !እወዳቸዋ ለሁና እ ነርሱን የሚወዱትን ሁሉ ውደዳቸው»
ይሉ ነበር

ለነርሱ (ሀሴንና ሁሴይን) የነበራቸውን ጥልቅ ፍቅር ሲገልጹም:

«እነዚህ ሁለት ልጆች በዚህች ዓለም ውስጥ ሁለቱ ጥንድ ጽጌረዳ አበቦች ናቸው»

እንዲሁም «ሀሰንና ሁሴይንን የሚወድ ይወደኛል፤ እነርሱን የሚጠላ እኔንም የሚጠላኝ ብቻ ነው።» ብለዋል።

የአላህ መልዕክተኛ (ዐ.ሰ.ወ) ሶላታቸው ይስግዱ የነበረው ሀሰንና ሁሴይን በየተራ በቅዱስ ጀርባቸው ላይ እየተቆናጠጡ እንደ ነበርና ቤተሰቦቻቸው ልያወርዱአቸው ሲጥሩ ከሶላት በኋላ እንዲህ ይሉዋቸው እንደነበር ተዘግቧል።

«አትንኩአቸው ! የሚወደኝ ሁለእነርሱን መውደድ አለበ ት»[አቡ ሀይታም የዘገቡት ሐዲስ]

«ሌላ ሀዲሳቸው ነብዩ (ዐ.ሰ.ወ) እንዲህም ብለው ነበር :-
«ከጅነት የሆነን ሰው ማየት የሚሻ ወደ ሁሴይን ይመልከት።»

በዚህ መልኩ ነበር የኢማም ሁሰይን (ዐ.ሰ) የሻሂድነት አዝማምያ ለኡማው የተበሰረው። ለሁሴይን (ዐ.ሰ.ወ) የተሰጣቸውን ክብርና ደረጃ ለሙስሊሞች ያስተዋወቁት ነቢዮ (ዐ.ሰ.ወ) ኡማው በሁሴይን ላይ በደል እንዳይፈጸም አስበው ነበር።

አጥብቀው ይወዱዳቸው የነበሩት ነቢዮም (ዐ.ሰ.ወ) በአላህ ትዕዛዝ ለዘለአለም ከምድር ተሰናበቱ አመታት አለፉ። ከአላህ መንገድ ያፈነገጡ ሰዎች ነቢዮን ስለ ሁሴይን የተናገሩት ቃል ከመጤፍ ባለመቁጠር ደፍረው የኢማም ሁሰይን (ዐ.ሰ) ደም ጭካኔ በተሞላበት አኳኋን አፈሰሱ።

ኢብን ዑመር (ረ.) በአንድ አጋጣሚ የሁኔታውን ከባድ ነት ሲገልጹ እንዲህ ብለው ነበር፡-

«የኢራቅ ሰዎች በሃጅ ዝንብ ስለመግደል ያወራሉ፤ የነቢዮን (ዐ.ሰ.ወ) ተወዳጅ ልጅ የፋጡማ ቱ ዛህራን ልጅ ሁሴይንን እየገደሉ፤ የአላህ መልዕክተኛ (ዐ.ሰ.ወ) በዚህች ዓለም ያሉኝ ሁለት ጥንድ ጣፋጭ አበቦቼ ያሉትን ዘንግተው።»

በዚህ ወሳኝ ታሪካዊ ክስተት ውስጥ ሁለት ተቃራኒ ገጽታ ያላቸውን ድርጊቶች እናስተውላለን። የመጀመሪያው ከአነስ ቢን ማሊክ የተወራውና የአላህ መልዕክተኛ (ዐ.ሰ.ወ) የሁሴይንን አፍ ላይ ስመውት ያሞካሹበትን የመረቁበትን ወቅት ሲሆን፤ ሌላው

የታሪክ ዘግናኝ ገጽታ የኩፋው ገዥ ኢብን ዚያድ የሁሴ ይን የተቆረጠ ጭንቅላት በእንጨት ላይ ሰክቶ ሲወስድ ነው፡፤ ኢብን ዑመር ድርጊቱን እንዲህ ገልጸውታል፡፡

> «ኢማም ሁሴይን ሻሂድ ከሆኑ በኋላ ጭንቅላታቸው ተቆጦ ወደ ኢብን ዚያድ ቤተመንግስት ተወሰደ፡፡ ኢብን ዚያድ የሁሴይንን ጥርሶች በብትሩ እየነካቸው «ቆንጆ ነበር. . .» እያለ ሲያሾፍ መታገስ ስላልቻልኩ ጣልቃ ገብቼ «አንተ ብትር የሚታሳርፍበት ንጹሕ አፍ ነብዩ (ዐ.ሰ.ወ) ይሰሙት ነበር» አልኩት»(በአል-ደሃቅ እንደዘገበው)

አቡበከር አል-ሲደቅም(ረ) እንዲህ ብለው መስክረዋል፡፡

> «የአላህ መልዕክተኛ ሀሰንና ሁሴይን የጀነት ወጣቶች አለቆች ናቸው ብለው ነብዩ ሲናገሩ ሰምቻለሁ፡፡»

ሁሰይን የነብዩን (ዐ.ሰ.ወ) ልብ የማረኩት ገና በጠዋቱ ነበር፡፡ ከሁሉም በላይ ሁሴይን የተገኙትና ያደጉት በአላህ ብርሃን በተሞላና ኢስላማዊ ህይወት፣ ፍቅር በተሞላበት የነቢዮ ቤተሰብ (አህሉል በይት) ውስጥ ነበር፡፡ ከነቢዮና ከሰሃቦቻቸው የኢስላምን አንኳር ጥፍጥና ቀስመዋል፡፡ ተልዕኮውን በአግባቡ ተረድተዋል፡፡ ይህ ሁናቴ የኢስላማዊ ፍትሕ፣ ዒማን፣ ዒባዳ፣ በአጠቃላይ የኢስላም ተምሳሌት ያደርጋቸዋል፡፡ ከእስላማዊ ማዕድ የተመገቡት ኢማም ሁሴይን ኢስላምንና ሙስሊሞችን ከውድቀት ለመታደግ ባደረጉት ወሳኝ ተጋድሎ የጨቋኞችን ብትር ሳይፈሩ የኢስላምን ህግጋት የጣሱትን ሁሉ በግልጽ በመቃወምና በመፋለም ውድ ሕይወታቸውን በአላህ መንገድ ለመክፈል በቅተዋል፡፡

ይህ በአምባገነን ገዢዎችና ስርዓቶች አካኳያ የተከተሉት ቆራጥ አቋማቸውና የከፈሉት መስዋዕት በሁሉም ትውልዶች ዘንድ በተለይ ለኢስላማዊ ፍትሕ ነፃነት ተፋላሚዎች ልብ ውስጥ ቋሚ መዘክር ያደርጋቸዋል፡፤ በኢስላማዊ ታሪክ ውስጥ የሚካሄዱ ትግሎች ሁሉ አንቀሳቃሽ ኃይል ናቸው፡፡ የአላህ ሕግ ሲጣስ፣ የነብዩ ሱንና ሲደፈር መታገስ ለማይችሉት ህይወታቸውን ጃሂሊያን አፍርሰው ኢስላማዊ ፍትሕ ለመገንባት ለሚታገሉት ፋና ወጊ ሆነው ይኖራሉ፡፡ ሙስሊሞች ሁሉ ለነቢዩ ቤተሰብ ባላቸው ሱናዊ ፍቅርና አክብሮት የተነሳ እንደ ኢማማቸው (መሪያቸው) ተቀብለውታል፡፡

የሁሴይን መታጣት በሙስሊሞች ዘንድ ውድቀትን አስከትሏል፡፡ ኡማው ያጣው ፍትሕን ጭምር ነበርና፡፡ ለዚህም ነው ታሪካቸው ከሳቸው ሞት በኋላ ከስሞ ያልቀረው፡፡ ባለፉት ዘመናትና ትውልዶች ፍትሓዊ ትግሎችንና አብዮቶችን ጨምሯል፡፡ ሙስሊሞች ጨቋኝ መሪዎችንና ስርአቶችን እንዲታገሉ በር ከፍቷል፡፤ የነፃነትና የሰብዓዊነት መድረክ ፈጥራል፡፡ በሳቸው የደም ጠብታ የተቀጣጠለው ኢስላማዊ አብዮት ብዙ ህዝቦች የጃሂሊያን ቀንበሮች ኢንዲጥል ስበብ ሆኗል፡፡ አዕላፍ ጂሃዳዊ እንቅስቃሴዎች እንዲከሰቱ

*አስችሏል፡፡ የተለያዩ የትግል ተቋማትም ለፈጠሩ በቅተዋል፡፡ የሁሴይን ዘለአለማዊ ድምጽ ሙስሊሞች ሁሉ አንደበት ሆኖ አገልግሏል፡፡*

*በከርበላ አሻዋ ላይ የፈሰሰው ንጹሕ የሁሰይን ደም የነቢዩ ደምና አካል መሆኑን ሙስሊሞች ሁሉ የሚያውቁት ነው፡፡ በርሳቸውና ባጠቃላይ በነቢዩ* (ዐ.ሰ.ወ) *ቤተሰብ ላይ የተፈጸመው ዘግናኝ ወንጀል የአላህን ጠላቶች ቅሉላቅ ቅጣት ሚጋብዝ ነው፡፡ በነቢዩ* (ዐ.ሰ.ወ) *መንገድ የሚመሩ ሙስሊሞች ይሄንን በሁሴይን* (ዐ.ሰ) *የተጀመረ ዘላለማዊ ኢስላማዊ ትግል በምድር ላይ ማምጣት የግድ ይሆናል የትግል[illegible]ነት ኛ ገጽታ ሙስሊሞች ሁሉ በውን ሊያጠኑት ይገባል፡፡ የፈሰሰው የሁሴይን ደም በከንቱ አልነበረምና በወቅቱ የኡማያድን ዙፋን ያሽመደመደና በቀጣይ ምድራዊ ታሪክ ውስጥ የኢስላማዊ ትግልን መንፈስ የጫረ ነው፡፡*

*ኢማም ሁሴይን* (ዐ.ሰ) *ሸሂድ ከሆኑበት ማግስት አንስቶ ብዙ ሙስሊሞች የደረሰን ግፍ በኢስላማዊ መንገድ ለመበቀልና ጨቋኞችን ሁሉ ለመቅጣት አያሌ እንቅስቃሴዎችን ፈጥረዋል፡፡ እነዚህም ወንጀለኞችን ለይቶ ወደ ኢስላማዊ ፍትህ ለማምጣት የተዋቀሩ ነበሩ፡፡ ከነዚህ በወቅቱ ከተካሄዱ እንቅስቃሴዎችና የትጥቅ ትግሎች ውስጥ የተዋቢን* (Permitents) *ና ወንጀለኞቹን በተወሰነ መልኩ የቀጡት የአል-ሙክታር እንቅስቃሴዎች ይጠቀሳሉ፡፡ የእዚህ ጥረቶች ነፀብራቅ አሁንም በስፋት ይታያል፡፡ ለብዙ መሰል ኢስላማዊእንቅስቃሴዎችና አብዮቶች የመሠረት ድንጋይ የሆነውም ይህው በኢማም ሁሴይን* (ዐ.ሰ) *የተጀመረው ኢስላማዊ ትግል ሆኖ እናገኛለን፡፡*

*ለሁሴይን* (ዐ.ሰ) *የፈሰሰው የሀዘኝእንባ አሁንም አልደረቀም፡፡ ስሜቱም አልቀዘቀዘም፡፡ በሙስሊሞች በአጠቃላይ የሰው ልጆች ላይ በጨቋኝ ገዢዎችና ስርዓቶች የሚካደው ግፍ እስካለ ድረስ ትግሉ ይቀጥላል፡፡ ከርበላ ሁሌም የፀረ-ጭቆና ጃሂሊያ ችቦ የሚቀጣጠልበት አምባ ናት፡፡ በአላህ መንገድ ለሚታገሉት ሁሉ መንደርደሪያ ተምሳሌት ናት፡፡ ሁሴይንም በልቦቻቸው የፍትሕና የትግል አርአያ ሆነው ይኖራሉ፡፡*

*ሁሴይን የተጨቋኞች የደካሞች* (*ሙስተዳዐፊን*) *ጠበቃ፣ በኢስላማዊ የትግል መድረክ ለተላለፉት የፊት መብራት ናቸው፡፡ አላህ* (ሱ.ወ) *እንድንወዳቸውና እንድናከብራቸው ግዴታ ካደረጉብን የነቢዩ* (ዐ.ሰ.ወ) *የቅርብ ዘመዶችም የመጀመሪያው ናቸው፡፡*

«... قُل لَّا أَسْأَلُكُمْ عَلَيْهِ أَجْرًا إِلَّا الْمَوَدَّةَ فِي الْقُرْبَى وَمَن يَقْتَرِفْ حَسَنَةً نَّزِدْ لَهُ فِيهَا حُسْنًا إِنَّ اللَّهَ غَفُورٌ شَكُورٌ»

*«በርሱ (መልዕክቴን በማድረሴ) በዝምድና ውዴታን እንጅ ዋጋን አልጠይቃችሁችሁም በላቸው፤ መልካሚቱንም ሥራ የሚሠራ ሰው ለርሱ በርሷ መልካሙን ነገር እንጨምርበታለን፤»* (አል-ሹራ 23)

ሁሰይንን አላህ (ሱ.ወ) ራሱ ንፁሕ ካደረጋቸው የነቢዩ (ዐ.ሰ.ወ) ቤተሰቦች አንዱ ናቸው::

...إِنَّمَا يُرِيدُ اللَّهُ لِيُذْهِبَ عَنكُمُ الرِّجْسَ أَهْلَ الْبَيْتِ وَيُطَهِّرَكُمْ تَطْهِير

*«የነቢዩ ቤተሰቦች ሆይ ! አላህ የሚሻው ከናንተ ላይ ርክስትን ሊያስወገድና ማጥራትንም ሊያጠራችሁ ብቻ ነው»* (አል-አሕዛብ 33)

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ከናጅራን ክርስቲያኖች ጋር በዳዕዋ ክርክር ባደረጉበት ወቅት አላህ (ሱ.ወ) የትኛው ወገን ትክክለኛ እንደሆነ በዱአቸው (ጸሎታቸው) እንዲረጋግጡ በዘዘበት ጊዜ ከነቢዮ ወገን ከቆጠራቸው ደጋግ በሮቹም አንዱ ኢማም ሁሴይን (ዐ.ሰ) ነበሩ::

فَمَنْ حَآجَّكَ فِيهِ مِن بَعْدِ مَا جَاءكَ مِنَ الْعِلْمِ فَقُلْ تَعَالَوْاْ نَدْعُ أَبْنَاءنَا وَأَبْنَاءكُمْ وَنِسَاءنَا

وَنِسَاءكُمْ وَأَنفُسَنَا وأَنفُسَكُمْ ثُمَّ نَبْتَهِلْ فَنَجْعَل لَّعْنَةُ اللّهِ عَلَى الْكَاذِبِينَ

*«ዕውቀቱም ከመጣልህ በኋላ በርሱ (በዒሳ) የተከራከሩህን ሰዎች ኑ፤ ልጆቻችንና ልጆቻችሁንም፤ ሴቶቻችንና ሴቶቻችሁንም፤ ነፍሶችንና ነፍሶቻችሁንም እንጥራ፤ ከዚያም አጥብቀን አላህን እንለምን፤ የአላህንም ቁጣ በውሸታሞቹ ላይ እናደርግ በላቸው»* (አሊ-ዒምራን 61)

## ከትግሉ ገጽታዎች (ትዕይንቶች)፡

ሦስተኛው ኻሊፍ ዑስማን ቢን አፋን (ረ.ዐ) ከተገደሉ በኋላ ሙስሊሞች ዓሊ ኢብን አቢጣሊብ የኡማው ቀጣይ ኸሊፋ (ኢማም) እንዲ ኑ ድጋፋቸውን ሰጡ፡፡ ሙባያዕ ገቡላቸው፡፡ ዓሊ (ዐ.ሰ) የኡማውን መንግስቱዊና አስተዳደራዊ ጉዳዮች እንዲ መሩ ተመረጡ፡፡ ሙአዊያ ቢን አቢ ሱፍያን ግን ድጋፍ ነፈጋቸው፡፡ የዓሊ ኻሊፋዊ ሥልጣንም እንደማ ይመለከተው አወጀ፡፡ ወዲውም በፊት በዑስማን ሥር አሚር በነበረበት ሶሪያ ሀገር ራሱን የግዛቷ ኻሊፋ አድርጎ ሾመ፡፡

ዓሊ በጊዜው በተከሰተው ፖለቲካዊ ቀውስ የተነሳ ራሳቸው አስተዳደራቸው ሳይጠናከር ከሦስት አቅጣጫ ተቃውሞ ገጠማቸው፡፡

1. በሙአዊያ-ቢን አቢሱፍያን የሚመራው የኡማያድ ቡድን
2. የዓሊን ጦር የካዱ ኸዋርጆች ቡድንና
3. የአይሻ ፣ የጣልሃና የዙበይር ቢን አል-አዋም ቅንጅት

ከተከታታይ ፖለቲካዊ ግጭቶች በኋላ ኢማም ዓሊ (ዐ.ሰ) በመጨረሻ የዐይሻ ጠልሃና ዙበይርን ቡድን በስራ ከተማ አጠገብ በተካሄደውና የግመል ጦርነት (The camel) በሚጠራው ግጭት (ዘመቻ) ድል አድርገአቸው የነርሱ ዐመጽ በዚህ አከተመ፡፡ ሙአዊያ በበኩሉ በሲፊን ጦርነት ተሸንፎ በድርድር ሌላ ተንኮል የሚጠነስስበት አጋጣሚ ተፈጠረለት፡፡ ዓሊ ይህንን ተንኮል የሞላበትን ድርድር አልተቀበሉትም፡፡ ይሁን እንጂ የበለጠ ደም መፍሰስ ለማስቀረት ዝምን መረጡ፡፡ ሙአዊያ ዳባውን ቀጠለበት፡፡ ደጋፊዎችን ማደራጀት ተያያዘ፡፡ ብዙ ሰዎችንም ከጎኑ ለማሳለፍ ቻለ፡፡

ኸዋራጆች በበኩላቸው የኢማም ዓሊን ጦር እየካዱ መውጣት ጀመሩ፡፡ ይሁን እንጂ በኋላ አል-ነህረዋን በሚባል ቦታ ከኢማም ዓ ሊ ኃይል ጋር ባደረጉት ግጭት ተሸንፈው ድል ተመተው ጦራቸው ተበታተነ፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያሉ ኸዋሪጆች በሙስሊሞች ሁሉ ላይ ያላቸውን ጥላቻ በማውጣት ታላላቅ ወንጀሎችን ለመስራት አቀዱ እናም አሚሩል ሙዕሚኒን ኢማም ዓሊን (ዐ.ሰ) ሙአዊንና አምር ቢን አሰን ለመግደል ወሰኑ፡፡ በዚህ ኢ-ሰብዓዊ ተግባራቸው ኢማም ዓሊ ቢን አቢጣሊብ የተንኮላቸው ሰለባ ሆኑ፡፡ በኢማም ዓሊ ሞት ሙስሊሙ ኡማ የኢስላም አርማ፣ የፍትሕ ፋኖ፣ የዕውቀት ማህደርና የጂሃድ ኤክስፐርት የሆኑት ይህንን ታላቅ ሰው አጣ፡፡

ይህ ጭካኔ የተሞላበት ግድያ የተፈጸመው አብዱልራህማን ቢን ሙልጃም በተባለ ሰው ነበር፡፡ ዓሊ (ዐ.ሰ) የተገደሉትን ቢን ሙልጃም በሰነዘረባቸው መርዛማ ጎራዴ ጭንቅላታቸውን ተወግተው ነበር፡፡ በ19ኛው የረመዳን ሌሊት ፈጅር ሶላት ለማሰገድ

ላይ እያሉ በተቃጣባቸው ጥቃት ጭንቅላቸው ላይ ተወግተው ከሁለት ቀን በኋላ በ21ኛው ዕለተ ረመዳን 40ኛ ዓመተ-ሂጅራ ለሻህድነት በቁ::

አሚሩል ሙዕሚኒን በተለይ ይወቁባቸው የነበ ሩት ልዩ ባሕርያት:- ከፍተኛ የአመራር ብቃት በጂሃድ ወቅት የማያሳዩት ፍፁም የሆነ ጀግንነትና የሰው ልጆች፣ የአላህ ፍትሕ ተቋዳሽ መሆን አለባቸው በሚለው ጽኑ አቋማቸው ነው:: ለነዚህ መሠረታዊ ጽንሰ ሃሳቦች ነው ሲታገሉ ህይወታቸውን ያሳለፉት:: ዓሊ (ዐሰ) እንደ ሌሎች ቀዳሚ ኻሊኖች ዓነት የተረጋጋ ዘመን ለማየትታደሉ ም:: ኡማውን የመሩባቸውን ዓመታት ያሳለፉት ከተለያዩ አፈንጋጭ ቡድኖች ጋር ሲታገሉ ነው:: ኢስላማዊ መርሆዎችና ነቢያዊ ፈለጎች ሲጣሱ ሲተላለፉ ዩታገሱበት ወቅት የለም:: አይታወቅም:: የእሳቸውን ህልፈት ተከትሎ በሙስሊሙ ኡማ ላይ አዲስና ውስብስብ ዘመን መጣ:: የሶሺዩ-ፖለቲካዊ ሚዛን በመዛባቱ የተወሳሰቡ ችግሮች መከሰት ጀመሩ የኻላፋቱል-ራሺዱን (ቀጥተኞቹ ኻሊፎች) ዘመን በማብቃቱም ኡማውን በትክክለኛው ኢስላማዊ ጎዳና ለመምራት ብቃት ያለው መሪ ሊገኝ አልተቻለም:፤ በምትኩ ድክመቶች ሁሉ እየተራቀቁ ሄደው ኡማው ፍትሕ አልባ ወደ ሆነ ስርዓት ተሸጋገረ:: የሙዓዊያ ተጽዕኖ እያለ መጣ::

የአላህ መልዕክተኛ (ዐ.ሰ.ወ) ስለ ሐሰንና ሁሴይን የተናገሩት ቃል፣እነርሱም በኡማሙ ዘንድ የነበራቸው ታላቅ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እንዲሁም በኢስላማዊ እውቀት ዘርፍ ያላቸውን የላቀ ፁ እንዲሁም የአባታቸው ኢማም ዓሊ (ዐ.ሰ) ወሲያ (ኑዛዜ) ተንተርሰው ሙስሊሞች ኢማም ሀሰንን ለኡማው ኢማምነት አጩ:፤ በሌላው ወገን ከኢማም አሊ (ዐ.ሰ) ሽሂድነት ማግስት ጀምሮ ሙአዊያ ራሱን የኡማው ኸሊፋ አድርጎ ሾመ:: በሙስሊሞች ቀጥተኛ ድጋፍ የኡማው ኢማም ሆኑት ሀሰንን (ዐ.ሰ) ኃላፊነታቸውን እንዲለቁ አለበለዚያ እንደሚዋጋቸው መዘጋጀቱን በደብዳቤ አሳወቃቸው:: ሙአዊያ ለኢማም ሀሰን (ዐ.ሰ) የላከው ደብዳቤ እንዲህ ይነበባል::

> «በአላህ ስም እጅግ በጣም አዛኝ እጅግ ሩህሩህ በሆነው:-
> አላህ በሮቹን ራሱ በፈለገበት ታሁኔይንከባከባል:: ውሳኔውንም የሚቃወም የለም:: አላህ በቅጣቱ ፈጣን ነው:: ሞትህ በእጃችን እንዳይሆን ከፈለግህ ኃይላችንን ተቀበል:: ከተቀበልከንና በይአ (ቃልኪዳን) ከገባህልን የምትፈልገውንና የምትጠይቀውን ልናሟላልህ ቃል እንጋለን:: ቃሌ ዐዕሻ በኒቀይብ ቢን ጠላባህ እን ዳላቸው ነው:፤ «አንድ ሰው የአማና (የአደራ) ዕቃ ቢያስቀምጥብህ በአግባቡ መልስለት፤ በኋላ ታማኝ እንድትባል፤ አዛዥህ ባለ ሙሉ ኃይል ሲሆን አትቅናበት፤ ደሃ ከሆነ አትካደው» ከኔ የበለጠ ለኸሊፋው ቦታ ስለሚይገባህ ቀጥለህ ተተኪዩ ትሆናለህ::»
> ወሰላም

ኢማም ሐሰን ቢን ዓሊ (ዐሰ) የሚከተለውን ምላሽ ፃፉለት፡፡
« ያሰኘህን የተናገርክበት ደብዳቤ ደርሶኛል አንተ በፃፍክልኝ ሁኔታ መልስ እንዳልሰጥህ በአላህ እጠበቃለሁ ፡፡ እምመክርህ ወደ ቀጥተኛው መንገድ እንድትመለስ ነው ትክክለኛነቴን በርግጥ ያኔ ትረዳለህ፡፡ » ወሰላም

ኢማም ሀሰን ለሙአዊያ ሊንበረከኩለት አልፈለጉም፡፡ ኸሊፋቸው ሕጋዊ በመሆኑና ከሙስሊሙ ኡማ /ድጋፍ/ በማግኘታቸው በያዙት አቋማቸው ፀኑ የሙአዊያን ኃይል በጂሃድ ገጠሙ፡፡ ይሁን እንጂ ብዙ የኢማም ሀሰን ጦር አዛዦች ከድተዋችው ወደ ሙአዊያ በመቀላቀላቸውና ሙአዊያ በሀገሩ ተሰሚነት ያላቸውን ሰዎች ከድል ማግስት በስልጣንና በሹመት ሊያንበሸብሻቸው በፕሮፓጋንዳው ስላሳመናቸው ጦረነቱን ሊያሸንፍ በቃ፡፡ ኢማም ሀሰን (ዐ.ሰ) ሌላ አማራጭ አጡ፡፡ የሙስሊሞች ደም በከንቱእንዳይፈስና አንድነታቸው ይበልጡኑ እንዳይነጋ እንዲሁም ጠንካሮቹ ጎረቤት ጠላቶቻቸው ሮማውያን ደጋጣሚውን ተጠቅመው እንዲያወሩዋቸው በማሰብ ከመአዊያ ጋር የሰላምና የዕርቅ ስምምነት ተፈራረሙ፡፡

የተፈጠሩት ወቅታዊ ውጥረቶች እስኪረግቡና በሙአዊያ የማይቀር ውድቀት በሁዋላ ያለውን የኡማውን ሰላማዊ ህይወት ለመንደፍና ተስማሚ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ለማቻቸት ሲሉ ለጊዜው ዮላፊነታቸውን ስልጣን ለመተው ተገደዱ፡፡ በሁለቱ ወገኖች መሀከል የተደረሰው ስምምነት እንዲህ የሚል ነበር፡፡

የተፈጠሩት ወቅታዊ ውጥረቶች እስኪረግቡና በሙአዊያ የማይቀር ውድቀት በኋላ ያለውን የኡማውን ሰላማዊ ሕይወት ለመንደፍና ተስማሚ ፖለቲካዊና ማሕበራዊ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ሲሉ ለጊዜው የኺላፋነታቸውን ስልጣን ለመተው ተገደዱ፡፡ ለሁለቱ ወገኖች መሃከል የተደረሰው ስምምነት እንዲህ የሚል ነበር፡፡

1. ይህ በኢማም ሀሰን ቢን ዓሊ አቢ-ጧሊብና በሙአዊያ ቢን አቢ ሱፍያን መሀከል የተደረሰ ስምምነት ነው፡፡ በዚህ ውል ሀሰን የኸሊፋነት ቦታቸውን ለሙአዊያ ለቀዋል፡፡ ይህ የሚሆነው ግን ሙአዊያ የሙስሊሙን ኡማ በአላህ ቁርአንና በነቢያዊ ሱንና እንዲሁም *በኸሊፋቱል ራሺዱን* መንገድ ላይ የሚያስተዳድር ከሆነ ብቻ ነው ሙአዊያ በስልጣኑ ፍጻሜ ላይ ሌላ ሰው ለኸሊፋነት ሊጠቁም አይችልም፡፡
2. ኢማም ሀሰን ከሙአዊያ ቀጥለው ኸሊፋ ይሆናሉ፡፡ ይሁን እንጂ በሳቸው ላይ አንድ ችግር ቢከሰት ወንድማቸው ሁሰይን ኡማውን የመምራት ቦታ ይይዛሉ፡፡
3. ሙአዊያ በኢማም አሊ አስተዳደር ዘመን የተለየ አቋም በነበራቸው የመዲና የሂጃዝና የዒራቅ ህዝቦች ላይ ምንም ዓይነት የበቀል እርምጃ አይወሰድም

4. በግዛቶቹ የሚሾሙ አሚሮች አሚሩል ሙዕሚኒን ዕሊን መሳደብ፣ ማውገዝ፣ ማንቋሸሽና በኩጥባና በቁኑት ሶላቶች ወቅት መራገም የተከለከሉ ይሆናሉ፡፡

5. ሰዎች ሁሉ ባሉበት (በሚኖሩበት) ሀገር ደህንነታቸው የተጠበቀ ነው፡፡

6. ሙአዊያ ኩፋ ያለውን ቤይተል-ማል የማስተዳደር ስልጣን አይኖረውም የማስተዳደሩ ስልጣን የኢማም ሃሰን ይሆናል፡፡

7. ሙአዊያ ሀሳን፣ ሁሰይንና ተከታዮቻቸውን ሴቶቻቸውን ለአደጋ አያጋልጥም፡፡ ንብረታቸውንም አይወርስም፡፡

እነዚህ ውሎች ተጽፈው ሁለቱም ወገኖች ተስማምተውበት አጸደቁት፡፡ ይሁን እንጂ መዲዊያ ወዲያው የሚከተለውን ለተከታዮቹ በስብሰባ ላይ በይፋ ተናገረ፡፡

«. . . በርግጥ ለሀሰን የተወሰኑ ነገሮችን ለማድረግ ቃል ገብቻለሁ፡፡ ፈጽሚያሁም አሁንም ሁሉም ነገርእግሮቼ ስር ገብቷል፡፡ ካሁኑ ሰዓት ጀምሮ ስምምነቶቹን የማከብርበት አስገዳጅ ሁኔታ አይታየኝም፡፡»

በዚህ የክህደትና የቅጥፈት መንገዶች ስልጣኑን ያጠናከረው ሙአዊያ በሙስሊሞች ታሪክ ውስጥ ታላቅ ጠባሳ አኖረ፡፡ ኢማም ሀሰን (ዐ.ሰ) ታግደው የኺልፋነት ቦታቸውን እንዲለቁ የተደረጉበትን ሁኔታ ተከትሎ የቀጥተኞች ከሊፋ (ኪሊፋተል-ራሺዱን) ዘመን አከተመ፡፡ ኢማም ሀሰን (ዐ.ሰ) ከአቸው መገደል በኋ ላ ተከትሎ የተከስተውን ፖለቲንዊና ማህበራዊ ቀውስ ለማርገብና የህዝቦቻቸውእለታዊ ህይወት እንቅስቃሴ ለመከታተል ለስድስት ወራት ያህል ወደ መዲና ተመለሱ፡፡ ይህ ሁሉ ግን የግጭቶች መቋጫ ሊያመጣ አልቻለም፡፡ በነቢዩ ቤተሰብና በቅርብ ተከታዮቻቸው ላ ይ የሚቃጣው የማሳደድ ዘመቻ ቀጠለበት፡፤ *ሀሰነይን* (ሁለቱ ሀሰንና ሁሰይን) ምንም እን ኳን ራሳቸውን ከፖለቲካዊው ዓለም በተጨባጭ ቢያገሉም ሙአዊያ በነርሱና በቤተሰቦቻቸው ላይ የሚያካሄደውን ጫና አባባሰ፡፡ ውጥረቱእያየለ መጥቶ ሀሰን (ዐ.ሰ) ሲሞ ቱ ሙስሊሞች ሙአዊያ አመራሩን ለሁሴይን እንዲለቅ በመፈለጋቸው ፍጥጫው ሌላ የተወሳሰበ ገጽታ ይዞ ቀርበ፡፡ ሙስሊሞች ለሁሴይን ያላቸውን ድጋፍ እያፈጠኑት ሄዱ፡፡

በተመሳሳይ ጊዜ ደግሞ በሙአዊያ አዕምሮ ሌላ የተለየ ሀሳብ ተፈጠረ፡፡ ሙአዊያ ከኢማም ሃሰን የነጠቀውን የኸሊፋነት ስልጣን ለራሱ ልጅ ያዚድ በውርስ ለማስተላለፍ ውሳኔ ላይ ደረሰ፡፡ ሙስሊሞች ይህንኑ ዓላማውን እንዲ ቀበሉትና ለያዚድ *ሙባያአ* እንዲገቡለት መርጣ ጀመረ፡፡ የሙአዊያ ድርጊት ለደነል ኢስላም በዕድ ነገር በመሆኑና በኸሊፍ አሰያየም ላይ ኢስላማዊ መስፈርቶችን የሚፃረር በመሆኑ በተለያዩ *ሰሐቦችና* ታዋቂ *አሊሞች* ዘንድ ከፍተኛ ተቃውሞን ቀሰቀሰ፡፡ የሙአዊያን ውሳኔ ከተቃወሙት ታዋቂ ሰሐቦች ጥቂቶች ሁሴይን ቢን ዓሊ(ዐሰ)፣ አብዱራህማን ቢን አቡበከር፣ አብዱላህ

ቢን ዙበይር፣ አብዱላህ ቢን ዑመርና ሌሎችምታዋቂ ሰ ሐቦት (ከይር ስራቸውን አላህ ይውደድላቸውና) ይገኙበታል፡፡

በወቅቱ የነበረውን የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች የታሪክ ሰዎች ዘግበውታል፡፡ እንዲህ ይነበባል፡-
በ50ኛው ዓመተ ሂጅራ ቁሂፅን ሙስሊሞች እ ጅ ወደቀች፡፡ ሙአዊያ ለያዚድ ያስተላለፈውን ኸሊፋነት ስልጣኝን ዲያጸድቁለት ለአዲሱ መሪዎች በይአ እንዲገቡ ትዕዛዝ አስተላለፈ፡፡ ሕዝቡም ሳይወድ በግድ ተቀበለው መሪው በሕይወት ሳለ ስልጣኑን በቀጥታ ለልጁ ሲያወርስ በኢስላም ታሪክ ይህ የመጀመሪያው ነበር፡፡ ይህ ባህል ተግባራዊ የሆነው በሙአዊ የአገዛዝ ዘመን በመሆኑ በኢስላማዊ ታሪክ ስልጣንን በዘር ሀረግ እየቆጠሩ ማውረስና መውረስ እንደ ባህል እየተቆጠረ መጣ ሙአዊያ በዚህ ሂደቱ የመዲና ገዥ ለነበረው ለመርዋን ቢን አልሀኪም ደብዳቤ ላከ፡፡ ዓላማው የልጁን ሹመት ለህዝቡ እንዲሰብክለት ነበር፡፡ አል-ሀከምም የታዘዘውን ለመፈጸም መዲናውያንን ሰብስቦ እንዲህ ሲል ተነገረ፡ - አሩል ሙእሚኒን ልጁን (የዚድን) በናንተ ላይ የመሾም ሀሳብ አለው፡፡ ይህም የአቡ በክርና የዑመር ሱንና ነው፡፡» ሲል ታወ የነበ ሩት አብዱልራህማን ቢን አቡበክር አል-ሲደቅ ተነስተው፡-

«በፍጹም ! ይሄ የኮስሮና የቂሳር ባህል ነው፡፡ አቡ በክርም ሆኑ ዑማር ልጆቻቸውንም ሆነ ዘመዶቻቸውእነርሱን እንዲ ተኩአቸው ለሥልጣን አጭተው አያውቁም፡፡» ሲሉ የተቃውሞ ድምጽ አሰሙ፡፡

«ሙአዊያ በዚህ ሁኔታ 51ኛው ዓመተ ሂጅራ ሀጅ ላይ ለልጁ የዚድ በቂ ድጋፍ ሊያሳባስብ ቻለ፡፡ ቀጥሎም ለኢብን ዑመርእንዲህ የሚል መልዕክት ላከ «ያ ኢብን ዑመር ! በፊት ለአንዲት ሌሊት ቢሆን እን ኳ ያለ አሚር ማደር አልሻም ስትል አልነበረምን? አሁን በሙስሊሞች መሀከል ምንም ዓይነት ሹክቻ እንዳትፈጥር በጥብቅ አስጠነቅቀሃለሁ፡፡»

«ኢብን ዑመር አላህን ካመሰገኑ በኋላ እንዲህ የሚል ምላሽ ሰጡ፡- «ካንተ በፊት ያስተዳደሩ ኸሊፎች ነበሩ፡፡ ልጆችም ነበሩዋቸው፡፡ ያንተ ልጅ ከነርሱ በምንም አይበልጥም፡፡ አንተ ለልጅህ የዋልከውእነርሱ አላደርጉትም! ሁሌም ለሙስሊሞች የተሻለውን ነበር የመረጡላቸው በሙስሊሞች መሀከል ልዩነት እንዲፈጠር አልፈልግም፡፡ ግን ከሙስሊሞች አንዱ ነኝ፡፡ እነርሱ የተስማሙትን ሁሉ እቀበላለሁ»

«ቀጥሎ ሙአዊያ ኢብን አቡበከርን አስጠርቶ እንዲህ አላቸው «የልጄን ጉዳይ ለአላህ ብቻ ትተዋለህ? አለ ሙአዊያ፡፡ ኢብን አቡበከርም አቋረጡትና» አላህን ፍራ ! ይህንን አናደርግም፡፡ ሁኔታው ለሙስሊሞች ሁሉ በሹራ ማቅረብ አለብህ፡፡» ብለውት ሲነሱ

ሙአዊያ «ያ አላህ በዚህ ሰው ላይ ድል ሰጠኝ አለና ኢብን አቡበከር -«ለሶሪያውያን ምንም እንዳትናገር እዚሁ ይጨ ርሱሃልና ቀድሜእኔ ካንተ ድጋፍ እንዳገ ኘሁ እነግራቸዋለሁ፡፡ ከዚያ በኋላ የፈለገውን መስራት ትችላለህ፡፡» አላቸው፡፡

«በመጨረሻም ለኢብን ዙበይር ላከባቸው-» ያ ኢብን ዙቤር!
አንተ እንደ ተንኮለኛ ቀበሮ ነህ፤ በአንድ ቀዳዳ ገብተህ በሌላ ትወጣለህ፡፡ እነዚህ ሁለት ሰዎች (ኢብን ዑመርና ኢብን አቡበከርን ማለቱ ነው) ሃሳባቸውን እንዲቀይሩና እንዲቃወሙኝ ያስደረግህ አንተነህ!» አላቸው፡፡ ኢብን ዙበይርም በተራቸው፡» ባስተዳዳሪነትህ ካልረካህ ስልጣኑን ልቀቅ እ ኛ ባንተም ሆነ በልጅህ ላይ እምነት የለንም፡፡ የትኛችሁንም መታዘዝ እንችላለን?» አሉትና ጥለውት ወጡ፡፡

«በቀጣዩ ቀን በጅሙዓ ኹጥባ ላይ ሙአዊያ እንዲህ ሲል ለህዝቡ ተናገረ ሰዎች የሚያወሩት ሁሉ ሀሰት ነው፡፡ ኢብን ዑመር ፣ ኢብን አቡበክርም ሆኑ ኢብን አል ዙበይር ለያዚድ ያላቸውን ድጋፍ *በበይአቸው* አረጋግጠዋል፡፡» ከሙአዊያ ጋር የነበሩ፡፡ ሶሪያውያን ደግሞ እነዚህ ሰዎች ድጋፋቸውን ህዝብ ፊት ሳ ይገልጹ አንለቃቸውም፡፡ እምቢታን ቢመርጡ እንሰይፋቸዋለን፡፡» ሲሉ ደነፉ፡፡ ብልጣብልጥነቱን ተጠቅሞ ሙአዊያ. . .» *ሱብሃናአላህ* ቁረይሶችን እንዴት ለክፋት ታስባላችሁ ከናንተ ይህንን መስማት አልሻም አላቸውና ከምንበሩ ወረዳ፡፡

«የመዲና ሰዎች እርስ በርስ ማንሾካሾክ ጀመሩ፡፡ ሦስቱ መሪዎቻቸው ኢብን ዑመር፣ ኢብን አቢበክርና ኢብን ዙበይር ለያዚድ *በይአ* ገቡ» የሚል ጥርጣሬ በነዋሪዎቹ ዘንድ ሰፈነ፡፤ እነርሱ በበኩላቸው «አልደገፍነውም» የሚለውን አቋማቸውን አስተጋቡ መዲናውያንን አምታትቶ የፈለገውን ያገኘው ሙአዊያ በሚቀጥለው ቀን ወደ ሶሪያ ለመመለስ መዲናን ለቀቀ፡፡»

## የሁሰይን ጽናት

ኢስላማዊ ሸርአ መሰራቃዊ የዲነስ ኢስላም መርሆዎችእንዲከበ ሩ አበክሮ ያዛል፡፡ በተለይ የሙስሊሞች ግብረገባዊ (ሞራላዊ) እሴቶች በኢስላማዊ መስፈርቶች ላይ መመስረት እ ንዳለባቸውና ሙስሊሞች ሁሉ በነዚኢስላም ዊ እሴቶች ተመርተው ግላዊና ማህበራዊ ስብዕናቸው ቁርዓናዊ አስተምሮቶችን የተላበሰ እንዲሆን ሸርአው ያስገነዝባል፡፡ ከነዚህ እስላማዊ ዕሴቶች አንዱ በተቃዋሚ ቡድኖች መሐከል የሚደረጉትን ስምምነቶች የተመለከተ ነው፡፡ የዲነስ ኢስላም አቋም ሙስሊሞች በሚደርሱባቸው ስምምነቶችና ውሎችን ማክበር እንዳለባቸው የሚገልጽ ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ሲል ደንግጓል

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُواْ أَوْفُواْ بِالْعُقُودِ

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ በቃል ኪዳኖች ሙሉ» (አል ማኢዳ -1)

وَأَوْفُواْ بِالْعَهْدِ إِنَّ الْعَهْدَ كَانَ مَسْؤُولاً

እንዲሁም « በኪዳናችሁም ሙሉ ፤ ኪዳን የሚጠየቁበት ነውና» (አል-ኢስራእ-34)

የነቢዩ (ዐ.ሰ.ወ) ቤተሰብ (አህሉል በይት) የሆኑ ኢማሞች ሁሉ በአኗኗኖቻቸው ሁሉ የዚህ ኢስላማዊ መርህ ተገዥ ነበሩ፡፡ ቃል ኪዳኖቻቸውን አክባሪዎች ንፁህ ኢስላማዊ አኽላቅ (ባህሪዎች) የሚተገብሩ ነበሩ፡፡ ከብዙሃኑ የሙስሊሙ ኡማም ሆነ ከተቀናቃኞቻቸው ጋር የነበራቸው ግንኙነት ሁሉ ኢስላማዊ ዘይቤን የተከተለ ነበር፡፡ ለዚህም ነበር ኢማም ሁሴይን (ዐ.ሰ) ከኢማም ሀሰን (ዐ.ሰ) መገደል በኋላ የዒራቅ ሙስሊሞች ያቀረቡላቸውንና ሙአዊያንእንግልብጥ የሚ ለውን ጥሪ ያልተቀበሉት የነቢዮን ቤተሰብ እ(ሁሉ ል ዘይት) አጥብቀው ይደግፍ የነበሩት የዒራቅ ሺአዎች በኡማያድ ገዥዎች ስር ሲማቅቁ በመኖራቸው ይህ ግፍ እንዲያከትም በመማፀን ኢማም ሁሴይን በሙአዊያ ላይ እንዲያምፁ ገፋፏቸ ው፡፡ ኢማሙ ግን ሃሳባቸውን አልተቀበሉዋቸውም፡፡ ምክንያቱም በኢማም ሀሰንና በሙአዊያ መሀከል ተደርሶ የነበረው የሰላም ስምምነት የማክበር ኢስላማዊ ግጼ ነበረባቸው፡፡ ቃ ል ኪዳናቸውን ሊጥሱ አልቻሉም፡፡ ለአላህና ለኡማው ታማኝ መሆን ነበረባቸው፡፡ በወቅቱ የነበረውን ሁኔ ሸክ ሙፊድ እንዲህ ይገልፁታል፡፡

> «በአል-ኸልቢ፣አል-መዳኢኒና በሌሎችም የታሪክ ምሁራን እንደዘቡት አል-ሀሰን (ዐ.ሰ) በተገደሉት ወቅት የዒራቅ ሺአዎች አንድእቅድ ነደ ፉ ሙአዊያን ከስልጣን አስወግደው የኢማምነቱን ፁ ኢማም ሁሴ ይን እንዲረከቡ የሚል፡፤ ለዚህም ለኢማም ሁሴይን ያላቸውን ጠንካራ ድጋፍ

በደብዳቤ ገልፀውላቸው ነበር፡፡ ኢማሙ ግን የነርሱን ፍላጎት እንደማይቀበሉ ምላሽ ሰጡ፡፡ ምክንያቱ በመጀመሪያ በሀሰንና በሙአዊያ መሀከል የተደረሰው ስምምነትእስከ ፍፃሜው እስኪደርስ የመጠበቅና የማክበር ግዴታ ነበረባቸው፡፡ ሙአዊያ ሲሞትና ያዚድ ህገወጥ ስልጣኑን ማንቀሳቀስ ሲጀምር ግን ጉዳዩን ዳግም እንደሚያጤኑት ገለፁላቻ፡፡»

## የሁሰይን ሚና

ሙአዊያ ስልጣን፣ገንዘብና ሽብርእ የተጠቀመ በህዝብ ላይ የተቀዳጀውን ጉልበት አጠናክሮ ኋላም ስልጣኑን ለልጁ የዚድ አውርሶ ሞተ። በዚህ ሁሉ መሀከል ግን የሙአዊያ ወገን ያጣ ነገር ነበር። ኡማያድ ፓርቲ መረጋጋትን አላገኘም። የሙስሊሞችን ልብ ሊማርኩ አልቻሉም። ውስጣዊታአማኒነትና ሊያገ ኙ አልበቁም። አዲስ ስልጣን ከአባቱ የወረሰው የዚያድም ሙስሊሞች ለነብዩ ቤተሰብ ያላቸውን ስር የሰደዱ ፍቅርና ከበሬታ ሊፍቅ አዳገተው። ለአህሉል በይት የነበራቸው ውጀታ ጥቅልና በመንፈሳዊና ፖለቲካዊ እሴቶቻቸው ሳይቀር ይንፀ ባረቅ ነበር። ኡማው ኢማም ሁሴይንን እንደመሪያቸው የመቀበል ኢስላማዊ፣ ነቢያዊና ታሪካዊ ሁኔታዎች አረጋግጠውላቸዋል። ለዚህም ዝግጁ ነበሩ። ከሁሉም ነገር በላይ ግን፤ ሙስሊሞች ትኩረት የሰጡት በኢስላም ቢድአ (ባኢድ) የሆነውን ስልጣንን በዘር የማስተላለፍ ባህል (ለዚያውም ገዥዎቹ አምባገነን በሆኑበት ሁኔታ) በርትተው በመቃወም ላይ ነበር ። ከአባት ወደ ልጅ የተጋባውን የጭቆና ስርዓትም መታገል ነበረባቸው።

የኡማድ አገዛዝ በተቆጣጠራቸው ዋና ዋና የሀብትና ሐይል ምንጮች፣ስልጣን፣ወታደራዊ ኃይል እየተጠቀመ ራሱን በህዝቡ ላይ አሰፈረ። ኡማው በሙአዊያ የስልጣን ዘመን የቀመሰውን ግፍ በልጁ ስር በረታበት። የተንሰራፋው ፈሳድ (ሙስና) የህዝቦቹን ህይወት በመከራና ስቃይ ይላ አጠላበት። በመሆኑም ያዚድን ለማስወገድና ኢስላማዊ ፍትህ ኢስላማዊ ስርዓት መልሶ ለማምጣት በየቦታው ድምፁን ማሰማቱን ገፋበት። ሽብርተኝነት ሲያይል የጨቋኞች ኮቴ ሲገዝፍ ህዝብ በተቃዋሚ ቡድኖች ላይ ዐይኑን መጣል ድጋፍን መግለጽ ጀመረ። በኢስላማዊ የአብዮተኝነት ስሜት ታንፀው ኢስላማዊ እንቅስቃሴዎችን ሊፈጥሩ ሊመሩ የሚችሉ የቁርጥ ቀን ልጆች አስፈለጉ። ኡማው ከገባበት ፖለቲካዊ ማጥ ለማውጣት መሪ ጠማው። በጊዜው ኡማውን ወደ ኢስላማዊ የትግል የፍትህ ጎዳና ሊመራ የሚችሉና ብቁ በህዝቡ ዘንድም ተአማኒነት የነበራቸው ሁሴይን ቢን ዐሊ ቢን አቢጣሊብ ነበሩ። ሁሴይን ዲነል ኢስላምን ከምንጩ የተጎነጩ፣በኢስላማዊ አኽላቅ የበለፀጉና እጩቀት በአመራር በተአማኒነት፣በእውቀት የመጠቁና ሙአዊያ ለያዚድ ስልጣን ሲያወርስ ለግንባር ቀደምትነት ከተቃወሙ ጥቂት ሰዎች ውስጥ አንዱ ናቸው። በሌላ መልኩ ሙአዊያ ገና በጠዋቱ ሁሴይንን ይፈራቸው ነበር ሁሴይን ባላቸው ታሪካዊ መብትና በአመራር ብቃታቸው ተነሳስተው ኡማውን በፍትሐዊ አመጽ ሊያንቀሳቅሱበት እንደሚችሉ ያምናል። ያዚድም በሁሴይንና በኡማው መሀከል ያለውን የቅርብ ቁርኝት ያውቀ ነበር፤። ሁሴይን አመቋ ብርቱ፣ጠንካራና አብዮተኛ እንደሆኑ ይገነዘባል። ለአባታቸው ስልጣን ሲቃወም እንደነበርና እውቅና እንዳልሰጡት ስለሚገባው ትኩረቱና ፍርሃቱም በኢማም

ሁሴይን ላይ አሳረፈ፡፡ ለዚህም ያዚድ ዙፋኑን በተቆናጠጠበት ጥቂት ቀናት ውስጥ ለመዲና ገዥ ለነበረው አል-ወሊድ ቢን ዑትባህ ቢን አቢ ሱፍያን እንዲህ ሲል ደብዳቤ ላከለት፡-

«ሁሴይንን፣አብደላህ አቢን ዑመርንና፣ኢብን አል-ዙበይርን በአፋጣኝ *በአይአ* (ቃል ኪዳን) እንዲገቡልኝ አድርግ፡፡ ጊዜ ልትሰጣቸውና ልትዘነጋ አይገባህም ...»

አል ወሊድ የሙአዊያን ሞት ከሰማ በኂላ ቦታውን በተካው በያዚድ እንደታዘዘው የመዲና ያሉትን ሶስቱን አንጋፋ ሙስሊም መሪዎች ለያዚድ *በይአ* (ቃል ኪዳን) ለማስገባት ደፋ ቀና ማለት ጀመረ፡፡ የሚወሰደው ቀጣይ እርምጃ ስለጠፋው መርዋን የሚባል ሰው አማከረ፡፡ የመርዋን ምክር ተንኮል የተሞላበት ነበር፡፡ መርዋንእንዲህ ሲል ነበር የመከረው፡፡ «የድጋፍ ድምፃቸውንእንዲሰጡ አሁኑኑ ጥራቸው፡፡ ከተቀበሉህ ባሉበት ሁኔታ ትተዋቸዋለህ፡፡ እምቢታን ከመረጡ የሙአዊያዊን መሞት ሳያውቁ በፊት በዚያው ጨርሳቸው፡፡ ሁሴይውን አስቀድመው ካ ወቁት ሁሉም በያሉበት ህዝቡን ሊቀሰቅሱት ይችላሉ፡፡ በርግጥ ኢብን ዑመር ጦርነት ያውጃል የሚልእምነት የለኝም፡፡ እርሱ በሰላማዊ መንገድ ካልሆነ በቀር ወደ ስልጣን ለመውጣት የሚፈልግ ሰው አይደለም፡፡»

ምክክሩ አበቃ ውሳኔ ተላለፈ፡፡ ሁሴይንም ተነጥሎ በጥበቃቸው ስር ንዲገቡ ተስማሙበት፡፡ ሉማው የሙአዊያን ሞትእንደሰማ ፊቱን ወደ ሁሴ ይን እንደሚያዞርና ለርሳቸውም ያለውን ድጋፍ እንደሚገልጽ የታወቀ ነበር፡፡

«አል-ወሊድ አብደላህ ቢን ዑመር ቢን ዑስማንን ወደ ሁሴይንና አልዘብይር ላከ መጥተው እንዲያነጋግ ሩት ነበር የፈለገው፡፡ ወቅቱ አል-ወሊድ በአደባባይ ለህዝቡ የማይታይበት ነበር፡፡ መልዕክተኛው ጥሪውን እንዳደረሳቸውም ሁሴይንና ኢብን ዙበይር ምክክር ያዙ፡፡ የተፈጠረውን ሁኔታ ለመገመት አላዳገታቸውም፡፡ አል-ወሊድ ከሰዎች በተገለለበት ሁኔታ እኛን የሚጠራበት ምን ምክንያት አለው ሲሉ አሰቡ፡፡

«ሁሳይን፡- . . . አምባገነኑ መርያቸው ያረፈ ይመስለኛል የፈለገንም ወሬው ሳይሰራጭ ድጋፋችንን ፈልጎ ይሆናል»

ኢቢን ዙበይር «. . . እኔም እንደሱ አስባለሁ፡፡ አሁን ምን ለማድረግ አስበዋል?
ሁሰይን. . . ተከታዮቼን ይዤ እገናኛቸዋለሁ፤ ራሴንም መከላከል በሚችልበት አኳኋን ሆኜ አናግረዋለሁ፡፡
ኢቢን ዙይበር፡ «ጥቃት ቢደርስብዎት?»
ሁሰይን ራሴን ከጥቃት ለመከላከል ቢሆን እንጂ አልገናኘውም፡፡»

በዚህ ሁኔታ ሁሴ ይንና ተከታዮቻቸው የተሰረባቸውን ዴባ ለማክሸፍ ታጥቀው ተነሱ:: የተጠቀሱት የሁሴይን ቃላቶች የያዚድን ህገወጥ ስልጣን ለመታገል ያላቸውን ጽኑ አቋም ይገልፃሉ:: የያዚድን ጨቋኝ ሥርዓት ለማስወገድ ደግሞ ኢስላማዊ ጂሃድ የግድ ሆነ::

ሁሴይን ወዲያው ለቅርብ ወንድሞቻቸው፣ ዘመዶቻቸውና ተከታዮ ቻቸው ላኩባቸው በዙሪያቸው ስላላ የሚሆኑ ቆራጥ ጀግኖችን አሰባሰቡ እነርሱንም አስከትለው በቀጥታ ወደ አል-ወሊድ አመሩ:: ወደ ቤቱም በቀረቡ ጊዜ ተከታዮቻቸውን ከው ጪ ትተው ወደ ቤቱ ገቡ: ከአል-ወሊድ ጋር ተገናኙ:: አል-ወሊድ የሙአዊያን ሞት ነገሯቸው አስከትሎም ሁሴይን ያዚድ ድጋፍ እንዲሰጡ ጠየቃቸ ው:: ምላሻቸው ግን እንዲህ የሚል ነበር::

«ያ አል-ወለድ! የድጋፍ *በይአ* በድብቅ አይሰጥም:: ነገ ህዝቡ በተሰበሰበበት ከነርሱ ጋር እኔንም ጥራኝ እዚያ እንገናኝ» አሉት

«ቀጥለውም ለአል-ወልድ እንዲህ አሉት

«እኛ ነቢዮ ቤተሰቦች ነን፤ እኛ መልዕክቱ ማዕከል ነን:: አላህ ታላቁን የነቢያቶች መደምደሚያ የሆኑት ነቢይም ያወጣው ከዚህ ቤተሰብ ነው:: ያዘድ ግን ጨቋኝ ገዥ ነው:: አላህ ሃራም ያደረገወን ኸምር (አስካሪ መጠጥ) ይጠጣል፤ አላህ የከለከለውን የብዙ ንፁሃን ሰዎች ህይወት አጥፍቷል:: ለርሱ ድጋፍ ልሰጥ አልችልም:: አንተ ግን ለያዝከው ስልጣን *በይአ* (ቃል ኪዳን) ሊትገባለት ትችላለህ::»

ሁሴይን ይሄን እንደተናገ ሩ ወጥተው ሄዱ:: ከአል-ወልድ ጋር የመጨረሻው ግኑኝነታቸውን በዚህ ተደመደመ:: ቀጥሎም ከያዚድ ጋር ለሚያደርጉት ጂሃድ ዝግጅታቸውን አፋጠኑ:: መካን ለጂሃዳቸው መንደርደሪያነት ለሚመሩት ኃይል የሚያደራጁበት ቦታ አድርገው መረጡ::

## አመፁ ለምን አስፈለገ?

ሁሴይን መዲናን ለምን ለቀው እንደሚሰደዱ ለሙስሊሞች ግልጽ አድርገው ነበር። በአዲሱ ኡማያድ መሪ ያዚድ ላይ ጂሃድ አውጀዋል። አገዛዙን ለመጋፈጥ ያነሳሳቸውን ምክንያቶች ለሕዝባቸው ግልጽ አድርገዋል። እርምጃዎቻቸውንም አስረድተዋል። በወቅቱ የተከሰቱት ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ ርዕዮቱዊ ቀውሶች ከፈጠሩት ውድቀት ሙስሊሙን ኡማ ለመታደግ ባለባቸው ኃላፊነት የተነሳ ለመታገል ወሰኑ። በዚህ በኢስላማዊ ታሪክ ፈታኝ ወቅት በያዚድ ላይ የሚደረገውን ተቃውሞ ለመምራት መዲናን ለቀው ተሰደዱ። በጊዜው የወሰዱትንእርምጃ ለወንድማቸው ሙሐመድ ቢን አል - ሀናፊያህ በላኩት ደብዳቤ በግልጽ አስቀምጠዋል።

> «ጂሃድ (የትጥቅ ትግል) ለማወጅ የወሰንኩት ለፈንጠዚያ አይደለም። ያለኝን ወደራዊ ኃይል ለማሳየትም አይደለም ። ሽብርና ትርምስ ለመፍጠርም አይደለም። ብቸኛው ምክንያቴ የነቢዮን (ሰዐወ) ኡማ ከአንዣበበበት አምባገነን አገዛዝ ለመታደግ እሳቤ ነው። ነ ቢዮና አባቴ የሄዱበትን በጎውን የማዘዝ መጥፎውን የመከልከልና የማስወገድ ኃላፊነት ስላለብኝ ብቻ ነው።»

ለያዚድ *በይዓ* ያልገቡበትን ምክንያትም ተጠይቀው ሲመልሱ እንዲህ ብለው ነበር።

> «ያዚድ ብልሹ ሰው ነው። ኢስላማዊ ህግጋትን ጥሷል። ኸምር ይጠጣል፡ አላህ በጥብቅ የከለከለውን የንጹሃን መስሊሞችን ህይወት አጥፍቷል። የሚፈጽማቸውን ክፉ አድራጎቶች ሁሉ በግልጽ በአደባባይ የሚያከናውናቸው ሆኗል። ለዚህ ዓይነት ሰው *በይአ* መግባት አይጠበቅብኝም»

ዲነል ኢስላም አንድ ሙስሊም መሪ ራሱን ለቁርአንና ሸርአዊ ሕግጋትና ነቢያዊ ሱናዎች ማስገዛት እንዳለበት ያዛል። በሥ ሩ ለሚያስተዳድራቸው ህዝቦችም ፍትህና እኩልነትን ማምጣት መለኮታዊ ግዴታ አለበት። ስልጣኑን መኳ አድርጎ ህዝቡን ጨፍልቆ በመግዛት ንብረታቸውን ዘርፎ ለራሱ መጠቀሚያ ማድረግ በኢስላም የተወገዘ ተግባር ነው።

ያዚድ በሁሴይንና በኡማው ዘንድ ተቀባነት ያጣው የአመራር ብቃትም ጭምር ስላልነበረው ነው። ራሱን ለክፋትና ለአካላዊ ደስታዎች አሳልፎ የሰጠ ሰው ነበር። ያዚድ የሚታወቀው በኸምር ጠጭነቱ፣ በሴሰኝነቱ፣ ጊዜውን በአደንና በፈረስ ጉግስ በማሰለፍ ሲሆን እንደ አንድ ኢስላማዊ መሪ ለኡማው ተምሳሌት ሊሆን አልቻለምቻዲያ ኢማም ሁሴይን ኢስላምን በጥልቀት ላልተገነዘበና ነቢያዊ አክላቅ ለሚባለው አንድ ጃህል እንዴት በኸሊፋነት ይቀበሉታል?

ሁሴይን (ዐ.ሰ) የዚድን በማንኛውም ረገድ ለመቃወም የላቸውን አቋም በተለያዩ ሙስሊም ግዛቶችና ከተሞች ላሉ ሙስሊሞችና መሪዎቻቸው በደብዳቤ ማሳወቅ ጀምሮ:: የኢማምነትን ምንነትና መስፈርት ጠቅሰው ለኩፋው ሙስሊሞች የላኩት ደብዳቤ እንዲህ የሚል ይገኝበታል::

በአላህ እምላለሁ! ኢማምነት ማለት በአላህ ቁርአን የሚዳኝና፣ ለፍትሕ የሚታገል፣ የዲነል ኢስላምን መመሪያዎችና ትዕዛዛት የሚፈጽም ህይወቱን ለአላህ እኩል መስዋዕት ከማድረግ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል:: ብለዋል::

በተጨማሪም የበስራ ሀገር ታዋቂ ሙስሊም ግለሰቦችና ለነበሩት ለነበሩት ለነ ማሊክ ቡን ወስማ አል በክራ፣ አል አህናፍ ቢን ቀይስ፣ አል-ሙንዝር ቢን አልጃሩድ፣ ሙሰዑድ ቢን አምሩ፣ ቀይስ ቢን አል ሀይተምና አምሩቢን ዑበይድ ቢን ሙአምር ተመሳሳይ መልዕክት ልከዋል:: ሁሴይን (ዐ.ሰ) መልዕክተኛቸውን ሱላይማን (አባራዚን) አስይዘው ለባስራውያን የላኩት ደብዳቤ በከፊል እንዲህ ሚል ነበር::

«በአላህ (ሱ.ወ) ቃልና በነቢዮ (ሰ.ዐ.ወ) ሱንና እንድትገዙ እማፀናችኋለሁ በአሁኑ ወቅት የነቢዮ (ዐ.ሰ.ወ) ሱንና ወደ ጎን ተገፍቶ ጃህልና እየተንሠራራ ነው:: መልዕክቴን ተቀብላችሁ የምትከተሉኝ ከሆነ በአላህ መንገድ ልመራችሁ ዝግጁ ነኝ:: ወሰላም::»

ሁሴይን በአስተዳደራዊ፣ ከሊፋዊ፣ ፖለቲካዊና በአጠቃላይ በኡማው ጉዳዮች ላይ ይከተሉ የነበሩት ፖሊሲዎች ቁርአንን መሠረት ያደረጉ ነበር:: በአንጻሩ ያዚድ የያዘው አቋም ፍፁም አምባገነናዊ ይዘት የነበረው ነው:: በሁሴይን (ዐ.ሰ) አመለካከት የአንድ ሙስሊም መሪ ተግባር ህዝቦቹን በአላህ መንገድ ላይ መምራትና የቁርአን ህጎችንና ነቢያዊ ሱናን በሕይወታቸው ውስጥ ለማምጣት ማስቻል ነው:: ሕይወታቸውን በሸርዓ ቀርጸው የአላህን መለኮታዊ ተልእኮ እንዲወጡ ማድረግ:: መሪው ለሚያስተዳድራቸው ህዝቦች ሁሉ በአላህ ፊት ግንባር ቀደም ተጠያቂ ነውና::

በአጠቃላይ ኢማም ሁሴይን (ዐ.ሰ) ካደረጓቸው ኹጥባዎና፣ ንግግሮች ከፃፏቸው ደብዳቤዎችና በጊዜው ከነበረው ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና፣ ኢኮኖሚያዊ፣እውነታዎች አኳያ ሲገመገም ዘመኑ የሚከተሉት ባህሪያት ነበሩት::

1. ጭቆና፣ ምዝበራና በሥልጣን መባለግ በኡመያዶች ዘንድ ሥር እየሰደደ ሄዷል:: ኡመያዶች ራሳቸውን በተናጠል በፖለቲካ ፓርቲ አደራጅተዋል:: የአንድን ጎሳ ብቻ መሠረት ያደረገ ፖለቲካዊ ቡድን ፈጥረዋል፡፤ ስልጣን ሀብትና የአስተዳዳሪነቱን ቦ ለራሳቸው አድርገዋል:: ብዙሃኑ የሙስሊም ህብረተሰብ ግን ከነዚህ ሀቄዎች የተገለለ

ሆኗል:: ኡማው የኡመያድ ቤተሰብ የግል ንብረትእስከመሆን ደርሶ ነበር ማለት ይቻላል::

2. ግድያ፣ ሽብርተኝነት፣ ዝርፊያ፣ ደም መፋሰስ ተንሰራፍቷል

3. የዑማው ሀብት በየአጋጣሚው ይዘረፋል:: አግባብ የሌላቸው ግብሮች በህዝቡ ላይ ይጫናሉ:: ብዙሃኑ ሙስሊም ህዝብ በድህነትና ኋላቀርነት ሲሰቃይ ባንፃሩ ጨቋኝ ካፒታልስታዊ መደቦች መሠረት እየያዙ ነበር፡፤ አብዛኞቹ አስተዳዳሪዎች ኃላፊነታቸውን የሚወጡ ዓይነት አልነበረም ሙስና ተንሰራፍቷል::

4. ሰዎች በግልም ሆነ በቡድን ከኢስላማዊ መንገድ የማፈንገጥ ባህርይ ጀምረዋል::

5. የሸርአ ህግጋትን መጣስእየተለመደ መጥቷል:: በዚህ ወሳኝ ወቅት ላይ ኢስላማዊ ደንቦችእየተጣ ሱ፣ ነቢያዊ ሱንና እየተላለፉ፣ ከአላህ ቃ ል ከነቢዩ አስተምሮቶች ይልቅ የገዢዎች ቃል የተሻለ ተሰሚነት እያገኙ መጥተዋል::

6. የተወሰኑ ሰዎች የነቢዩን (ዐ.ሰ.ወ) ሀዲሶች በመደለዝና በመበረዝ እ ኩይ ተግባር ላይ የተሰማሩበትም ወቅት ነበር:: ብልሹ የሆኑ ሰበካዎችና ቡድኖች (fatalists) መፈጠር ጀምረዋል:: የዚህ ዓይነት ቡድኖች እንቅስቃሴዎች መፈ ጠር ለአምባገነን መሪዎች የተያያዙት አገዛዝ ምቹ አጋጣሚ ፈጥሮላቸዋል::

ከታሪክ እንደምንረዳው በጊዜው የተከሰተው ማህበራዊ ልሽቀት ሰዎች ከኢስላም እንዲርቁ በር የከፈተ ነበር:: ኡማው ኡማውን ውድቀት ለማዳን ኢማም ሁሴይን በአምባገነኑ መሪ ላይ ያነሱት ተቃውሞታሪካዊ አስፈላጊነትም ነበረው በኢስላም ጥላ ስር በሰላምና በፍትሕ የመኖር መብት ተነፈገበትና ይሄ የጭለማ ዘመን በቁርአን ከተጠቀሰው ጋር ተመሳሳይነት አለው::

... وَمَنْ أَحْيَاهَا فَكَأَنَّمَا أَحْيَا النَّاسَ جَمِيعًا وَلَقَدْ جَاء تْهُمْ رُسُلُنَا بِالبَيِّنَاتِ ثُمَّ إِنَّ كَثِيرًا مِّنْهُم بَعْدَ ذَلِكَ فِي الأَرْضِ لَمُسْرِفُونَ

> «ነፍስን ያለ አግባብ መግደል፤ ነፍስን የገደለ ሰው ሰዎቹን ሁሉ እንደገደለ ነው፤ ከዚያም ከዚህ በኋላ ከነሱ ብዙዎቹ በምድር ላይ ወሰንንኃላፊዎች ናቸው::»(አል-ማኢዳህ 32)

ገዢው የኡማየድ ፓርቲ ይህንን የአላህ ትዕዛዝ በመቃረን በገዛ ህዝቦቹ ላይ የሰቆቃና የመከራ ብትር አሳረፈ:: የሚፈጸመው ግፍ በተለይ ያመዘነው በነቢዩ ቤተሰቦች ፣ በኢማም ዐሊ (ዐ.ሰ) ፣ ሀሰንና ሁሴይን (ዐ.ሰ) ተከታዮችና ደጋፊዎች ላይ ነበር::

አንድ የታሪክ ፀሀፊ በጊዜው ይደርስ የነበረውን የሰብዓዊ መብቶች መጣስ እንዲህ ገልጾታል::

«ሰዎች ይቃረዳሉ:: እጃቸውና እግሮቻቸው ይከረተፋል:: አይኖቻቸው በጋለ ሽቦ ተጉልጉለው እንዳ ወጡ ይደረጋል:: የነቢይን ቤተሰብ በመውደዳቸው ብቻ ብዙዎቹ

በተምር ዛፎች ላይ ተሰቅለዋል:: ሽብርና ፍርሃት በመንገሱ ነዋሪዎች ከቤቶቻቸው ሳይወጡ ለረዥም ወቅት ታፍነው ይቆዩ ነበር::

በመአዊያ ቢን አቡ ሱፍያ አገዛዝ ዘመን የተገደሉ ሰዎች ቁጥር እጅግ ብዙ ነበር የጥቂቶቹ ዝርዝር በታሪክ ተዘግቧል::

ሂጁር ቢን ዐዲይ የተባሉ የነቢይ (ዐ.ሰ) የተከበሩ ሰሐቢ ያለምንም ጥፋት በግፍ መገደላቸውን አል ሐኪም አልሙስተድሪክ» በተባለ መጽሐፍ ጠቅሷል:: ኢማም ሁሴይን (ዐ.ሰ) የዚህን ሰሐቢ መገደል በመቃወም ለሙአዊያ ቢን አቡ ሱፍያን የተቃውሞ ደብዳቤ ልከው ነበር:: «የፆ-ራምደውን ኢ -ፍትሐዊ ስርዓት በመቃወም ብቻ የነቢዮ ወዳጅ የነበሩትን ሂጅርና ተከታዩቹን የፈጃቸው አይደለህምን? እነዚህ ሰዎች የአላህ ዲን ሲጣስ መታገስ ስላልቻሉ ተገደሉ:: የአንተን ብቀላ የሚፈሩ ግን አይደሉም:: በኛ መሀከል የተደረሰውን ውል ጥሰህ ለነርሱ በቋጠርከው ቁርሾ ተገፋፍተህ ደማቸውን አፍስሰክ»

የሙአዊያን አምባገነናዊ አገዛዝ በመቃወማቸውና ለኢማም ዐሊ (ዐ.ሰ) ድጋፍ በመስጠታቸው የተገደሉ የሂጅር ተከታዮች ከነበሩት:-

1- ሸሪክ ቢን ሻዳህ አል-ሐድራሚ

2- ሰይፊ ቢን ሽዳድ አል ሸይባኒ

3- አብዱልራህማን ቢን ሀሰን አል-ኢንዚ

4- ቀቢሳህ ቢን ራቢዓ አል-አብሲ

5- ኪዳም ቢን ሀያ አል ግንዚ

6- ሚህሪዝ ቢን ሺሃብ ቢን ሙጃይር ቢን ሱፍያን ቢን ኻሊድ ብን ሙንቂር አልተሚሚ

ከነዚህም ውጭ በሙአዊያ የተገደሉ ተዋቂ ግለሰቦች ነበሩ::

1- አምሩ ቢን-ሁምቅ አል-ኹዛል የረሱል (ዐ.ሰ.ወ) ሰሐባ ሙሐጂር የነበረ በምስል (ዒራቅ) ተሰይፎ ጭንቅላቱ ወደ ዲማሽቅ (ደማስቆ) ተወስዷል::

2- አብዱላህ ቢን ያህያ አል-ሐድራሚና ጓደኞቹ

3- ረሺድ አል ሑጃሪ ሳይገደል በፊት እጆቹና እግሮቹ ተቆርጠው ነበር

4- ጁዋይሪያ ቢን ሙስህር አል-አብዲ

5- አውፈር ቢን ሁሴይን :- በኩፋ በዚያድ ሐይሎች የተገደለ የመጀመሪያው ተቃዋሚ ነበር::

በኢማም ሀሰን (ዐ.ሰ) ና በሙአዊያ መሀከል የሰላም ስምምነት ከተደረሰ በኋላ በባስራ ከተማ የደረሰውን የሰው ዕልቂት ኢብን አቲር የተባለታዬክ ምሁር እንዲህ ዘግበውታል::

«ዚያድ ሱምራህን ጊዜያዊ የበሰራ ገዥ አድርጉ ከሾመ በኋላ ብዙ ባስራውያ ተጨፍጭፈዋል፡፡ ኢብን ሲሪን እንደዘገቡት ዚያድ ከአካባቢው ሄዶ በነበረበት ወቅት ብቻ በሱምራህ የተገደሉ ሰዎች ቁጥር ስምንት ሺህ ይሆናሉ፡፡ የዋህ የሆኑትን ሳይቀር ስትገድል አትፈራም ወይ? ብሎ ዚያድ ጠይቀውት ሱምራህ ሰጠው ምላሽ የዚህን ቁጥር እጥፍ ቢገድል ምንም አይመስለኝም «የሚል ነበር፡፡ አቡ አል-ሰዋሪ አል አዳዊ ሲናገሩ፡- በአንድ ቀን ውስጥ አርባ ሰባት ጓደኞቼ ተገድለውብኛል፡፡ ሁሉም ሐፊዝ (ቅዱስ ቁርአንን በቃላቸው የያዙ) የነበሩ ናቸው፡፡

ይህ በኡማያድ ጀኔራሎች በህዝቡ ላይ የደረሰው እጅግ ጥቂቱ ታሪክ ነው ተዳፍኖ የቀረው ብዙ ነው፡፡

ከሁሉም በላይ በነቢዮ ቤተሰብ ላይ  የፕሮፓጋንዳ የስም ማጥፋት ወንጀል ይፈጽም ነበር፡፡ ሹሞችና ኢማሞች የነቢዩን ቤተሰቦች በተለይ ዓሊን፣ ሀሰንና ሁሴይንን በየኩጥባቸውና በየንግግራቸው እያብጠለጠሉ ይሰድቡና ይረግሙአቸው ነበር፡፡ በሰፊው ይነዛ በነበረው የዘለፋ ፕሮፓጋንዳ በስተጀርባው ሙአዊያ ቀዳሚው ሰው ነበር፡፡ አል-መሰዑዲ የተባሉ ታሪክ ፀሐፊ በሙአዊያና በሰዑድ መካከል ባንድ አጋጣሚ የተካሄደውን ክርክር ይጠቅሳል፡፡

*«አቡ ጃዕፊር ሙሐመድ ቢን ጃሪር አል ጠባሪ፣ ሙሐመድ ቢን ሒብ አልራዚን አቢ ሙጃሂድን፣ ሙሐመድ ቢን ኢሻቅን ፣ ኢብን አቢ ነድሪን ጠቅሰዉን ደዘገቡት አንዴ ሙአዊያ ሐጅ ያደርጋል፡፡ ከሰዑድ ጋር ጠዋፍ አድርገው እንዳበቁ ሙ አዊያ ህዝቡን ወደ ሚቀበልበት አዳራሽ ያመራል፡፡ ሰዑድን አጠገቡ አልጋው ላይ አስቀምጦት ስለ ዓሊ መጥፎ ንግግር ማናገር ጀመረ፡፡ ሰዑድ ንግግሩን በመቃወም እንዲህ ሲል ተናገረ፡- ዓሊን ታንቋሽሻለህን? በአላህ እምላለሁ የዓሊን አንዲት ችሎታ  ቢኖረኝ የአለምን ሀብት ሁሉ አልፈልግም፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ዐ.ሰ.ወ) በኸይበር ጦርነት ዋዜማ ዓሊን እንዲህ ብለው ያወድሱት ነበር «ነገ፤ የክብር ባንዲራ አላህና ነቢዩው ለሚወዱትና እሱም አላህና ነቢዮን ለሚወደው ፣ ከጦርነቱ ሜዳ ለማያፈገፍገውና አላህ ድልን በርሱ እጅ ለሚያመጣው የክብር ባንዲራ አኖራለሁ» ላሉለት፤ በተቡክ ጦርነት ዕለት «ሀሩን ከሙሳ ጋር እኩል ደረጃ እንደነበረው  አንተ ዛሬ ከኔ እኩል  በመሆንህ አትደሰትምን? ምንም እንኳ ን ከኔ በኋላ ሌላ ነቢይ ባይኖርም ያሉለትን፤ ዓሊን ከአለም ከያዘችው ሀብት በላይ እሳቸውን እወዳለሁ፤  ከዛሬ ጀምሬ በሕይወቴ እስካለሁ ፊትህን አላይህም ብለውት ጥለውት ወጡ ሲል ጽፏል፡፡*

በነቢዮ ቤተሰብና ተከታዮች ላይ ይደርስ የነበረው ጭቆና ቀጠለበት፡፡ ኢብን አሲር ሁኔታውን እንዲህ ይገልጻል፡፡

«ዚያድ አልሚራራ የተባለውን ሰው የኩፋ ገዥ አድርጎ ከሾመ በኋላ በኢማም አሊ ላይ የሚደረገው የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ አየለበት፡፡»

«አል መስዑዲም እንዲህ ሲል ዘግቧል፡፡

«ዚያድ ኩፋ በሚገኘው ቤተመንግሥቱ ነዋሪዎቹን ሰብስቦ ዓሊንዲረግሙ ይደረግ ነበር፡፡ የተቃወመ ሁሉ ይገደሉም ነበር፡፡»

ይህ የጥፋት ዘመቻ አሙር ቢን አብዱል ዐዚዝ ወደ ስልጣንእስከ መጣበት ጊዜ ቆይቷል፡፡ ቢን አብዱልአዚዝ የኡማውን አስተዳደር ከብልሹ መሪዎች በማፅዳቱ ሁኔታው ሊረግብ ችሏል፡፡ ዐሙርአጅግ ሷሊህ መሪ ነበር፡፡ በኡማያድ የተመረጡ ገዢዎችን በማባረር በፋንታቸው ለኢስላምና በሙስሊሞች ደህንነት የሚሠሩትንና በኢስላማዊ ዕውቀትና በቂ የአመራር ችሎታ ያላቸውን ሙስሊም መሪዎች ሾመ፡፡ በኢማም ዓሊ ላይ የሚካሄደውን እርግማን ዘመቻ በማስቆም ኹጢቦች ከዘለፋ ንግግር ይልቅ የሚከተለውን የቁርአን አያት ለሙስሊሞች እንዲስተላልፍ አደረገ፡፡

«አላህ ሆይ ! እኛንና እነዚህን በዒማናቸው የሚቃድሙንን ወንድሞቻችንን ምህረት አድርግልን፡፡ ከልባችንም ቅሬታንና ጥላቻን እጠብልን፡፡ አዛኝ ርህ ሩህና መሐሪ ነህና፡፡» አላህ በጎውእንዲሰራ ከክፍው እንዲ ንከለክል፤ ያዛል፡፡ ለሌሎችም በጎንድንሰራ፤ የአመጽንም መንገድ እንድንዋጋ ደንግጓል፡፡»

በዚህም የተነሳ በዑመር ትዕዛዝ መሠረት አሊሞች ይህንን ቁርአናዊ ዱአ በየጁምአ ኹጥባዎቻቸው እንዲጠቀሙበት አደረገ፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ነባራዊ ሁኔታዎች በተጨማሪም ኢኮኖሚያዊ ክስተቶች በኡማያድ ረገድ ለተመራው ኢስላማዊ አብዮት ምክንያቶች ነበሩ፡፡ ጊዜው የኡማያድ ፓርቲ ሀብት፣ የሀብት ምንጮች በጥቂቶች እጅ እንዲገባ በማድረጉ ብዙሃኑ የሙስሊሙ ህብረተሰብ ለድህነት ተጋለጠ፡፡ የመኖር ዋስትና ነው በጨቋኞችና በዧሊሞች እጅ ወደቀ በጣት ሚቆጠሩ ሰዎች እየበለፀጉ ሲሄዱ አብዛኛው ህዝብ ለደህንነትና ለድንቁርና በመሰጠቱ ታላቅ ቁጣን ቀስቀሰ፡፡ ለዚህም ነው የተቀጣጠለው ፍትሃዊ ትግል ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊ ማህበራዊ መነሻ አለው የሚባለው፡፡

***ይህው የሙስሊሙ ክፍል ኢኮኖሚያዊ መብቶች በመነጠቁ ጥቂቶች ከበሩ:: ቁርአን ሲያሰጠነቅቅ:-***

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُواْ إِنَّ كَثِيرًا مِّنَ الأَحْبَارِ وَالرُّهْبَانِ لَيَأْكُلُونَ أَمْوَالَ النَّاسِ بِالْبَاطِلِ وَيَصُدُّونَ عَن سَبِيلِ اللّهِ وَالَّذِينَ

يَكْنِزُونَ الذَّهَبَ وَالْفِضَّةَ وَلاَ يُنفِقُونَهَا فِي سَبِيلِ اللّهِ فَبَشِّرْهُم بِعَذَابٍ أَلِيمٍ

***«እነዚያንም ወርቅና ብርን የሚያደልቡትን በአላህም መንገድ ላይ የማያወጧትን በአሳማሚ ቅጣት አብስራቸው::»*** ***አል-ተውባህ 34***

مَّا أَفَاء اللَّهُ عَلَى رَسُولِهِ مِنْ أَهْلِ الْقُرَى فَلِلَّهِ وَلِلرَّسُولِ وَلِذِي الْقُرْبَى وَالْيَتَامَى وَالْمَسَاكِينِ وَابْنِ السَّبِيلِ كَيْ لَا يَكُونَ دُولَةً بَيْنَ الْأَغْنِيَاء مِنكُمْ وَمَا آتَاكُمُ الرَّسُولُ فَخُذُوهُ وَمَا نَهَاكُمْ عَنْهُ فَانتَهُوا وَاتَّقُوا اللَّهَ إِنَّ اللَّهَ شَدِيدُ الْعِقَابِ

***«አላህ ከከተሞች ሰዎች ሀብት) በመልእክተኛው ላይ መለሰው (ሀብት) ከናንተ ውስጥ በሀብታሞቹ መካከል ተዘዋዋሪ እንዳይሆን አላህና ለመልእክተኛው ለዝምድና ባለቤትም አባት ለሌላቸው ልጆችም፣ ለድሆችም ለመንገደኛም (የሚሰጥ) ነው፤ መልዕክተኛውም የሰጣችሁን ማንኛውንም ነገር ያዙት:: ከርሱም ከከለከላችሁት ነገር ተከልከሉ:: አላህንም ፍሩ፤ አላህ ቅጣቱ ብርቱ ነውና»*** ***(አል-ሐሽር 7)***

***ይህ ኡማየዶች የተከተሉት ሚዛናዊ ያልሆነ የኢኮኖሚ መስመር ግና 4ቱ ካሊፎች ዘመን ነበር አንዳንድ የኡማያድ ያቆጠቆጠው ባለሥልጣኖችን በምዝበራ የተከማቹትን የሀብት መጠን ታሪክ ፀሀፍት ይጠቅሳሉ::***

***«በሙአዊያ ዘመን የግብጽ ገዢ የነበረው አምሩ ቢን አል-አስ ብቻ በግብጽ ሀገር 325000 ዲናር 200000 ዲናር የሚያወጣ የጥራጥሬ ሀብት 10000 ዲናር የሚገመት አል-ወህት ተባለ የታወቀ የእርሻ መሬት ነበረው::***

***ሌላው አብዱልራህማን ቢን አውፍ ይባላል:: ሲሞት ብቻ 16 ቦታ የተከፈለው ሀብቱ ለእያንዳንዱ ሚስቶቹ በነፍስ ወከፍ የደረሳቸው (የተሰጣቸው) 80000 ድርሃም ነበር::***

***«መርዋን ቢን አል ሀኪም ከአፍሪካ ግዛቶቹ 500000 ዲናር ሰብስቧል» ፣ ኢብን አል ዓስ 100000 ዲርሃም ስጡ ተቀ ብሏል:: አብዱላህ ቢን ኻሊድ ቢን ዑሳይድ 400000 ዲርሃም ስጦታ አግኝቷል:: የያዕላ ቢን ዑመያህ ሀብት 800000 ዲናር ይበልጣል:: ሰዐድ ቢን ኢቢወቀስ ሲሞት 250 000 ዲረሃም ውርስ ትቷል:: ሰግድ ቢን አል-ሙሰይብ እንደዘገበው ዘይድ ቢን ሳቢት ሲሞት እጅግ ግዙፍ የወርቅ የብር ክምችትእንዲሁም 100000 ጥሬ ዲናር ነበረው::»***

***እነዚህ ለምሳሌ ያህል የተጠቀሱት ናቸው::  በአጠቃላይ ከዚህ የምንረዳው ጥቂት ግለሰቦች ሹሞችና አስተዳዳሪዎች የግላቸው የሆነ የገዢ መደብ*** /Aristocracy/ ***ሲፈጥሩ፤***

የተቀረው ህዝብ ከኡማው ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ሳይጠቀም በድህነትና በጅህልና እንዲኖር መደረጉን ነው፡፡

በመሪዎቹ አምባገነናዊ አስተዳደር ፍትሕ ያጠው ኡማ ህይወቱ በኢስላማዊ ህግ፣ ፍትሕና አስተዳደር ለማስመለስ መላ ማፈላለግ ጀመር፡፡ በጊዜው የኡማውእሮሮ ሊስማ፣ ስቃይና መከራቸው ሊጋራና ወደ በሚያካሄዱት ፍትሕ ትግል ሊመራቸው የሚችሉት ሰው ኢማም ሁሰይን ቢን አቢጣቢል ነበሩ፡፤ የያዚድ፣ የዚያዱና የሌሎቹንም አምባገነኖች ስርኣት ፍጻሜ ለማቃረብ በወቅቱ ኢስላማዊ አብዮት መቀስቀስ ብቸኛው አማራጭ ሆነ፡፡

## ኢማም ሁሰይን በመዲና

ሁሴይን የኡማያድን ተንኮል የተረዱት አስቀድመው ነበር፡፡ ኡማው በኡማያድ አገዛዝ ስር ታላቅ ውድቀት እንደሚደርስበት ገብቶአቸዋል፡፡ ኡማውን ከዚህ አደጋ ለማዳን ባላቸው ህጋዊ ኃላፊነት መንቀሳቀስ ነበረባቸው ፡፡ በመሆኑም አላማቸውን ከግብ ለማድረስ መዲና የመቆየታቸው ሁኔታ አስፈላጊ ሆነ፡፡ መዲና በወቅቱ ፖለቲካዊ ውጥረት ሰፍኖባታል፡፡ ሙአዊያና በሃሰን መካከል የተደረሰው ስምምነት በመፍረሱም ህዝቡ የተሰማውን ቅሬታ በመግለጽ ጀምሯል፡፡ የዚድን እንዲቀበል ዘንድ በአል ወሊድና በመርዋን የሚደረግባቸው ጫና አይሏል፡፡ ኢማም ሁሴይን ግን በአሉታዊ ምላሻቸው እንደጸኑ ናቸው፡፡ የያዚድ ወደ ኸሊፋው ስልጣን መምጣት በሀሰንና ሙአዊያው መካከል የተደረገውን ውል የሚፃረር በመሆኑና የኡማውን መሠረት የሚያናጋ ውጤት በማስከተሉ ሁሴይን ወቅታዊ እርምጃዎችን ለመውሰድ ወሰኑ፡፡ የያዚድ ወደ ከሊፋነት መሸጋገር ኢስላማዊ መንገድ የተከተለ አለመሆኑ፤ የአመራር ብቃት አለመኖርና፣ የኡማያድ ጋዢ ቤተሰብ ኡማውን ከኢስላምና ከሙስሊሞች ተቀባይነት ሳያገኝ ነቢዩ ቤተሰብና ከቀደምት ተከታዮቻቸው መንጠቃቸው ተደማምረው ኢማም ሁሴይን ለሚያካሂዱት ፍትሐዊ ትግል ለመዘጋጀት ወደ መካህ መሰደድ የግድ ሆነ፡፡

ኢማም ሁሴይን ከአልወሊድና መርዋን ቢን አል ሀኪም ጋር የመጨረሻ ክርክር ካደረጉ በኋላ ቤተሰቦቻቸውን የቅርብ ዘመዶቻቸውንና ተከታዮቻቸውን ለረጅም ታሪካዊ ጉዞ እንዲዘጋጁ አደረጉ፡፡ ለዚህ ድርጊታቸው የትግሉን ችቦ አቀጣተሉ፡፡ ለ ላለማዊ ፀረ-ጭቆና ትግል ተለኮሰ፡፡ ጉዞአቸውን ወደ መካ ሆነ፡፡ የኡማያድን ፀረ-ኢስላም አገዛዝ ለማናወጥና ኡማውን ከታላቅ ውድቀት ለመታደግ ቀዳሚውን እርምጃ ወሰዱ፡፡

ከታላላቅ ድሎች፣ ማህበራዊ ለውጦች በስተጀርባ ሁሌም ጠንካራ መሪዎች አሉ፡፡ የአመራር ብቃታቸው የተዋጣላቸው፣ የህዝባቸውን ፍላጎት በጥልቀት የተረዱ፣ ምሉዕ ህይወታቸውን ለህዝባቸው መስዋእት ያደርጉ ፣ በአዕምሮአቸው ንቃተ-ህሊናን የሚተክሉ እነዚህ በሳል መሪዎች ታሪካቸውና የትግሎቻቸው ፍሬ ዘላለማዊ ሆኖ ይኖራል፡፡

ሁሴይን (ዐ.ሰ) በኢምባገነኑ የኡማያድ ዙፋን ስር የፍትሕ እ ሳተ ጋሞራ ሊያኖሩ ተመረጡ የያዚድን ጨቋኝ ሥርዓት በእስላማዊ ፍትሕ ሊተኩት ታጩ፡፡ ለዚህ ዓይነት ህገወጥ ሥርዓት ተገቢው እስላማዊ ጂሃድ ብቻ መሆኑን አስመሰከሩ፡፡ በተያያዙት ፍትሓዊ የጂሃድ እንቅስቃሴአቸው ካሸነፉ በኢስላም ዳግም ህይወት ሊዘሩ፤ ወይንም አስፈላጊውን መስዋዕት ከፍለው ሊያልፉ ቆርጠው ተነሱ፡፡ ሸሂድ ሆነው ሊያልፉና ደማቸው በታሪክ ምእራፎች ብቅ እያለ በጨቋኞችና በሥርዓቶቻቸው ላይ ተቀጣጣይ አብዮቶችን ይጭራል፡፡

በመካ ሊጀምሩት ያሰቡት ቷሪክ በጨቋኝ መሪ ላይ የተደረገ የመጀመሪያና ኢስላማዊ አብዮት የኢስላምን መሰቷዊ መርሆ ዎችና ቅደም ተከተል ከግምት ያስገባ ነበር:: ሁሴይን ወንድሞቻቸውን፣ ልጆቻቸውን የቅርብ ዘመዶቻቸውንና ታማኝ ተከታቻቸውን አስከትለው ጉዞአቸውን ቀጠሉ:: ወደ ኋላ የቀረው ወንድማቸው ሙሐመድ ቢን አል ሀናፊያ ብቻ ነበር:: ሀናፊ ለሁሴይእንዲህ ብሎ መክሮ አቸው ነበር::

« በምትሄድባቸው ከተሞች የሚኖሩ ህዝቦች ከፊሎች ሚደግፍህ፤ ከፍሎቹ የሚቃወሙህ ይሆናል ብዬ እፈራለሁ፤ የሚቃወሙህ ይዋጉሃል:: የጥ ቃታቸውም ሰለባ ትሆናለህ:: ይህ የኡማሙ ምርጥ ቤተሰብም ደማቸው ይፈሳል:: በጠላቶቻቸው እጅም ይዋረዳሉ::» አላቸው:: «ሁሴይንም» እንደሚፈጸም አስባለሀ ·:: ኢንሻአላህ::» አሉት ሀሳባቸው ገፋበት::

ሁሴይን ለሽሂድነትእንደሚበቁ የነቢዮን ሀዲስ ጠቅሰውለት የተናገሩት ሌላው ወንድማቸው ዑመር ቢን ዓሊ ቢን አብጣሊብ ነበሩ:: ቢን ዑመር ስለዝህ ጉዳይ ከነቢዮ የሰሙት እንዳለ አስተላልፈዋል:: በዚሁ መሠረት ነቢዩ የሁሴንና ጀሳቸውን አብረው ለሺሂድነት እንደሚበቁና ጃናዛቸውም በአንድ አካባቢእን ደሚያርፍ ተንብየው ነበር:: ልጃቸው ፋጡማንና ቤተሰቦቻቸውን የበደለ አንድም ሰው ጀነትእንደማይገባ ነቢዩ አስረድተዋል::

ሁሴይን በጠላቶቻቸውእጅ እንደሚገደሉ ገምተዋል:: ይሁን እንጂ ባርነትና ችቆና ከሞት ይበልጣና ውሳኔያቸውን አላስቀየራቸውም:: አንዳንድ የመዲና ነዋሪዎች ለሁሴይን ህይወት በመሳሳት በያዚድ ላይ ያወጁትን ጂሃደእንዲቀይ ሩ አሳስበዋቸው ነበር:: ከነዚህ ለሁሴይን ታላቅ ፍቅርና ከበሬታ ከነበራቸው የቅርብ ዘመዶቻቸው ውስጥ ኡም ሰላማ የተባሉት የነቢዩ (ዐ.ሰ.ወ) ባለቤት ይገኙበታል:: ኡም ሰለማ የነቢዮን ትንቢት በመናገር ሁሴይን ሊገደለ እንደሚችሉ ጠቆሙዋቸው:: ለኡም ሰላማ የሁሴይን ምላሽ የነበረው ግን ‹እናቴ ሆይ! እንደሚገደገል እያወቅኩኝ ነ ው እምሄደው!» አብዱላህ ቢን ዑመር ቢን አል-ኻጣብም ሁሴይን ሀሳባቸውን እንዲቀይ ሩና ለያዚድ ድጋፋቸውን እንዲሰጡ መክረዋቸው ነበር:: ሁሴይን ግን ጨቋኙን ስርዓት የሚታገሱበት ልብ አልነበራቸውም:: ኡማው ለአረማዕያዊ ጭቆናና ፍትሕጦት ሰ ،ጋለጥ እንዴት ይታገሱታል:: ለዚህም ነው አብዱላህ ቢን ዑማርን እንዲህ ሲሉ የመለሱላቸው::

«ያ አቡ አብዱልራህማን! በአላህ ዕይታ ህይወት ዋጋ ቢስ ነገር እንደሆነች እስራኤላውያን የያህያ ቢን ዘካሪያን ጭንቅላት ቆርጠው ለሴትእንዳበረከቱ ሲታይ አትረዳምን? አላህ በአይሁዶች ላይ የሚወሰደው ቅጣት ቢዘገይ እንጅ አይቀርም?. . »

# የአላህን ነቢይ ስለመሰናበታቸው

ሁሰይን የነቢዮ መሃመድ (አያታቸው) (ዐ.ሰ.ወ) ያረፉበትን መቃብር ለመጨረሻ ጊዜ ከጎበኘ (ከዘየሩ) በኋላ መዲናን ዳግም ላይመለሱባት ተሰናበቷት። ከዚህ በኋላ ኢማም ሁሴይን ወደዚች ከተማ ብቅም አላሉም። የኢማም ሁሴይንና የነቢዩ (ዐ.ሰ.ወ) ቀጣይ ግንኙነት ጀነት ብቻ መሆኑ ሁሴይን አውቆውታል ። ኢማም ሀ ሁሴይን (ዐ.ሰ) በአያታቸው መቃብር አጠገብ ሁለት ረከአ ሰላት ከሰገዱ ኃላ የሚከተለውን ዱአ አደረጉ።

«ያ አላህ! ይህ ከጎኑ የቆምኩት መቃብር ያንተ መልዕክተኛ የነቢዮ መሃመድ (ሰዐወ) ነው። እኔም የነቢዮ የልጅ ልጅ ነኝ። ምን ለማድረግ እንዳቀድኩ ታውቃለህ። ያ አ ላህ ሆይ በጎውን ነገርእንደማፈቅር ሁሉ፤ ክፍውን እጅግ እጠላለሁ። ፤ የሚከተለውን የህይወት አቅጣጫዬን ታውቃለህ ። ያ አላህ የክብር የውዳሴ ባለቤት የሆንክ ፈጣሪ ለአንተንና ለመልእክተኛ የሚያስደስትን ነገር ሁሉ ምረጥልኝ።

የሁሴይን በዕለተ ጁመዓ ወደ መካ ተንቀሳቀሰ። ረጅሙን በረሃ አቋርጠው አብረው ከተጓዙ ሰዎች አብዛኞቹ የኢማም ሁሴይን የቅርብ ዘመዶችና ተከታ ዮቻቸው ናቸው። ከሁሉም በላይ ኢማም ሁሴይን በጠንካራው እህታ ቸው ዘይነብ ታጅበው ነበር ። በጽኑ ዓላማ የተሞላውን ይሄን ጉዞ ኢማም ሁሴይን የጀመሩት በዚህ የቁርአን አያት ነበር።

فَخَرَجَ مِنْهَا خَائِفًا يَتَرَقَّبُ قَالَ رَبِّ نَجِّنِي مِنَ الْقَوْمِ الظَّالِمِينَ

«የፈራና የሚጣባበቅ ሆኖ ከርሷ ወጣ፤ ጌታዬ ሆይ ! ከበደለኞቹ ህዝቦች አድነኝ አለ። »አል-ቀሰስ 21

በረጅሙ ጎዙአቸው በመንገድ ላይ አብዱላህ ቢን ሙጢዕን አግኝተው ነበር። ቢን ሙጢዕ ኢማም ሁሴይን ላይ አደጋ ቢደርስባቸው ኡማው መሪ አልባ ሊሆን እንደሚችል የተሰማውን ሰጋት ገለጠላቸው። የሙስሊሞችን ችግሮች ሊፈታ የሚችል መሪ ሊታጣ እንደሚችል አሳሰባቸው። ተስፋቸው ሁሉ በሁሴይን ዙሪያ ነበር። ልቦች ሁሉ ለርሳቸው ባለቸው ፍቅር ተነደፉ። የኡማው መከታ የችግሮቻቸው ግንባር ቀደም ተጋፋጭ የሆኑት ሁሴይን ጨቋኙን የያዚድ አገዛዝ ሊያሽመደምዱ የሚችሉ ብቸኛው ሰው ነበሩ። አብዱላህ ቢን ሙጢእ ደጋግሞ ስጋቱን አንፀባረቀ፦

«በአላህ ይሁንብኝ፤ አርሶ ቢገድሉ እኛ ተከትለን ለባሪነት እንዳረጋለን።»

ይህ አብደላህ ቢን ሙጢዕ ስጋት በወቅቱ የሙስሊም ዓለም ሁሉ ላይ በኡማያድ አገዛዝ የደቀነውን አደጋ የሚያንጸባርቅ ነው። በኡማው ላይ ያንዣበበውን ይህን አስከፊ የውድቀት ዳመና ሊገፋ የሚችል ብቸኛ መሪም ሁሴይን ብቻ ነበሩ።

«በአላህ ይሁንብኝ፤ አርሶ ቢገደሉ ዕጣ ፋንታችን ባርነት ይሆናል።» የቢን ሙጥዕ ቃል። ነበር ቀጥሎ ቢን ሙጢዕ የሁሴይንን መድረሻ ጠየቃቸው? ሁሴይንም ወደ መካ እንደሚሄዱና ከዙያ የስደታቸው መጨረሻ (መቋጫ) የት እንደሆነ አላህ እንደሚገልጥላቸው ትእንደሚመራቸው) ነገ ሩት። ቢን ሙጢዕም የመጨረሻ ምክሩን እንዲህ ሲሉ። «መካ እንደደረሳችሁ ከዛች የጥፋት ከተማ ከሆነችው ኩፋ አጠገብ እንዳትደርሱ። የአባትዎ ህይወት የተቀጠፈበት፣ ወንድምዎም ተከድተው ለሞት የዳረጋቸውን የመቁሰል አደጋ የደረሰባቸው እዚህ ነበር። ስለዚህ የአላህን ቤት ብቻ መጠጊያዎ ያድርጉ። የሂጃዝ ሰዎች (ዐረቦች) የሞቀ አቀባበል ያደርጉላቸዋል። እር ሶ ለግድያ ቢጋለጡ ግን እኛ ባርነትን ስር መውደቃችን ነው።»

የመካው ጉዞ ረጅምና አድካሚ ነበር። የበረሃው አሸዋ ፀሐይ ቃየከለደ ይለበልባል። የሁሴይን ጭፍራ የንዳድ ማዕበልያጣሱ አሸዋማ ኮረብቶችን እያቆራረጡ፤ ፊት ፊታቸው ተዘረጋውን ረጅም የበረሃ አድማስ እየገመሱ ወደፊት ገፉ።

ሁሴይን የወጡት መንገድ የአባታቸው ዓሊ ቢን አቢ ጧሊብ ቁር ይሾችን በመቃወም የመሩትንና የአራቱ ፋጡማዎች ጉዞ ተብሎ የሚታወቀውን ዓይነት ነበር (ኢማም ዓሊ (ዐ.ሰ) ከመካ ወደ መዲና ሲሰደዱ አብሯቸው የተጓዙት አራት ሴቶች ስሞቻቸው ሁሉም ፋጡማ የነበሩበት ነው። ሴቶች የነቢዩ ቤተሰብ ጋር ዝምድና ነበራቸው።
1-ፋጢማ አልዛህራ
2-ፋጢማ የአሳድ ቢል ሐሺም፤ የኢማም ዓሊ እናት ነበሩ
3-ፈጢማ ቢንት እል ዙበይር የነቢዩ ሞግዚት የነበሩ
4-ፋጢማ የሃምዛ ቢን አብዱል መጠሊብ ልጅ ነበረች) ። ይሁን እንጂ የአሊ ጊዜ ድብቅና ሚስጥራዊ ጉዞ ሲሆን ሁሴይን የመሩት ስደት በግልጽ የተከናወነ ነው። ሽሽት አልነበረም። ልባቸው የዓሊ ዓይነት ድፍረት ነበረው። ኢብን አል-ዙበይር ከዋናው መንገድ አሳብረው ፋናቸውን በማጥፋት ቢጎዙም ሁሴይን የተከተሉት ዋናውን የበረሃ መንገድ ነበር። ሁሴይን ይሄን ያደረጉት ሆን ብለው ነበር። በአምባገነኑ የያዚድ አገዛዝ ላይ ያላቸውን ቀጥተኛ ተቃውም ለመግለጥና ጉዞአቸው ሽሽት ሳይሆን የፊት ለፊት ፍልሚያ መሆኑን ለነቢዩ ቤተሰብና (ዐ.ሰ) ለሙስሊም ኡማ ለማስገንዘብ ነበር። ሁሴይን ለምን መንገድ አሳብረው እንዳልተጓዙ ከቤተሰቦቻቸው በእዳንዶቹ ለሚጠይቁአቸው ሲመልሱ:-

> «አላህ ራሱ የሻውን ፍርድ እስኪሰጠን ድረስ በቀጥተ ኛው መንገድ ላይ እራመዳለሁ።» ይሉ ነበር።

በሌሎች ሥፍራዎች ሁኔታዎች የተለያዩ ቅርጽ ይዘዋል። የመዲና መሐጂሮችና (ሰደተኞች) ና አንሷሮ (ረጂዎች)ና ብዙ የነቢዮ ሰሐቦች በተገኙበት ሹራ ተቀምጠው

ኢማም ሁሴይን የመልዕክተኛውን (ዐ.ሰ.ወ) ከተማ ለቀው የወጡበትን ሁኔ ይመለክራሉ:: ይህ ለያዚድን ህገወጥ አገዛዝ ለመቃወም የተደረገ ውሳኔ መሆኑን ያምናሉ:: ታዲያ ኡማው ፀጥታን ለምን መረጠ?

በከተማቱ የኢማም ሁሴይንና የአል-ዘህራ ቅጢር ግቢ ሰጥ ረጭ ብሏል:: የሀዘን ጣል ተንጣሎበታል:: ሁሴይን ለቀው ከወጡ ከተማቷ ታለቅሳለች:: ሕዝቡ ከመሀከላቸው መሪያቸውን በማጣቱ በሀዘንና በፍርሃት ስሜት ተውጧል:: በልባቸው በድንጋጤና አለመረጋጋት ይስተዋላል:: የመዲናውያን ስጋት ሁሴይን በደጋፊዎቻቸው እንዳይከዱና ለጠላቶቻቸው አሳልፈው እንዳያጋልጧቸው ነው:: ይህ ከተፈፀመ ታላቁ የኢስላም ኮከብ ከሰማይ ወደቀ እንደማለት ነው::

ዕንባ ያቀረሩ ዓይኖች ወደ ሁሰይን ቤት መስኮቶች ይመጣሉ:: ጥቁር መጋረጃ የለበሱ መስኮቶ ብቻቸውን ቀርተዋል:: ትላንት የሶላት ብርሃን የሚያፈነጥቅ ቤት ብቻውን ቋሚል:: የሰጋጆች ለአላህ በሚያቀርቡት ኢባዳ ክንውኖች የተሞላ ህይወታዊ ግቢ በጭለማ ተውጧል:: በሮች፣ መስኮቶች ከነርሱም በስተጀርባ የመዲናውያን ልቦች ዓይኖች ወደ ተራቆቱ መንገዶች ያፈጣሉ:: ሁሴይን መች ይሆን ደግሞ የሚመለሱት? ወይስ እንደወጡ ይቀራሉ? የዘመዶቻቸው አንደበቶች ለተለዩአቸው መሪያቸውና የቅርብ ዘመዶቻቸው ፣ ወንድሞችና እህቶች ያለቅሳሉ? ዘለዓለማዊ ዕንባን ያፈሳሉ::

ዛሬ ብቻቸውን በቆመው የነቢዩ ቤተሰብ መንደር ትላንት የቤተሰብ ጓዳ ነበር:: የነቢዩ ቤተሰቦች ሥለ ዲናቸው ያወጉበት ቤቱ ራሱ ጭቆናን የመታገል አምሳያ ነው:: የትግል ተምሳሌትነት ድምጽ አለው:: የሕዝቦቹን ድምጽታሪካቸውን ከ ጅምር እስከ ፍፃሜው ይተርካል (የፍትሕ ታሪክ)::

ሁሴይን ረጅሙን የበረሃ ጎዞ ሊያገባድድ ነው፤ በወረሃ ሸዕባን ሶስተኛው ቀን ላይ መካ ገቡ:: የአላህ ምልክትም በህይወታቸው ላይ ተፈጸመ::

وَلَمَّا تَوَجَّهَ تِلْقَاء مَدْيَنَ قَالَ عَسَى رَبِّي أَن يَهْدِيَنِي سَوَاء السَّبِيلِ

«ወደ መድየን አቅጣጫ ፊቱን ባዞረ ጊዜምታጌቀጥተ ኛውን መንገድ ሊመራኝ እከጅላለሁ አለ::» [አል-ቀሰስ 22]

## ሁሰይን በሀረም

ሁሴይን በመጨረሻ ነቢዩ (ዐ.ሰ.ወ) ከአላህ የተላከላቸውን መለኮታዊ መልዕክት (ወሂይ) የተቀበሉበትን ቃቦ የመካ መንደር ደረሱ:: ያረፉትም በዓል-ዕባስ ቢን አብዱልሙጢሊብ ቤት ነበር:: ከዚህ የነቢዮ ቤተሰብ መሀከል ሆነው ፖለቲካዊ እንቅስቃሴያቸውን ማደራጀት ጀመሩ::

የሁሴይን መካ መግባት በነዋሪው ዘንድ ታላቅ ዜና ነበር:: በወቅቱ የዑምራ የጸሎት ሥነ-ሥርዓት ላይ የተሰማሩ ሰዎች ከሀረም ወደ ሁሴይን መጉረፍ ጀመሩ:: የሁሴይን አመጣጥ የመዲናውን የያዚድ አገዛዝ በመቃወም መሆኑን የሕዝቡ ጆሮ ደረሰ:: ደጋፊዎችና መልዕክተኞች ከየአከባቢው ቀበሌዎችና ግዛቶች ወደ ሁሰይን አመሩ:: ሁሴይንም በሀገሩ ለተለያዩ የጎሳ መሪዎቕዋቂ ግለሰቦችና ህዝቦቻቸው መልዕክታቸውን መላክ ጀመሩ:: የመልእክ ቸው ዋና ዓላማ ህዝቡ በያዚድ አገዛዝ ላይ ለጂሃድ እንዲነሳሳ የሚያሳስብ ነበር:: አንዳንድ መሪዎችና ሕዝቦች በሥልጣን፣ በጉቦና ሃይል ተገደው ለያዚድ የሰጡትትን ድጋፍ እንዲ ሽሩና ለ ኢስላማዊ ፍትሕ ብቻ ታማኝ እንዲሆኑ ሁሴይን አጥብቀው ተማጸኑ::

ህዝብም በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በየሀገሩ ሹራ ተቀመጠ፡ በጥልቀትም መከረበት:: ሁሉም አንድ ግንዛቤ ላይ ደረሰ:: የሁሴይን መካ መቀመጥ በኢስላም ታሪክ የትግል ሂደት አዲስ ምዕራፍ ከፋች መሆኑን ግንዛቤ ጨበጡ::

የሁሴይን መካ እቅዳቸው የሚከተሉትን ነጥቦች መሠረት ያደረገ ነበር::

1. ብዙሃኑን ህዝብ በተከተዱት የጂሃድ መንገድ ላይ ማሳመን
2. ህዝቡን ለትግሉ መቀስቀስና በአስተዳደር ጉዳዩች ላይ ኢስላማዊ መመሪያዎችንና ህጎችን ለይቶ እንዲያውቁ ማድረግ፡-
3. ህዝቡን የሚመሩበትን ለጂሃድ የሚያንቀሳቅሱበሰት ምቹ ቃ ጊዜና ስትራቴጂካዊ እቅዶችን መንደፍ
4. በያዚድ ላይ የሚካሄደውን ተቃውሞእንቅስቃሴ ማፋጠንና ውድቀቱን የሚያቀርቡ እርምጃዎችን መውሰድ፣ ይህ ለቁርአናዊ መርሆችና በነቢዩ (ዐ.ሰ.ወ) ሱንና ስር የሚመሰረተውንና በኢማም ስር የሚተዳደረውን ኢስላማዊ መንግስት ከመመስረት በፊት የሚመጣ ቅድመ ሁኔታ ነበር::

እነዚህ ሃሳቦች ሁሴይን በፃፉዋቸው ደብዳቤዎችና በላኩዋቸው መልክቶች ውስጥ በሰፊው ይንፀባረቃሉ:: ዓላማቸው የሁሉም ሙስሊም ልብ ትርታ ነበርና በኡማው ዘንድ አዳሽ መንፈስን ፈጠረ:: የነቢዩ (ዐ.ሰ.ወ) ቤተሰብ ደጋፊዎች ማዕከል በሆነችው ዒራቅ ጠንካራ የተቃውሞ ኃይል አቆጠቆጠ:: በሱለይማን ቢን አል-ቁዛእ ቤት የተሰባሰቡት

ቁልፍ እንቅስቃሴው መስራቾች የአከባቢውንና የኡማውን ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ከመረመሩና በተለይ ከሙአዊያ ሞትና የያዚድ ወደ ስልጣን መምጣት ያስከተለውን የስጋት ዓለም በጥልቀት በማጥናት ኢማም ሁሴይንን ለመደገፍና ለመከተል በርሱም የሙጃሂዲን ጦር ስር ገብተው በተራ ወታደርነት ለመዋጋት ወሰኑ:: የሱለይማን ቢን ሱርድ አል-ቁዛሪ ባደረጋቸው ንግግር ውስጥ እንዲህ የሚል ነበር::

«ሙአዊያ ሞቷል:: ሁሴይን በኡማያዶች በመቃወም ወደ መካ ተሰደዋል:: እናንተ ደግሞ ደጋፊዎች (ሺአዎቹ) ናችሁ:: የአባቶቻቸውም ሺዓዎች (ደጋፊዎች) ነበራችሁ:: አሁን የሳቸውን ደጋፊዎችና ወታደሮች ለመሆን የሚትፈልጉ እንደሆናችሁ ጥሩዋቸው፣አልያም ፃፉላቸው:: ህይወታችሁን ጠላቶቻቸውና ጠላቶቻችሁ የሆኑትን በመዋጋት የሚትረዱ ከሆነ አሳውቀዋቸው:: ውድቀትን፣ ሽንፈትና፣ፍርሃት የሚያሸንፉዋችሁ ከሆነ የማትፈጽሙትን ቃል አትግቡላቸው:: ህይወቱንም ለአደጋ አጋልጣችሁ አትስጡ::» የተሰበሰበውን ህዝብም ባንድ ድምጽ ጠላቶቹንም እንዋጋለን ነፍሶቻችንንም ለርሱ ድጋፍ ሰንል እንሰዋለን » አሉት::

ለኢማም ሁሴይን እንዲህ የሚል ደብዳቤም ፃፉላቸው:-

«በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው:: ከርሱ ሌላ ኃይል አለመኖሩን እንመሰክራለን:: ጠላትህን የጠፋውን አላህንናመሰግናለን:: ይህ ገዥ ህገወጥ በዳይ ኡማውን ከመሰረታዊ መብቶቹ የነፈገ፣ንብረታቸውን የዘረፈ፣የኡማውን ጠንካራ ሰዎች እያጠፋ ደካሞቹን ክፉዎችን ያነገሰ ነበር:: እኛ አሁንም ምንም መሪ የለንም:: ወደ እኛም እንዲመጡ እንጠይቃለን:: በእውነተኛውና ቀጥተኛው መንገድ ሰብንድታዋህደን እንፈልጋለን:: በሁለቱ ዒዶችና በጁሙዓ ስላቶችም ሹሙን አል-ኑማን ቢን በሺርን ተከትለን መስገድ አቁመናል:: እርስዎ ወደ እኛ እንደሚመሩ እርግጠኛ ብንሆን ከከተማይቷም እናባርርዋለን:: ኢንሻአላህ:: ወሰላሙ አ ላይኩም ወረህሙቱላህ ወበረካቱሁ::»

«ይህን መልእክታቸውን በአብደላህ ቢን ሳቢእ አል-ሐማዳኒና በአብዱላህ ቢን ዋል እጅ ላኩ:: ከሁለት ቀናት በኋላ ተጨማሪ ሁለት ደብዳቤዎችን ሰደዱ:: በአጠቃላይ ሕዝቡ 250 የሚሆን የድጋፍ ደብዳቤዎችን ጽፏል:: ሶስተኛ መልእክተኛቸውንም ላኩ:: ለሁሴይን ያላቸውን የድጋፍ ድምጽ በደብዳቤዎች ከገለጡትዋቂ የዓ ራቅ ሰዎች መሀከል ሸባዝ ቢን ሪብዕ፣ሐጃርቢን አብጃር፣ ያዚድ ቢን አልሐሪስ፣ ያዚድ ቢን ሩዋይም፣ዑርዋህ ቢን ቀይስ፣ዑመር ቢን አል ሐጃጅ አል ዛቢዲና ሙሐመድ ቢን ዑመይር አል ተሚሚ ይገኙበታል::»

ሁሴይንን በበኩላቸው ለኩፋውያን በላኩት ደብዳቤ ለሳቸው የገቡትን ቃል እንዲጠብቁና ልዩነታቸውን ፈትተው በአንድነት እንዲነሱ አሳሰቡዋቸው፡፡ በፊት ኢማም ዐሊ (ዐ.ሰ) በልጃቸው ሀሰን ላይ የደረሱ ዘግናኝ አጋጣሚዎች ስለሚያውቁ ነው፡፡ የኩፋውያንን ድጋፍ እንዲያቀናጅና የአካባቢውን ሁኔታ እንዲያጠናክር ሙስሊምን ቢን አቅልን መርጠው ከዚህ ደብዳቤ ጋር ላኩት፡፡

«በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡

ከሁሴይን ቢን አሊ

ለሙኢሚኖች መሪዎችና ሙስሊሞች

ሀኒና ሰዐድ ያመጡልኝ መልዕክቶቻችሁ ደርሶ ኛል የናንተን እያንዳንዱ ፍላጎታችሁን ተገንዝቤያለሁ፤ ሁላችሁም ዘንድ አንድ ዋና ሀሳብ አለ፡፡ «ሌላ ኢማም የለንምና ባንተ አመራር ስር አላህ አንድነታችንና ኃይልን ሊሰጠን ይችላልና ይምጡልን የሚል ነው፡፡ እኔም ከቤተሰቦቼ የሆነን ወንድሜን ሙስሊም ቢን አቅል ልኬላችኋለሁ ታማኝ ልኬላችኋለሁ፡፡ ታማኝ መልክተኛዬ ነውና ተቀበሉት፡፡ እርሱ ስለ እናንተ በሚጽፍልኝ ላይ ተመርኩዤ ልመጣ እችል ይሆናል፡፡ ኢንሻአላህ ፡፡ እንደ የሙስሊም መሪ (ኢማም) በአላህ ቁርአን የሚፈርድ ፍትሕ የሚጠብቅ ነውነተ ኛውን፣ ቀጥተኛውን ሐይማኖት የሚከተልና ሕይወቱን በአላህ መንገድ መስዋዕት የሚያደርግ ነውና፡፡»

ሁሰይን ታላቅ ትኩረት የሰጡት ለበስራ ሙስሊሞችም ነበር፡፡ የላኩላቸው ደብዳቤ በከፊል እንዲህ ይነበባል፡-

«በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ከፍጥረቶቹ መሀከል ነቢዩ መሐመድን (ዐ.ሰ.ወ) መርጦ በመለኮታዊ መልዕክት ላካቸው፡፡ እሳቸው ተልዕኮአቸውን ፈጽመው ካለፉ በኋላ ኡማውን የመምራት ኃላፊነት ከማንም በላይ የተጣለው በቤተሰቦቻቸውና በቅርብ ተከታዮቻቸው ላይ ነበር፡፡ ኡማው ግን አንድነቱን ጠብቆ ከመከፋፈል ለመዳንና በሠላም ለመኖር ባለውእምነት ና ፍላጎቱ በአንባገነኑና ጨቋኙ የኡመያድ ፖርት በኋይል ተገፍቶ የሕገ ወጦቹን ኡማያድ ገዢዎች ሥልጣን እንዲቀበል ተደረገ፡፡ ኡማውን የመምራትና ኢስላምን የመንከባከብ ኃላፊነት የኛ መሆኑን ጠንቅቀን እናውቃለን፡፡ በመልክተኛዬ እጅ የላኩላችሁ በዚሁ መልዕክቴ የአላህ ቁርአንና የነቢዩን ፈለግ እንድትተገብሩት ነው፡፡ የነቢዩ (ዐ.ሰ.ወ) ሱንና ወደ ጎን ተገፍቶ ፈሳድ (ሙስና) ተንሰራፍቷል፡፡ ቃሌን የምታከብሩና እኔንም የሚትከተሉ ከሆነ በቀጥተኛው መንገድ ልመራችሁ ዝግጁ ነኝ፡፡ ወሰላሙ አለይኩም ወራህመቱላሂ ወበረካቱሁ፡፡»

በዚህ የሁሴይን የተቃውሞ እንቅስቀሴ በስራ ደረሰ፡፡ በስ ራ በዘመኑ ከኩፋ ቀጥላ ታዋቂ ኢስላማዊ ከተማ ነበረች፡፡ የበስራ መሪዎችና ህዝቦች የኡማያድ አገዛዝን አይወዱትም፡፡ የሁሴይንን እንቅስቃሴ ለመመርመርና ውሳኔ ላይ ለመድረስ ማሪያ

በተባለች ቤት ሹራ ተቀመጡ:: ኢብን አሲር ሁኔታውን አል ካሚል ፊልታሪክ በተባለው መጣጥፋቸው ውስጥ ዘግበውታል :: «የተወሰኑ የሺአ ሰዎች ባስራ ውስጥ ማሪያ ቢንት ሰዓዳ በምትባል ከአብዱልቀይስ ነገድ በሆነች ሴት ቤት ተሰባሰቡ:: በሁዋላም የዚድ ቢን ባኒት የተባለ የአብዱልቀይስ ሰው በቆጥወደ ሁሴ ይን ወገን እንደሚቀላቀል ገልጦ ነበር:: በኋላም ይህው ሰው ከሁለት ወንዶች ልጆቹ (አብዱላህና አብዱላህ ጋር በመሆን ወደ መካ ተሰዷል:: በኋላም ወደ ካርበላ ከሁሴይን ጋር ዘምተው ሁሉም አንድ ላይ ሸሂድ ሊሆኑ በቅተዋል::

ያዚድ ቢን መስዑድ የተባለ የሙስሊሞች መሪ በኒ ተሚም፣ ቢኒ ሀንዘላህ ና ቢኒ ሰዐድ የተባሉትን ነገዶች ለኢማም ሁሴይን ድጋፍ እንዲደረግላቸው ሰፊ ዘመቻ አድርጓል:: ህዝቡ ሁሴይንን እንዳይክድ ካሳሰቡበት ንግግሮች በጥቂቱ:-

«. . . ያዚድ ኸምር ጠጪ ው፣ የጥፋት ልዑል፣ የኸሊፋነቱን ሥልጣን ከተገቢዎቹ ኢማሞች ነጥቆ ያለ ሙስሊሞች ፍላጎት ስሜቶቹ በሚመሩት መንገድ ሕዝቡንእየገዛ ነው:: ጨቋኝ የመሆኑ ያህል ድንቁርና ትክክለኛውን ነገር አይገነዘብም:: በእምነት ያዚድን መዋጋት ዲነል ኢስላምን ለማስፋፋት በሙሽሪኮች ላይ ከሚደረግ ጂሃድ የላቀ ይሆናል:: በሌላ በኩል ሁሴይን ቢን ዐሊ ለኢስላም ባዋሉት የረጅም ጊዜ አገልግሎቶችና ኢስላም በፈነጠቀበት ኢስላማዊ ቤተሰብ የነቢዩ ቤተሰብ በመውጣታቸው ኡማውን የመምራት ኃላፊነት ይገባቸዋል:: ይሁሴይን ለህጻናት ፣ ለደካሞቹ፣ ለአረጋውያን ሁሉ መጽናኛ ናቸው:: ይህንን አላህ በራህመቱ የለገሳችሁን ብርሃን አታዳፍኑት::

«ስኸር ቢን ቀይስ በአል ጀመል (የግመል ጦርነት) ወቅት የተከዳው በዚሁ ህዝብ ነበር:: ይህን ነውር አሁን የነቢዩ የልጅ ልጅ ሁሴይን በመረዳት አካካሱት:: እኔ በዚህ ዓላማ ቀዳሚ ነኝ:: በጂሃድ ሁሴይን ጎን አሰለፋለሁ:: በዚህ ጂሃድ የተሰዋ ሁሉ ታላቅ ሞትን ሞተ:: የሸሹትም ያው ከምድር ላይ ማለፍ አይቀርም:: ግን በውርደት አላህ ፊት ይቀርባሉ:: ምላሻችሁን እጠብቃለሁ:: የአላህ ራህመት በእናንተ ላይ ይሁን::

የሕዝቡ ምላሽ እንዲህ የሚል ነበር: - «ያ አቡ ኸሊድ» አሉት ባኒ ሀንዘላህ «እኛ የወስፈንጥር ቀስቶች ነን ዒላማህን ለመምታት ዝግጁ ነን በምት መራን ጦርነቶች ሁሉ በጎራዴዎቻችን እናግዝሃለን:: በአካሎቻችን እንከላከልልሃለን::» ሲሉት በኒ ሰዐድ ቢን ቢን ያዚድ ነገድ ደግሞ:-

«አቡ ኻሊድ ሆይ ! ለኛ አንተን አለመታዘዝ ከምንም በላይ ውርደት ነው:: ላቅር (ሳኸር) ቢን ቀይስ ጦርነቱጀንድናበቃ አዘዘን :: ይህንንም በማድረጋችን ሰላምንና ክብራችንን አስጠብቀን:: ጊዜ ስጠንና ሙሉ ውሳኔያችንን እናሳውቃለን» አሉት::

በኒ አሚር ቢን ቲሚም ነገድም እንዲህ ሲሉ ድጋፋቸውን ገለጡላቸው፡-
«አቡ ኻሊድ ሆይ ! እ ኛ በኑ አሚርነን የአባትህ ልጆችና ደጋፊዎችህ ነን፡፡ በኛም ንደት እንድትገባ አንሻም፡፡ ለጥሪህና ለትዕዛዞችህ ፈጣን ምላሽ ልንሰጥ ዝጅጉ ነን፡፡ ውሳኔው በእጅህ ነው፡፡» አሉት፡፡

ቢን መስዑድ (አቡኸሊድም) በመጨረሻ ለበኒ ሰዕድ እንዲህ ሲሉ ተናገ ሩ፡-
«ሁሴይንን በመርዳት (በማገዝ) ላይ ብታንገራግሩ፤ አልያም ብትክዷቸው አላህ ለዘለዓም ጎራዴያችሁን ከአንገታችሁ አያወርድም፡፡»

ቀጥሎም ለሁሴይን (ዐ.ሰ) እንዲህ ሲሉ ደብዳቤ ፃፉ፡-
«በአላህ ስምእጅግ በጣም ርህ ሩህ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡ የደብዳቤህን መልዕክት በጥልቀት መርምሬያለሁ፡፡ ወደ ምኝንደምትጠራኝና ወደምን እንደምትጋብዘኝ አውቃለሁ፡፡ አላህ ሁሌም ዓለምን የሚቀይርና ሰዎችን በቀጥተኛው መንገድ የሚመራ ሰው ይልካል አንተ የዚህ የአላህ ራህመት ምልክት ነህ፡፡ የነቢዩ መሐመድ (ዐ.ሰ.ወ) ቀጣይ ራህመት፡፡ የእርሳቸው ሥርወ ግንድ ሲሆኑ አንተ ቅርንጫፋቸው ነህ፡፡ በኒ ተሚምን እሳምኛሁ፡፡ በኑ ሰዑድንም ለማሳመን ችያለሁ፡፡ የበፊት ውርደታቸውንም በዚህ አጋጣሚ እንዲታጠብላቸው ተማምነናል፡፡»

ሁሴይንም ደብዳቤውን አንብበው እንዳበቁ «አላህ *የውመል ቂያማህ* (የትንሳኤ ቀን)፤ በዚያ የፍርሃት ቀን ሰላምና እርጋታ ያስፍንባችሁ፡፡ ክብሩን ይለግሳችሁ፡፡» አሉ፡፡

ያዚድ ቢን መስዑድ ሁሴይንን (ዐ.ሰ) ኃይል ለመቀላቀል ሲዘጋጁ ተገደሉ የሚል ዜና ደረሳቸው፡፡ ይሄ በውሸት የተሰራጨ ጭምጭምታ አሰራጨ የተባለውን ደብዳቤውን ይዞ የመጣው ሰው በአል ሙኒዚር ቢን አል-ጃሩድ ተይዞ ለፍርድ ወደ ኡበይዱላህ ቢን ዚያድ ተወደ፡፡ ኡበይዱላህ መልዕክተኛው እንዲሰቀል አዘዘ፡፡ የባ ስራ ህዝቡንም ለተሰራጨት ተባራሪ ወሬዎች ጆሮ እንዳይሰጥና ችግር ለመፍጠር ቢሞክሩ ታላቅ ቅጣት እንደሚጠብቃቸው አስጠነቀቃቸው፡፡ በሚቀጥለው ቀን ወንድሙን በበስራ ህዝብ ላይ በምክትልነት ሹሞ ለራሱ ወደ ኩፋ አመራ፡፡

በዚህ ሁኔታ የታቃውሞ መነኻሪያ ምትሆን ቦታ ተለየች፡፡ ኢማም ሁሴይን (ዐሰ) ሽዕባን፣ ረመዷን፣ ሸዋልና ዚልሂጃ፣ ወራትን ለዚሁ እንቅስቃሴያቸው ዕቅድ ሲያወጡና ተከታዮቻቸውን ሲያዘጋጁ ከረሙ/ሰነበቱ፡፡ ሕዝቡን ከዚሁ የኢራቅ ምድር ወደ ኢስላም ፍትሕ ሊመሩ አሰቡ፡፡ ኢስላማዊ መንግሥትውን ለመመስረት በኢ ራቅ ለመንደርደሪያነትና ለማዕከልነት ለመጠቀም ወሰኑ፡፡

# የጦር አዝማችና መሪነት

ሁሴይን ለመሐመድ አቂል የሰጡት መመሪያ ባጭሩ የሚከተለውን ይዘት የያዘ ነው፡፡

«መጥፎውን ነገር ሁሉንዲከላከል አዘዙት ፡፡ ተልእኮውን በሚስጥር እንዳይዝና ሥራውን በፀጥታ እንዲፈጽም በሕዝቡ መሃከል እውነተኛ ደጋፍና አንድነት መኖሩን ካረጋገጠ እንዲያስውቃቸ፡፡

ሙስሊም በረመዳን ወር 15 ቀን 60 ሂጅራ መካን ለቀው ወደ ኢራቅ አቀኑ፡፡ በተከተሉዋቸው ጥቂት የቅርብ ሰዎቻቸውና ሁለት መንገድ መሪዎች ብቻ ነበሩ፡፡ በጋ ስለነበር የሙቀቱ ንዳድ እጅግ ከፍተኛ ነበር፡፡ የበረሃውን መንገድ ረጅም በመሆኑም በጣም አስቸጋሪ ጉዞ ገጠማቸው፡፡ ከ20 ከባድ ቀናት በኋላ ሸዋል 5 ላይ ኩፋ ደረሱ፡፡ የተቀበሉት አል-ሙክታር ቢን አል ሰቃፊ የተባሉ የኩፋ ተዋቂ ሰውና የሁሴይን ደጋፊ ነበሩ፡፡ ሙስሊም አቂል ለሚካሄድው ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎቹ ይህንኑ ቤት ምሽግ አድርገ፡፡ የከተማይቱ ሙስለም ሕብረተሰብ ልባዊ አቀባበል ስለ አደረገለት ከብዙ ሰዎች ጋር እየተገናኘ መወያየት ጀመረ፡፡ የሁሴይንን ትክክለኛ ተልዕኮ ዓላማ ለመላው የከተማይቱ ነዋሪዎች በዝርዝር በማስረዳቱ ሕዘቡ በሁኔታው እ ጅግ ተመሰጠ፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥም 18000 የሚሆኑ ተከታዮችንና ደጋፍዎች አፈራ፡፡ ይህ ሃይል ማንኛ ውንም የጠላት ወገን ሊደመስስ የሚችል ብቃት ያለው ነበር፡፡ በመሆኑም ሙስሊም በኩፋ ያለውን ተጨባጭና ምቹ ሁኔታዎች ለማስረዳት በአፋጣኝ ወደ ኩፋ በማሳሰብ ደብዳቤ ላከላቸው፡፡

በኩፋ የተወጠነው እንቅስቃሴ ኃይል እያገ ኘ መጣ፡፡ የነዋሪዎች እስላማዊ ስሜት ከእለት እለት እየጠነከረ ሄዶ መልኩን በመቀየር ታላቅ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ፈጠረ፡፡ ይህ ለውጥ አዘልእንቅስቃሴ ለኡማያድ ዙፋን የመነቅነቅ ጉልበት እያገኘ በመምጣቱ በያዚድ አገዛዝ ላይ ታላቅ ስጋት ተደቀነ፡፡

በኩፋ መታየት የጀመ ሩ ፖለቲካዊ ክስተቶች የያዚድንና የኩፋ ሹማቸውን አል ኑዕማን ቢን በሺር እጅጉ አሳሰበ፡፡ አል -ኡዕማን የተፈጠረውን ፖለቲካዊ ውጥረት በሰላማዊ መንገድ ለማርገብ ቢሞክርም ገንፍሎ የመጣውን የህዝብ ስሜት ሊቆጣጠር አዳገተው፡፡

በሌላ በኩል የአል ኑማን የገዢዎቹ መመሪያዎች ከሰፊው የሙስሊሙ ህብረተሰብ ፍላጎት ጋር ሊጣጣሙ አልቻሉም፡፡ የገዢዎች ፍራች የተፈጠረው ፖለቲካዊ ውጥረት ወደ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ተቀይሮ የተደላደሉትን ጥቅም ያሳጣናል የሚል ነው፡፡ በወቅታዊ ክስከቶች በነዚህ ቦታዎች ሁሉ ከሁሉም በላይ ያሳሰበው አብዱላህ ቢን

ሙስሊም የተባለ የያዚድ ሚስጥረኛ ደብዳቤ በመላክ ያዚድ አል ኑዕማንን እንዲሽርና በሐይል ጨፍልቆ ሊገዛ የሚችል ሰውእንዲሾም አሳሰ በው፡፡ ለዚህ የሰጠው ምክንያት በሀገሩ የተፈጠረው የለውጥ እንቅስቃሴ በአል ኑእማን አላማ አመራር ስር መፍትሔ ሊያገኝ አይችልም የሚል ነው፡፡ ከ አል ራማን ሌሎች ሰዎችም ለያዚድ ተመሳሳይ ደብዳቤ ጽፏል፡፡ ከነዙህ ሰዎች ሁለቱ አማራህ ቢን አቀባና ዑመር ቢን ሰዐድ ቢን አቢ ወቃስ ይገኙቡታል፡፡ ከነዚህ ሁለት ሰዎች የተላከው ደብዳቤ በከፊልእንዲህ የሚል ነው፡

«ሙስሊም ቢን አቂል ወደ ኩፋ ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ ለሁሴይን ቢን ዐሊ ቢን አቢ ጧሊብ ድጋፍ በማሰባሰብ ድርጊት ላይ ተሰማርቷል፡፡ በመሆኑም ለኩፋ የምትብላት ከሆነ በአፋጣኝ ጠንካራ መሪ መላክ ያሻል፡፡ ትእዛዞችህን በአግባቡ የሚፈፀምና ጠላቶችህ በአንተ አካኋን የሚቀጣው ሰው ለኩፋእጅግ ያስፈልጋታል ፤ አል ኑዕስማን በበኩሉ በድክመቱ ከፀና ቆይቷል፡፡»

ኩፋ የሁለት ወገኖች የትግል መድረክ ሆነች፡፡ የኡማያድ ጭፍኖች በሁሴይንን ተፋላሚዎች ተፋጠጡ፡፡ ፍጥጫው ሊፈነዳ ተቃረበ፡፡ የያዚድ ስልጣን ተነቅሎ ሊጣል ተቃረበ፡፡ ከኩፋ የሚመጡት ዜናዎች የራሳቸውን መልክና ዓላማ ይዘው ወደ ሁሴይንና ወደ ያዚድ ይጎርፋሉ፡፡ ለያዚድ የሚደርሱት ወሬዎች የአል ኑስማን ማስተዳደር አለመቻሉና ለሌላ ጨካኝ መሪ መሾም የሚጣሩ ናቸው፡፡

ያዚድ በመጨረሻ ውሳኔ ላይ ደረሰ፡፡ ለኩፋ ምህረት የለሽ ገዢ እንደሚያስፈልጋት አመነ፡፡ ይህ ሰው ለስልጣንና ለዝፉላቅ ቦታ የሚሰጥና ለጥቅማ ጥቅሞቹ ሲል አስፈላጊውን እርምጃዎች የሚወስድ መሆን አለበት፡፡ እነዚህን መመዘ ኛዎች የሚያሟላለት ሰው በወቅቱ የበስራ አስተዳዳሪ የነበረው ዑበይዳላህ ቢን ዚያድ ብቻ ነው፡፡

በተለይ ሰርጃን የተባለው አገልጋዩ ተግባራዊም ባይሆንም በፊት በሙአዊያ ዘመን ዑበይዳላህ ለኩፋ አስተዳደርነት ተሹሞ እንደነበር ከነገረው በኋ ላ በሀሳቡ ፀና፡፡ የዑባይዱላህ ከመጠን በላይ ለኡማያድ አጎብዳጅ የመሆቍውፁኄ ውሳኔውን አጠናክሮታል፡፡ ያዚድ ወዲያው እቅዱን ተግባራዊ አደረገው፡፡

ዑባይዱአላህ ወደ ኩፋ እንዲዛወርና የህዝቡን ትግል ለማክሰም ማናቸውንም ዓይነት ጉልበት እንዲጠቀም አዘዘው፡፡ የተፈለገውን በኩፋውያን ላይ የሚደር ሰውን እልቂት ሳይሆን ስልጣኑ አለመታጣቱ ላይ ነው፡፡ ያዚድ ለዑባይዱአላህ የፃፈው ደብዳቤ እንዲህ ይነበባል፡፡

«በኩፋ የሚገኙት ተከታዮቼ እንደነገ ሩኝ መሐመድ አቂል የሚባል ሰው በሙስሊሞች መሀከል ክፍፍል በማምጣቱ ህዝቡን በመቀስቀስ ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ደብዳቤ እንደደረሰህ

ወደ ኩፋህ ተጉዘህ ይህን አቂልን እንድታገኘውና እንድትገድለው ወይም ከከተማይቱ እንድታባርረው ታዘሃል:: «ወሣላም::»

## የደበዘዘው ተስፋ

ዑባይአላህ ቢን ያዚድ የያዚድን ትዛዝ እንደደረሰው በሚቀጥለው ቀን ወደ ኩፋ ተጓዘ:: ኩፋውያን በጉጉት የሚጠባበቁት ሁሴይንን ነበር:: ይሁንጂ አብዛኛው የኩፋ ነዋሪ ሁሴይንን በዓይን አይተው አያውቁም:: ቢን ዚያድ ይህንን አጋጣሚ ለመጠቀም ፈለገ:: ስለዚህ ጭንቅላቱ ላይ በጠመጠመው ጥቁር ጨርቅና ፊቱን በግማሽ በመሸፈን ኩፋ ገባ:: ህዝቡም አዲሱ እንግዳ ሁሴይንን ስለመሰለው በጋለ ስሜት ተቀብለው:: በከተማይቱ መንገዶች መዘዋወር ሲጀምርም ነዋሪው እንኳ ን ደህና መጣችሁ ነቢዩ ልጅ!»እያለ ይጮህ ነበር::

ከነዋሪዎቹ በሰማቸው ቃላት የተናደደው ዚያድ በቀጥ ያመራው ውዳ ኩፋ ቤተመንግስት ነበር:: አንድ ሁኔታ ግን ተረድቷል:: ህዝቡ ለሁሴ ይን ያለው ፍቅርና ለያዚድ አገዛዝ ላይ ያለው ጥላቻ:: ኩውያን በድንጋጤ የተዋጡት ሙስሊም ቢን አምሩ አል ባህሊ የተባለው አጃቢ ዚያድን ማንነት ይፋ በማድረግ ነው::

«የኩፋ ህዝብ ሆይ ይህ ገዢያችሁ ዑበይዱአላህ ቢን ዚያድ ነው::»እያለ መለ ፍፍ ሲጀምር ነው::

ዚያድ በተደነጋገረ የዋህ ህዝብእየታጀበ ወደ አል -ኑእማን ቤት አመራ:: ግማሽ ነዋሪ አሁንም ዚያድንእንደ ሁሴይን ለ መውሰድ ይከታተሉታል:: አል ኑማን በበኩሉ በቤተ መንግስት ውስጥ ስጋት ገብቶታል:: ዚያድ ወደ ቤቱ እየቀረበ ሲመጣ አልኑእማን እንዲህ እያሉ መጣራት ጀመሩ:: «አላህን የምትፈራ ከሆነ ተከልከል፣ስልጣኔንም ላስረክብህ አልፈልግም ልዋጋህም አልሻም::» ለአል ኑዕስማን እንግዳው ሰው ሁሴይን መስሎች ኖሯል::

ኢብን ዚያድ ቃል አልተነፈሰም:: ወደ ቤተመንግስቱ ደጃፍ ሲደርስ አልኑእማን ስላወቀው ሰተት ብሎ ገባ:: ሴሊቱም ያው አሳለፈ:: ኩፋ ያልተጠበቀ ስጋት ተደቀነበት::

በሚቀጥለውም ቀን ህዝቡ በቤተ መንግስቱ እንዲሰባሰብ ኢብን ዚያድ አዘዘ:: በማይመጡት ላይ ቅጣት ለጅሙዓ ሶላትንደማ ፈፀም በማስፈራራት እነዚህ የማይታዘዙ የርሱን ሹመት የሚቃወሙ ነዋሪዎች ላይ በግርፋትና በጎራዴ እንደሚቀጡ አስጠነቀቁ::» የተቃዋሚ ቡድኖች መሪዎች እ ንዲለዩለት በከተማይቷ ስላዮችን አሰማረ:: ትእዛዞቹንና ሹመቱን በሚቃወሙ ነዋሪዎች ከቤይቱል ማል የሚሰጣቸው ማንኛውም ዓይነት እርዳታ እንደሚቋረጥ አስፈራራ:: ማስጠንቀቂያው እንዲህ የሚል ነበር::

«ተቃዋሚዎችን ያጋለጠ ከሚወሰዱት እርምጃዎች የተጠበቀ ይሆናል:: (ይድናል:: በዚህ ረገድ የማይተባበረን ሰው ደሙ ሊፈስ፣ቤተሰቡና ንብረቱን ሊነጠቅ ይችላል:: ከቤተሰቦቹ ወይም ከወገኖቹ ሁሴይንን ሲደግፍ የተገኘ ሰው በስቅላት ይቀጣል::»

ኩፋውያን ያልጠበቁት ነገር ስለተከሰተባቸው የተስፋ መቁረጥ ስሜት ተሰማቸው:: በእለታዊ ህይወታቸው ፍራቻና ስጋት ነገሰ:: ነዋሪው ህዝብና መሪዎቻቸው በተፈጠረው ሁኔታ የተሰፋ መቁረጥ ስሜት ተሰማቸው:: ዑበዱላህ ቢን ዚያድ በሽብር፣በጉቦ፣ስልጣን፣ህዝቡን እርስ በርሱ በማከፋፈልና በስለቶችእየተደገፈ ስልጣኑ አበጃጀ:: ይህ ዘዴ የኡማያድ ገዢዎች ሁሉ የወል ባህሪይ ነው::

ያልተጠበቀው ሲከሰት ያልታሰበው እንቅስቃሴ መሪ የነበሩት በኩፋ የሁሴይን ሰው መሐመድ ቢን አቂል ከሁሉም በላይ የሚገባበት ጠፋው:: ኢብን ዚያድ ከተማይቷ እንደገባ ኢብን አቂል የወሰደው ቀዳሚ እርምጃ አድራሻውን መቀየር ነበር:: ከነበረበት የአል ሙኽታር ቢን ሁበይዳ አል ሰቃፊ ቤት ወደ ሃኒ ቢን ሁርዋ ቤተሰብ ተጠቃለለ:: ኢብን ዑርዋ በከተማይቷ ታዋቂ ሰውና የነብዩ ቤተሰብ ታላቅ ወዳጅ ናቸው:: ከዚያድ አነፍናፊ ሰላዮች ግን አላመለጠም:: ኢብን ወርዋ በያዚድ እንደሚጠራ ተነግሮአቸው ወደ ቤተመንግስቱ እንደደረሱ::

ሁሴይን በመደገፍ ወንጀል ተከሶ ታሰ ሩ:: በእስር ቤት ያዚድ ራሱ ደብድቧቸዋል:: ሚስሃጅ የተባለው የሃኒ ነገድ ሰዎች ሊያስለቅቁት ቢሄዱም ኢብን ዚያድ በመልካም ቃል ስለተናገራቸው ተመልሰው ሄዱ::

ኩፋ የጦርነት ቀጠና ሆናለች:: በሁለቱ ወገኖች መሀከል የሚደረገው ፍጥጫ ወደ ውጊያ እየተቀየረ ነው:: ሙስሊም ቢን አቂል ለጊዜው ተደብቀው ቢቆዩም ተዋጊዎቻቸውን እያደራጁ ነበር:: በመጨረሻም ሁበይ ዱላህ ቢን ዚያድን ለማጥቃትና ከስልጣኑ ለማባረር ወሰኑ:ታማኝ ደጋፊዎቻቸውን አስከትለው ወደ ቤተመንግስቱ አቀኑ:: ሲደርሱ የተከተላቸው ብዙ (4000) የሚሆኑታጣቂዎች ነበ ሩ ኢብን ዚያድ ሊገጥሙዋቸው አልደፈሩም:: በተቃራኒው ቤቶቻቸውን ቆልፈው የስውር ደባቸውን ቀጠሉ:: ግር ብሎ ከወጣው ህዝብ መሀከል የተለያዩ ሰላዮችን በመሰግሰግና አፍራሽ ፕሮፓጋንዳ በመንዛት እንዲሁም የህዝብን ጥያቄ እንደሚቀበሉት ቃል በመግባት በቀስታ አንድነታቸውን አፈረሱት:: በነዋሪው ዘንድ በስፋትእንዲረጭ ካደረጉት ወሬ አንዱ ታላቅ ወታደራዊ ኃይል ከሶሪያ ተነስቶ መንገድ እንደገባና ኩፋ ሲደርስ ተቃዋሚዎችንና ደጋፊዎቻቸውን ሁሉ እንደሚፈጅ የሚል ነው:: ነዋሪው ደማቸውን በከንቱ እንዳይፈስም ለማጋባባት ጣሩ:: በዚህም ቡዙ ህዝብ ኢብን አቂል እየተወ ወደ የቤታቸው ተመለሱ:: በእሻ ሰላት አቂልን ተከትለው የሰገዱ ደጋፍዎቻቸው 10 ሲሆኑ ሰላቱን ሲያበቁ እነርሱም ጥለዋቸው ሄደዋል:: ብቻቸውን በኩፋ መስጅድ ቀሩ:: በከተማይቷ መንገድ የሚመራቸውም ሆነ የሚያሳድራቸው ሰው አጡ:: የትእንደሚሄዱ ማንም ለእርዳታ እንደሚጠይቁ ጠፋቸው::

በዚህች አስቸጋሪ ቅጽበት መቋቋም ነበረባቸው:: የሁሴይን ተወካይ ናቸውና:: በአቋማቸው ፀንተው ተ[illegible]አቸውንም መ ወጣት የግድ ሆነባቸው:: ኢብን አቂል ከመስጀዱ ለቀው ወደ ከተማይቷ ጎዳና ወጡ:: አንድ መፍትሔ መዘየድ አለባቸው::

በያዚድ ሰዎች ሳይያዙ በፊት ሰለ ኩፋ ቃሁ'ክሁሴ ይን አስረድተው ወደ ሀገሩ እንዳይመጡ ሊመክሩዋቸው ተመኙ::

የከተማይቷ መንገዶች ፀጥ ረጭ ብለዋል ሽብር ሰፍኖባቸዋል:: ሰላዮች ሁሴይንን ለመያዝ አካባቢውን እያሰሱት ነው:: ኢብን አቂል የመጨረሻ አንዲት ሴት አየ:: (አገኘ) አሮጊት ናቸው:: ጠዋህ ይባላሉ:: ውሃ እንዲያጠጡት ጠየቃቸው:: ሁኔታውንም አይተው አዘኑለት:: መሐመድ አቂል የሁሴይን አምባሳደር መሆኑን አስረዳቸው:: በቤታቸውም ለሊቱን እንዲያሳልፍ ፈቀዱለት::

ኢብን ዚድ በኢብን አቂል ላይ የደረሰውን ሽንፈት ሰምተዋል:: የመጨረሻ በትራቸውን በተቃዋሚዎቻቸው ላይ ለማሳረፍ ተሰናዳ::

«ሙአዚኑን አስጠርተው የዒሻን (ምሽት) ሰላት ላይ ለማይገኝ ሰውና ሌላ ፁ ለሚሰግድ ነዋሪ የህይወትም ሆነ የንብረት ዋስትና እንደማይኖረው እንዲለፍፍ አደረገ::

ኢብን ዚያድ ካሰገደ በኋላ መስጀዱን ሳጨናነቀው ህዝብ እንዲህ ሲል ተናገረ:: «ኢብን አቂል የተቃውሞ እንቅስቃ ሴ ከሽፏል:: እርሱን ያስጠጋ ሰው ከኛ ምህረት አይኖረውም:: ድጋፋችሁንም ለአስተዳደራችን እንድታደርጉ ይሁን::» የጥበቃ ኃላፊውንም አሰጠነቀቀ::

«ሁሴይን ቢን ኑማይር የኩፋ መውጫ ሁሉ ዘግተው ይደሩ:: አቂል ቢያመልጥ እናትህ ታጣሃለች:: የነዋሪዎች ቤትእንዲፈተሽ ስልጣን ሰጥቸሃለሁ:: ነዋሪ ውም በጥቆማውን እንዲተባበር ሲል አዘዘ::»

የኩፋ ቤቶች በለሊት ታመሱ ሙስሊም አቂል በነዚህ በአንዱ ተደብቋል:: በሴት ሙዳሂዷ ጠዋህ ቤት ከከተማይቷ ተደብቆ የሚያመልጥበትን አጋጣሚ ተጠባበቀ ነው:: አልያም በዚህ መሀከል ረጂ እጅ ያገኝና አካባቢውን ለቆ ይወጣል::

በዚህ መሀከል ያሰበው ሁሉ ያሚያደፈርስ ነገር ተከሰተ:: በዚያድ የሽልማት ቃላት የማርከው የአሳዳሪው ጠዋህ ልጅ ተደብቆ ሌሊቱን ወደ ዚያድ በመሄድ አቂል የተደበቀበትን ቤታቸውን ይጠቁማቸዋል:: ቤቱ በ70 ወታደሮች ተከበበ:: አቂል የፈረስ ኮቴውን እንደሰማ ፈጣን ውሳኔ ላይ ደረሰ:: ለመሸሽ አልፈለገም:: ብቻውን ጥቃት ሰነዘረባቸው:: ከቤቱም የተወሰነ ርቀት አሳደዳቸው:: ፊት ለፊት ሊዋጋው የደፈረ የለም:: በኋላ ሌላ መላ ዘየዱበት:: በቤቱ ላይ እሳት መወርወር ጀመ ሩ:: ሁኔታው ከቤቱ ገፍቶ አወጣው:: በሜዳው ላይ ብቻውን ሊገጥማቸው ተገደደ:: ፊቱን ሰውነቱን በደም እስኪሸፈን ተ ዋጋቸው:: ክፉኛም ቆሰለ:: በበቅሎ አድርገው ወደ ዚያድ ዘንድ ተወሰደ:: ለዚያድ ያለው ንቀት ከፊቱ ይነበበብ ነበር:: ዚያድ «ልትገደል ነው» እንዳለው ኑዛዜ እንዲነገር ተፈቀደለት: : ሶስት አንኳር ነጥቦችን ኢቢን ሰዐዲ የተባለ ሰው እንዲጽፍለት አደረገ:: ኢብን ዚያድ መሐመድ አቂል በህይወት እንዲሰነብት አይፈልግም:: የተቃውሞ እንቅስቃሴው የጀርባ አጥንት አቂል ስለሆነ አሁን ባገ ኘው አጋጣሚ ተጠቅሞ ሊበቀለው አሰበ:: ወዲያውም በክር ቢን ሀምራን ለተባለና በአቂል

ሰይፍ እጅግ የቆሰለውን ወታደር ጭንቅላቱን  እንዲቆርጠውና ሰውነቱን ከሰገነት እንድወረውር አዘዘ። ሙስሊም «አላሁ አክበር» «አላህ ታላቅ ነው!» እያለ በግፍ ተገደለ። የምርጥ ሙስሊሞች አሟሟት በማግኘት ለሸሂድነት በቃ።ከሹሃዳዎች፣ከነቢያትና፣ ከደጋግ የአላህ  ባሮችን ተቀላቀለ።

ቀደም ብሎ ኢብን አቂልን ያስጠጋው ሀኒ ቢን ሁርዋህ የተባለ ሰውም ሱቅ አልጋናም (የበጎች ገበያ) ወደ ተባለ ቦታ ተወስዶ ተመሳሳ  ሁኔታ በአስቃቂ ሁኔታ ተገደለ። የሁለቱ ሸሂዶች የተቆረጡ ራሶች ለያዚድ ኢብን ሙአዊያ ተላኩ። የተቀረው አካላቸው ለኩፋ ጎዳናዎችና ገበያዎች ላይ በነሙድ ተጎተቱ። የመጀመሪያው ዙር የተቃውሞ እንቅስቃሴ በዚህ ተደመደመ። የነዚህ ጥቂት ውድ ህይወታቸውን ለኡማው በለገሱ ሹሃዶች ደም ላይ ያቆጠቆጠው ኢስላማዊ የፍትሕ አብዮት በጮሪክ ም ዕራፍ እየገነፈለ ጨቋኞችንና  ስርዓታቸውን ያንቀጠቅጣል።

## ከርባስ

ሙስሊም ለኩፋ ቆይታው የሁሴይንን ኢስላማዊ ንቅናቄ መንሲዒዎች፣አላማና ግብ ለህዝቡ እያስረዳ ድጋፍ ስያ ሰባስብ ነበር:: በዚሁ ጥረቱም በተለይ በሀገሩ የታወቁ ግለሰቦችን ድጋፍ አግኝቷል:: ነዋሪው በኢማም ሁሴይን (ዐ.ስ) ያለውን ውዴታ መግለጽ ጀምሯል:: በመጨረሻም ሙስሊም በኩፋ ያለውን ወቅታዊ ሁኔታዎች ለኢማም ሁሴይን ሲጽፍላቸው ከርሞ ህወቱንም አብሮ ሰጠ:: ሙስሊም ሳይገደል በፊት ኢማም ሁሴይን ወደ ኩፋ ቢመጡ አመቺ ጊዜ እንደሆነ የሚገልጽ መልእክት ልኮላቸው ነበር::

ሁሴይን ቢን አሊ (ዐ.ስ) መልዕክቱ እንደደረሳቸው በመጨረሻው ጉዞ ተሰናዱ:: ልጆቻቸውን፣ሚስቶቻቸውን፣ወንድሞቻቸውን፣በአጠቃላይ የቅርብ ዘመዶቻቸውንና ታማኝ ምእመናን ተከታዮቻቸውን ለጉዞው አዘጋጁዋቸው:: የመካ ነዋሪ ይህን ሲሰማ ደነገጠ:: ሃሳባቸውንም እንዲቀይሩ መከሩዋቸው:: የህዝቡ ፍራቻ በወጡበት እንዳይቀሩባቸው ነው:: በመካ ቆይታቸው በሳቸው መንፈሳዊ አመራር ስር ፍትሐዊ ህይወት ስለኖሩ ለሁሴይን ታላቅ ከበሬታና ፍቅር አዳብረዋል:: እንዲለዮዋቸው በፍጹም አልፈለጉም::

ሁሴይን በበኩላቸው ከያዚድ ጋር መደራደርም ሆነ ያወጁትን ጂሃድ ማቆም አይችሉም:: ምናልባት ለህዝቡ ያልታየና እሳቸው አጉልተው የተመለከቱት ጉዳይ አለ:: ይሄም ዲነል ኢስላም ነቢዮ በሄዱበት ጥቂት አስርት ዓመታት ውስጥ ታላቅ አደጋ ሲደቀንበት፣ለሙስሊሞችና ለዓለም ህዝቦች በሙሉ የፈነጠቀው የኢስላም ብርሃን ፍትህ በጨቋኝና ራስ ወዳድ መሪዎች አገዛዝ ሲደበዝዝ በምን ትዕግስት ተቀምጠው ያዩታል? እንዴትስ ያስችላቸዋል? አላህ ፊትስ ምን ይዘው ሊቀርቡ ነው? እሳቸው ከያዚድ ጋር ስምምነት ቢፈጥሩ ሙስሊሙ ኡማ የኡማያዶችን አገዛዝ እንደ ኢስላማዊና ህጋዊ ስለሚወሰዱት ጃሂሊያ በቀላሉ ይመሀልላል:: ተቃዋሚ እንቅስቃሴም የሚነሳበት ምክንያት አይኖርም ነበር:: የሁሴይን ኢስላማዊ እንቅስቃሴ በዚህ መልኩ ከታየ ከያዚድ ወይ ኡማያዶች አገዛዝ ጋር የተደረገ ትግል ብቻ ሳይሆን የሁሉም አምባገነን መሪዎችና ስርዓቶች ላይ ያነጣጠረ ዘላለማዊ የኢስላማዊ ፍትህ እንቅስቃሴ ነው:: ለዚህ ነበር የነበረው ኡማ ዘንድ ሁሴይን የአንድ አገዛዝ ትክክለኛነት መለኪያ ተምሳሌት ሆነው ያገለገሉት::

ሁሴይን በውሳኔያቸው ፀኑ ጉዞአቸውእንዲሰርዙ ግፊት ከአደረጉባቸው ሰዎች ውስጥ ወንድማቸው መሐመድ ቢን አልሐነፊያ፣ ዑመር ቢን አብዱል ራህማን ቢን አል ሐሪስ ቢን ሒሻም፣ ወንድማቸው አብዱላህ ቢን ጃእፋር፣ የአጎታቸው ልጅ አብደላህ ቢን ዐባስ ይገኙበታል:: በመካ የያዚድ ተወካይ አምሩ ቢን ሰእድ ቢን አቡ ዓስ ሳይቀር በመካ ቢቆዩለት ደህንነታቸው ዋስትና እንደሚሰጣቸው ሊያግባባቸው ሞክሮ አልተሳካለትም::

ሁሴይን ለነዚህ የመካ ነዋሪዎች የሰጡት ምላሽ በህልማቸው ነቢዮን(ሰ.ዐ.ወ) እንደታያቸውና አንድ ወሳኝ ተግባር እንዲፈፅሙ እንዳዘዛቸው ይህንንም እሳቸው ብቻ ሊወጡት የሚችሉ ገድል መሆኑን እንደነገሩዋቸው ገለጡ፡፡

በኩፋውያን እንዲሚከዱ ሁሴይን ጠንቅቀው ያውቁታል፡፡ ኢስላማዊ ተልእኮአቸውን ከዳር ማድረስ ነበረባቸው፡፡ ብቻቸውን ቢቀሩ እንኳን ከአቅማቸው ንቅንቅ ማለት አይችሉም፡፡ የኡማያድ አገዛዝ ኡማው ላይ የሚያደርሰው ጭቆና ለማስቆም የሚችሉትን ከማድረግ ወደ ኋላ ለማለት አልፈለጉም፡፡ ስለዚህ ዙልሂጃ ወር 8ኛው ቀን 60 ዓመቱ ሂጅራ ወደ ዒራቅ ተንቀሳቃሱ፡፡ በየመንገዱ ለሚመክራቸው ሰው ሁሉ አንድ ምላሽ ነበራቸው፡፡

«እንደሚገድሉኝ አውቃለሁ፡፡ ይህን ሊሰሩ ግን አላህ ያዋርዳቸዋል፡፡ የሚያዋርዳቸውን ሌላ ሐይል ያመጣባቸዋል አባቴ በነገሩኝ መሠረት-መካ ውስጥ ቆይቼ ውርደት አልጠብቅም የኡማውን ሽንፈት በዓይኔ አላይም፡፡ በደ፝፞ምነዳ ቸዋለሁ፡፡ በመካ ላይ ከመገደልእዚያው ሩቅ ሀገር ባሉበት ሄጅእጋፊ ጣቸዋለሁ፡፡ ይሉ ነበር፡፡ ያጠሩ፡፡

ሁሉ ነገር ግልጽ ሆኖላቸዋል፡፡ የሚሰሩትን ጠንቅቀው ተረድተዋል፡፡ የተሰጣቸውን ታላቅ ተልዕኮ የሚፈጽሙት በሽሂድነት ሊወድቁ ብቻ መሆኑን ተርድተዋል፡፡ የሚከተለው ኢስላማዊእንቅስቃሴም ጊዜውን ጠብቆ የሚፈነዳ ታሪካዊ ክስተት እንደሚሆን አምነውበታል፡፡

በሌላ በኩል የሁሴይንን ውሳኔ የሚቃወሙ ሰዎች ሁለት ምክንያዎች ያቀርባሉ፡፡ የመጀመሪያው ሙስሊሙ ኡማ ህጋዊውን አማራር ያጣል፡፡ የኡማያድ አገዛዝ በዚህ አጋጣሚ ተጠቅሞ ህዝቡን ወደ ባሰ ብዝበዛ ያሸጋግራል የሚል ነው፡፡ ይህ ስቓቸው በአብደላህ ቢን ሙጢዕ አንደበት ተገልጾአል፡፡ « እርስዎ ቢገደሉ እ ኛ ለኡማያድ ባርነት እንጋለጣለን፡፡»

ሌላው ያቀረቡት ምክንያት ድልን የተደረጉበት ግንዛቤያቸውን ይመለከ፡፡ ለነርሱ ድል ወይም ማሸነፍ ማለት የጠላትን ኃይል ከረቱ በኋላ ስልጣን መያዝ ነው፡፡ ለኢማም ሁሴይን (ዐሰ) ግን ሌላ ትርጓሜ ነበረው፡፡ ኢስላማዊ ድል በጦር ሜዳ ማሸነፍ ብቻ አይደለም፡፡ አስፈላጊውን መስዋዕትነት ከፍሎ ኡማው ቀጥተኛውን መንገድ እንዳይስት የደም ብርሃን መፍጠር ነው፡፡ በሽሂዶች ደም መሰረት የተጣለ ኢስላማዊ ትግል ቢታሪክ ሄደት ውስጥ የትኛውንም ኃይል ገኸ ወይንም ስርዓት የመፈረካከስና በሚያሰችለው ዘልአለማዊ ኃይል የተሞላ ይሆናል፡፡

ህዝቡ የፈለገውን ሁሰሴይንን ከአጠገባቸው አለማጣትን ሲሆን እሳቸው በሹሃዳነት አልፈው የኡማውን የታሪክ ሂደት በኢስላማዊ ጎዳና መቀየስ ነበር፡፡ ባላቸው ውታደራዊ አቅም የተነሳ ቋይል መ ንገድ አማራጫቸው መሆንእንደለ ؍ለበት የአብዛኛው ሰው እምነት ነበር፡፡ የሁሴይን እቅድ ግን ቢያንስ ጨቋኝ መሪዎችን በጊዜ ርዝመት ውስጥ ከየቦታቸው መፈነቃቀል የሚያስችል ደም ለኡማው መለገስ መቻላቸው ነው፡፡ ደማቸውን የሚመጠው የበረሃ አሸዋ ቀደራቸው ነው፡፡ ነገ ጃሃ ؍ሊያን ባለበት የሚያንቀጠቅጥ ሙጃሂዲን ያበቅላል፡፡

ሁሴይን በ8ኛው ዙል ሂጃ ቀንታሪካዊውን ጉዞ ጀመ ሩ፡፡ ብዙም ሳይርቁ የገጠማቸው የሂጃዙ አስተዳዳሪ አምሩ ቢን ጰድ ቢን አል አስ ከትግላቸው ሊያስቆሙዋቸው ሊወጉዋቸው አሰቡ፡፡ መለስተኛ ሰራዊት አስከትለው ገጠሙዋቸው፡፡ የሁሴይን ወገን በጀግንንት ፣ሰለ ተዋጓቸው የአል ዓስ ቅጥረኞች ተሸንፈው አፈገፈጉ፡፡

አል-ተንዒም የሚባል ቦታ ሲደርሱ የያዚድ ቢን ሙአዊያ የሚሆን ስጦታ ጭነው ከየመን የሚመጡ ግመሎች አገኙ፡፡ ስጦታዎቹን በምርኮ ወስደው መንገዳቸውን ቀጠሉ፡፡ ሁሴይን ያዚድ ላይ ኢስላማዊ ጅሃድ በማወጃቸው በዚህ ረገድ ሸርዓው የሚፈቅደውን መስራት ይችላሉ፡፡

አል-ስፋህ ላይ ተዋቂውን ገጣሚ አል ፋረዝዳቅ አገኙ፡፡ የኩፋ ህዝብ ስለእሳቸው ያለውን አመለካከት ጠየቁዋቸው፡፡ አልፋረዝዳቅ « ኩፋውያን ልቦቻቸው ከእርስ ጋር ነው፡፡ ጎራዴዎቻቸው ግን አይደሉም» አላቸው፡፡ ሁሴይን በሁኔታው ተገርመው እንዲህ አሉ፡- «የውነት ቃል ተናግረዋል ምስጋና ሁሌም ለአላህ አዎእሱ ከላይ በሚልካቸው ፈተናዎች መደሰት አለብን፡፡ ፈተናዎችም ተስፋችንን ቢያደበዝዙም *በሷሊሆች* ልብ ውስጥ ሊገሉት አይችሉም፡፡እነዚያ አ ላማቸው እውነት የሆኑ ጥቂት ሰዎች ከምንም በፊት ተስፋ አይቆርጡም፡፡ እንዲያውም ጥንካሬን ይጨምርላቸዋል፡፡ »

በሁሴይን እንቅስቃሴ ፍርሃት የገባባ ቸው ሌሎች ወገኖችም አበሩ፡፡ እነዚህም ለሁሴይን ህይወት ወይም ለኡማው ውድቀት አስበው አይደለም፡፡ የትርምሱ ፣የፍርሃታቸው ምንጭ ሁሴይን የኡማያድን ዙፋን ገልብጠው ወደ ስልጣን ቢመጡ የሚያጡትን ጥቅማጥቅሞች አስበው፤ የነርሱ ህልውና በኡማያድ መውደቅ ጋር እንደሚረግፍ ያውቃሉ፡፡

የሂጃዝና የዒራቅ ህዝብ በተቃውሞእንቅስቃሴዎች ተናወጠ፡፡ በሁሴ ይን ወገን በየመንገዱ የሚቀላቀሉዋቸው ተከታዮቻቸው እየበረከተ ሄዱ፡፡ ዑበይዱላህ ቢን ዚያድም የበኩሉን ደባ ማሴር ጀመር፡፡ የወታደሮቹን አለቃ ሆሲን ቢን ዑመይር በሁሴይን ላይ ድንገተኛ አደጋ ጥለው ግስጋሴያቸውን እንዲያቆም አዘዘው፡፡ ኢብን ኡ መር የታዘዘውን

ለመፈፀም ቀደሲያ ላይ ቀደም ብሎ መሻገ::ወታደሮቹን ከቀዲሲያ ና እስከ ሽፋን ከቀትቀታና እስከ ባእላዕ ተራራዎች ያለውን ቦታ ላይ አሰፈረ::

ሁሴይንና ተከታዮቻቸው ሌሊቱን ዘባላህ ላይ አሳለፈ:: በማግስቱ ጎህ ሲቀድ ጉዞአቸውን ጀመሩ:: *በበትን አል አቀባህ* አልፈው አመሻሽ ላይ ሸርፍ የሚባል ቦታ ላይ ድንኳናቸውን ጣሉ:: ተጓዦቹ ተዳክመዋል:: ለቀናት ጉዞአቸው አካላቸው ዝሏል:: በበረሃ ስንከራተቱ ጉልበታቸው ተሚጧል::

በሚቀጥለው ቀን ማልደው ተነሱ የበረሃ ፀሐይ ከነጠረው ሰማይ ላይ ትፋጃለች:: እኩለ ቀን አካባቢ ከሩቅ ከፊታቸው የተምር ዛፎች የሚመስል ነገር ተመለከቱ:: እየቀረቡ ሲመጡ ግን ያዩት የተምር ማሳ አልነበረም:: በነርሱ አቅጣጫ የሚተሙ የጠላት መንጋ ነበር:: ተዋጊዎች ከፈረሶቻቸው፣በኮቴያቸው የሚነሱት አቧራ፣ ጦሮቻቸውና ሰንደቅ አላማዎቻቸው በመሬት ላይ የሚንቀሳቀስ የደመና ክምችት ይመስላል:: የሁሴይን ኃይል ዙዐስም በተባሉ ተራራ ስር አመች ቦታ ይዘው መሸጉ:: ቦታው ከጠላቶታቸው በስተግራ በኩል ገባ ብሎ ይገኛል:: የባላጋራ ወታደር 1000 ፈረሰኞችን ያቀፈና በሑር ቢን ያዚድ አል ሪያሒ ይመራል:: ሁሴይን የያዙት ቦታ የውሃ ኩሬዎች ነበሩበት:: ሁር የሁሴይንን ወገን በመክበብ ለማጥቃት ፍላጎት ቢያሳይም ሁሴይን እ[illegible]ት ተንከባከቡዋቸው በበረሃ ጥም የደረቁ የፈረሶቻቸውንና ወታደሮቻቸው በሁሴይን ከተያዙ ኩሬዎች እንዲጠጡ ፈቀዱላቸው:: ይህ አባታቸውና የአላህ ነቢይ ያስተማሩዋቸው ኢስላማዊ ስነ-ምግባር ነው:: ነብዩ (ዐ.ሰ.ወ) መካን ሰብረው ሲገቡ ቅሕፀ ያሳደዱዋቸው ነ በሩት የመካ ነዋሪዎች በሙሉ ምህረት እንዳደረጉ ይታወሳል::

የዙህር ሶላት ሲደርስ ሁሴይን ሙአዚናቸውን አል-ሐጃጅ ቢን መስሩቅ አዛን እንዲሉ አዘዙ:: የሁለቱንም ወገኖች ቀደሮች አንድ ላይ ባሉበት በኢማምነት መርተው አሰገዱ:: ኃላም የሁርና ጭፍሮች ፊት ለሳቸው የገቡትን ቃል እንዲያከብሩ ጠየቁአቸው:: ከኩፋውያን የተላኩላቸውን የድጋፍ ደብዳቤዎች ዘርግፈው አሰቡዋቸው:: የአስር ሶላት ሳይደርስ ከቦታው እንዲንቀሳቀሱ ተከታዮቻቸውን አዘዙ:: የሁር ወገን ሊያስከዱዋቸው አልፈለጉም:: ወደ ኩፋ ሊመጣቸው ዘንድእንደተላከ አሳወቃቸው:: ረጅም ሰዓት ከፈጀ ድርድር በኋላ ግን አንድ ስምምነት ላይ ደረሱ:: ይሄም ሁሴይን ወደ ኩፋ መጓዛቸውም እንዲያቆሙ ሁሴ ይን አል ሐጅር የሚባልታቦ ሲደርሱ ለኩፋውያን መልእክት በነርሱ አቅጣጫ እየመጡ እንደሆነ ጠቅሰው በቀይስ ቢን ሙስሂር አል-ሳይዳዊ እጅ ላኩት:: ይሁንጂ ሰይዳዊ በየአካባቢው የመሸገውን ወታደር ጥሶ ማለፍ አልቻለም:: ተያዘ ወደ ዚያድ ዘንድም ተወሰደ:: ኢብን ዚያድ ሁሴይንንእንዲያወግዝና እንዲረግም አዘዘው:: ሰይዳዊ በመስጀድ ለተሰበሰው ህዝብ የሁሴይንን ፍትሐዊ ትግል

በመደገፍና አብይደላህ ቢን ያዚድን በማውገዝ ተናገረ:: ቀጰውነት በመናገ ሩም ወዲያም ተገደለ:: ሌላ ሺሂድ::


በኩፋ ላይ ዐብይደላህ የተቃዉሞእን ቅስቃሴውን እያዳከመ ነው:: ሽብር፣ጉቦ፣ስለላ በመጠቀም ዋና ዋና የተቃውሞ መሪዎችን በማሳደድ እ የገደለና እያሰረ ህዝባዊውን ዐመጽ ለማዳፈን የማይፈነቅለው ድንጋይ አልነበረም:: በተለይ ሁለት ዋና ዋና ሰዎችን ሙስሊም ቢን እቂል፣ሃኒ ቢን ዑርዋህ ከገደለና አል ሙኽታር ቢን ዑባይንህ አልስቃፊ ካሰረ በኋላ ብትሩን ወደ ተራው ሙስሊሙ ሕብረተሰብ አዞር::

በኩፋ የተቃውሞውእንቅስቃሴ መቀልበሱን ሁሴ ይን አሁንም አልደረሱበትም:: ሁለተኛ መልእክተኛቸውን አብደላህ ቢን የቁርን ወደ ሙስሊም ቢን አቂል ላኩት:: ትክክለኛውን መረጃ ያገኙት አል-ጣለቢያህ የሚባል ቡታ ሲደርሱ ነው:: ዐብደላህ ቢን ያቅታርም በኢብን ኑመይር እጅ ወደቀ:: ወደ መስጅድ ተወሰደ ፤ እንደ ቀይስ ሁሉ ሁሴይንን ተሳድቦእንዲ ናገር ተጠየቀ::እሱ ግን በተቃራኒው ሁሴይንን በማወደስ ኡመያዶችን በማውገዝ ተናገረ:: ህዝቡም ሁሴይን እኸጁሰ ለፍ ተማፀነ:: በዚህ የተናደዱት የዚያድ ሰዎች ኢብን ያቅታርን ከሰገነት ገፍትረው ገደሉት::

አል-ዙባላህ የሚባል ቃ ሲድሱ የመልእክተ ኛቸው ሙሐመድ አቂል መገደል መርዶ ደረሳቸው:: በዚህም የጠሩዎቸው የኩፋ ነዋሪጃንደ ከዱዋቸው ተረዱ:: ወዲያውም ተከታዮቻቸውን ሰብሰባው የሚከተለውን ነገሯቸው::

«በኩፋ ያሉት ረዳቶቻችን ከድተውናል:: ከኛ ጋር መቆየት የምትሹ መቆየት ትችላላችሁ:: መሄድ የምትፈልጉ ማቆቸሁ ነው:: ነ ፃ ናችሁ አሉዋቸው:: ይህን እንደተናገሩ አብረዋቸው ከነበሩ ሰዎች አብዛኞቹ ተሰናበቱ:: የቀሩት ከሩቅ ከመካ አብረዋቸው የነበሩ ሙሃጂሮች ብቻ ነበሩ::»

ወደ መዲና መመለስ እንደማትችሉና ከዚህ ውጪ ባሉ አቅጣጫ ብቻ ሊንቀሳቀሱ እንዳለባቸው ተስማሙ:: ሁሴይን ተከታዮቻቸውን እየመሩ በዑስይብ አል-ሐጅነት አቅጣጫ ተጓዙ ሲመሽ ቀስር በኒ ሙቃል የሚባል ቦታ ድን ኳናቸውን ጣሉ:: (ሰፈሩ) ተከታዮቻቸው ፈረሶቹን ውሃ እንዲያጠጡና ራሳቸውምእረፍት እንዲወስዱ አደረጉ:: ሌሊቱንም ድካምእጅግ ተጫጭኖአቸው ስለነበር ራሳቸውን ሰተው እስከ መውደቅ ደርሰው ነበር:: «ላ ሀውላ ወላ ቀወተ ኢላ ቢላህ» የሚለውን ዱዓ ደጋግመው ይሉ ነበር:: በሁኔታው ግራ የተጋባው ልጃቸው ዐሊ ቢን አል ሁሴይን ለምን ይህን እያ ደጋግሙ እንደሚሉ ሲጠይቃቸው የሰጡት ምላሽ፣ እብድ ፈረሰኛ አየሁ:: ቀርቦም እንዲህ ሲል ተናገረኝ ሰዎች ይጓዛሉ፣ሞት ትከተላቸዋለች::» አለኝ እኔም ሞታችንን የምትጠቀሙን የገዛ ነፍሳችን (ሩሃችን) ናት አሉት»




ኢማም ሁሴን ከመካ ወደ ከርበላ ባደረጉበት ጎዞ ያለፉባቸውን ከተማዎችና ቦታዎች የሚያመለክት ካርታ።

የፈጅር ሶላት እንደሰገዱ ጉዞዘቸውን ቀጠሉ መንገድ አሳብረው ከኩፋ በተቃራኒው አቅጣጫ እየራቁ ሄደው:: ላይናዋ ላይ ደረሱ (ናይናዋ ትንሽ መንደር ናት):: ያልተጠበቀ ነገር የተከሰተውም እዚህ ላይናዋ ላይ ነበር:: »

በዑበይዳላህ ቢን ዚያድ ለሑር የተላከው ይህ ደብዳቤ አሳዛኝ ዜና ያዘለ ነበር:: በመልእክቱ አብን ዚያድ ታላቅ ወንጀል ለመስራት መፈለጉን ይጠቁማል:: ሑር የታዘዘበት ጉዳይ ሁሴይንን ከማንኛውም ዓይነት ጉዞ እንዲገታቸውና ለዚህም ምቹ ቦታ አትክልትና ውሃ በማይገኝለት ባዶ ሜዳ ላይ እንዲሆን የሚል ነበር::

ሑር ደብዳቤውን ለሁሴይን አነበበላቸው:: ሁሴይንም በናይም በአል ገዚሪያ ወይንም በሹፊያ ላይ ቢቆሙ እደሚስማሙ ነገ ሩዋቸው:: ሑር አልተስማማም:: ዙብይር ቢን አል ቀይን የተባለ ሰው መድረሻቸውን አል አቅር ላይ እንዲሆን ሃሳብ አቀረበ:: ሁሴ ይን ተቃወሙት:: በጉዞአቸውም ገፉ:: ለተሰበሰበው ተከዮቻቸውም እንዲህ ሲሉ ንግ ግር አደረጉ:: «የገጠመን ሁኔታ በ ውን የምትረዱት ነው:: ህይወት ላይ ላይታ ማጽ ለዘልአለም ጥሎን ጠፍቷል:: ከላይ የተንሳፋሪው ተጽኖ እያለቀ ከስር የሚቀረው ይቀራል:: ህይወት በአረምም እንደተሞላች የግጦሽ መሬት ነች:: እውነት ተከታይ እያጣች ውሸት ከልካይ ሲጠፋን:: ምእሚን ግን ፈጣሪውን በያዘው የእውነት ጎዳና ላይ ይገናኘዋል:: እኔ ከሞት ሽሂድነትን፣በጨቋኞች ስር ከመኖር ትግልንና ነፃነትን ቢሆን እንጂ አልመርጥም::»

## ቃል የተገባችው ምድር

የኡማያድ ጦር ጊዜ ሳያጠፋ ሊተናኮሉ ተጣደፉ:: የሁሴይን ወገኖች በበኩላቸው ጉዞአቸውን እንዲያቆሙ ተገደዱ:: ሁሴይን የአከባቢውን ስም ለማወቅ ፈልገው ጠየቁ:: ተከታዮቻቸው የቦታው ስም የጣፍ (ታፋ) ምድር መሆኑን ነገሩዋቸው:: ቦታው ሌላ ስም ይኖረው እንደሆነ ደግመው ጠየቁ:: ሀገሩ ከርባላ ተብሎም እንደሚታወቅ ተነገራቸው:: እንዲህም አሉ:-

> «አላህ ሃይ! አ ማናቸውም ጥቃት (ከር)ና መከራ (ባሏ) በአንተ  ጥላህን ስጠኝ:: ይህ ምድር የጉዞአችን መድረሻ ነው:: የመከራና ስቃይ የምንቀበልበት ደማችንን የሚናፈስበት መቀበሪያችን ነው:: አያቴም የነገሩኝ ይህንኑ ነበር::»

እለት ሐሙስ 2ኛው ሙሀረም 61ኛ ዓመቴ ሂጅራ ሁሴይንና ተከታዮቻቸው በዚሁ የመስዋእት ምድር ላይ ድንኳናቸውን ጣሉ:: ኢማም ሁሴይን ድንኳናቸውን ዘርግተው ገራዴያቸውን ማሾል ጀመሩ:: በአንደቡታቸው ስለ ገጠማቸው ሁኔታም እንዲህ ብለው ተናግረው ነበር:-

> « ጊዜ በውስጥሽ ስንቱን ነገር ይዘሻል ዳገት ቁልቁለቱ ባንቺ አድማስ ላይ ያልፋል:: ስንቱ ደጋግ ሙዕምን ባንቺ ውስጥ ሰምጧል:: ጊዜ ለዚሁ ድርጊቷ ምትክ ያላትም:: ፍጡርን ሁሉ በዚሁ በኛ ጎዳና ላይ ይራመድ ከምድር ላይ ስንሰናበት እንዴት አጭር ቅጽበት አለን:: ጉዳያችን ሁሉ ከ አላህ ጋር ነው::»

ሁሴይን ይህን ሲናገሩ ታዳምጥ የነዚህችው እህታቸው ይህ ሞት የተቀረበበት ሰው የሚናገረው ነው:: ሁሴይን  ስለ አሟሟታቸው እየጠቆሙን ነው::» አለች::

የዚያድ ጦር የሚመራው ሁበይዳላህ የመጀመሪያውን ተዋጊ ቡድን ላከባቸው:: ሁሴይንን እንድወጋው  በቅድሚያ ከተገፋፉት ሰዎች አንዱ ዑመር ቢን ሰዑድ ነበር:: ኢብን ሰዕድ ሁሴይንን ሊያጠቁ አልደፈሩም:: ፍላጎትም አልነበራቸውም:: በአእምሮአቸውም ሁለት መቓ ጥያቄዎች ይመላለሱ ነበር:: ሁሴ ይንን በመግደል ለዚህች አለማዊ ህይወት እጅ መስጠት ወይንም ጠንክረው አለማዊ ጥቅማ ጥቅሞችን ከሁሴን ህይወት ማብለጥ::  መሆን ወይም አለመሆን! በመጨረሻ ግን ኡበዱላህ ቃል የገባላቸውን የኢል-ረይ ሀገር ሹመት ሊሰርዝባት ሲያስፈራራ በመዋጋቱ ላይ ወሰነ:: በሁሴይን ላይ ወሰነ:: በሁሴይን ላይ ጦደሮቹን ለማዝመ  ት እንዲህ የምትል የስንኝ ሰንዝሮ ነበር ይባላል::

«የአልርይ ሀገር ሹመት ህልም
ወይ ሁሴይንን ገድዬ ልወቀስ?
ሁሴይንን ቢገድለው ዘለአለማዊ እሳት
የአልረይ ጓሮም የአይኔ ማረፊያ ነው!!»

በጥፋቱ ገፋበት ለሹመቱ አጎበደደ ምድራዊው ጥቅም አሸነፋቸው:: 4000 ወታደሮችን እየመራ ወደ ላይናዋ ተሰማሩ:: የሁሴይንንም ካምኘ ከበበ:: ሁሴይንን ለድርድር ቀርቡዋቸው:: ሰኡድ ተቀበሉ:: ለዑብይዳላህ ቢን ዚያድ የላከው መልክት የሁሰይን ሰዎች አከባቢውን ለቀው እንድሰደዱ የሚል ነበር:: ኢብን ዚያድ ግን ድርድራቸውን ውድቅእያደረገ:: ሁሰ ይን አሁን ከገቡበት ወጥመድ ማዳን ማለት የወታደራዊው ኃይል ዚዛን ማዛባት ስለሚያመጣ የተከሰተውን ምቹ አጋጣሚ በመጠቀም የሁሴንን ኃይል መደምሰስ እንደሚሻል አመነበት:: ይህ ውሳኔ ኋላ ውጤቱ የከፋ ነበር:: በኡማው ላይ ታላቅ ውድቀት ከማስከተሉም በላይ ለ ኡማያድ አገዛዝ ሽንፈት ሁነኛ ምክንያትም ነበር::

ኡበዱላ በግብዝነቱ ፀንቶ ሁሴይንን እንዲ ቱ አዘዘ:: ለዑመር ኢብን ስዑድ የላከው የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ በከፊል እንዲህ የሚል ነበር::

«ከሁሳይን ጋር ከመዋጋት ወደ ኋላ እንድትል አልፈልግም:: ጊዜህን በድርድር አታጥፋ:: የሠላምና የህይወት ዋስትና ስትሰጥ አትኑር:: ከኔ ጋርም ለማስታረቅ አትጣር:: የኛን ስልጣን የሚቀበሉ ከሆነ በሰላም ወደኛ ላካቸው አለበለዚያ ተዋጋቸው:: ይህ ቅጣትእንቢተኝነታቸው ይገባቸዋል:: ትእዛዜን በአግባቡ የማትፈጽም ከሆነ የአዛዥነቱን ፁ ለተወካዬ ሺምር ቢን ዚል ጀወሽን አስረክብ፤ ወሰላም::»

በሙሐርም ወር ሰባተኛው ቀን ላይ ዑመር አብን ሰወድ የሁሰይን ወደ ጢግሪስ ወንዝ እንዳይደርሱ መንገዱን ዘጋባቸው:: በዚህ ድርጊቱ በውሃ ጥም ሊፈጃቸው ወይ በቸነፈር ተቆልተው እጅ እንዲሰጡ ለማስገደድ ነበር:: ይህ ሳይበቃው ኢብን ሰኡድ ለወታደሮቹ የጥቃት እጃቸውን ሊሰነዝሩ ጎራዴዎቻቸውን መወልወል ጀመሩ:: ሐሙስ ሙሐረም 9ኛው ቀን በታሪክ ምእራፍ ልዩ ቀን ናት የጠላት ሰራዊት እየቀረባቸው መጣ: ሁሴይን ሰለ ወደፊቱ የሰላስላሉ ትግላቸው በሚመጣው ኢስላማዊ ትውልድና የነፃነት ናፋቅ ህዝቦች ዘንድ የሚፈጥረውን ስሜት ያስባሉ:: ኡማው ለሚገጥመው ውድቀት ይጨነቃሉ:: ይህ በአእምሮአቸው ከሚመላለስ የሃሳብ አለም የነቁት እህታቸው የጠላት መንጋ የመምጣቱን ዜና ስታበስራቸው ነበር::
«የጠላት ሳራዊት ድምጽ አይሰማህም» ዘይነብ:: አልአበስ ቢን ዐሊም
«ወንድም ሆይ የጠላት ሰራዊት ደርሷል ----» አሉት::

ሁሳይን ከተጋደሙት ተነስተው የሚያደርጉት አሰቡ:: ቀድመው ከኡማያድ ወታደዎች አዛዥ ጋር ለመወያየት ፈለጉ:: ወታደሮቹና አዛዦቻቸው የሁሰይንን ደም ጠምቶአቸዋል:: ገድለዋቸው በኢብን ዚያድ ቃል በተገባላቸውን ሹመት ለመንበሽበሽ ቋምጠዋል:: ሁሰይን (ዐ.ሰ) ለድርድሩ አል ዐባስን ላኩባቸው:: የተጠበቀው መልስ መጣ:: ቃላቸው አንድ ነበር:: «ሁሰይን ለኢብን ዚያድ ሰልጣን  ጅን ይስጥ:: አገዛዙን ያጽድቅ::» የሚል ሁሴይን ደግሞ ህይወታቸውን ለማዳን ሲሉ ለአንድ ጨቋኝ ገዢ ሰርዓቱን ለማጽዳት አልፈለጉም:: ህገ-ወጡን የኡማያድ አገዛዝ በኡማው ላይ ሊጭኑት አልደፈሩም::

«እንዴት ያዚድን ለመሰለ አምባገነንና ህገወጥ ሰው አገዛዝ ድጋፍ እሰጣለሁ?»

«ሞቴ ከሸሂድነት ሌላ እንዲሆን አልሻም:: በጭቆና ስር የምትኖር ህይወት ራሷ ሞት ናትና::»

ከጥቂት ቀናት በፊት አል-በይዳ ላይ ለኡማያድ ሰራዊት የተናገሩትን ቃል ደግሞ ለተከታዮቻቸው አሰሙ:-

«ህዝቦች ሆይ! የአላህ መልእክተ ኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:: አንድ ጨቋኝ ገዥ አላህ የከለከለውን የሚፈቅድ፣የነቢዮን ሱና የሚፃረር ድርጊት ሚሰራ ዜጎችን ያለ ርህራሄ ረግጦ የሚገዛ ሀራም የሆኑ ስራዎችን እንዲሰራ የሚያስገድድን መሪና ስርዓቱን መደገፍ ከአላህና ከነቢዮ ጋር የሚያጋጭ በመሆኑ ይህን ከመፈጸም ሞቴን እመርጣለሁ::

ከዚህ መልዕክት ጋር አያይዘው ኢማም ሁሴን አል አባስን ወደ ኢብን ሰዓድ አንድ ሌሊት እንዲታገሷቸውና እርሳቸውም አስቦበት መልስ እንዲሰጡ ጥያቄ እ ንዲያቀርብ ላኩት:: ኡመር ኢብን ሰዒድም የአንድ ምሽት ማራዘም ጥያቄን ተቀበለ::

## የመጨረሻው ሌሊት

ኢማም ሁስይን አንዷን ሌሊት የፈለጉበት (ምክንያት) ውሳኔያቸውን ለመቀየር አልነበርም:: ሌሊቱን *ለኢባዳ* ነበር የመረጡት:: ከቤተሰቦቻቸውና ከዘመዶቻቸው ከሚወዷቸው ተከታዮቻቸው ጋር የሚገናኙበት የመጨረሻው ሌሊት እንደምትሆን ይፈልጋሉ:: በነጋታው የሚጠብቃቸው ነገር ያውቁታል:: ለዚህም ነው ወንድማቸው ኢብን የባሰን ወደ ኢብን ሰዐድ እንዲህ ሲሉ የላኩ፡-

> «ወደ እነርሱ ሂድ:: (ተመለስ) ሌሊቱን እስከ ንጋት ይታገሱን ዘንድ አግባባቸው:: ይህም ለፈጣሪችን አንዳንድ ዱእንድናደርግ ይረዳናል:: ተውባህ እንድንገባ፣ምህረቱን እንድንጠይ ቃለን:: አላህ ሁሌም ስላትን እንደሚወድ ቁርዓኑን መቅራትና ለርሱ ዱዓ ማድረግ ዝክር ማብዛትና እስቲግፋር ምህረት መጠየቅ እንደሚወድ (እንደማፍቀር) ያውቃል::»

የኡመያድ ሠራዊት የሁሰይንን ካምኚ መክበብ ጀምሯል:: ሴቶችና ህፃናት በሁኔታው ተደናግጠዋል:: ኢማም ሁሴይን እነርሱን ከአደጋ ለመከላከልና ከሚሰነዘርባቸው ጥቃት ደካሞች እንዳይጉዱ ለማድረግ ተጨንቀዋል:: (ሀሳብ ገብቶዋቸዋል::)

ፀሐይ ልትጠልቅ ስትከበኩብ ኢማም ሁሴይን ለቤተሰቦቻቸውና ለተከታዮቻቸው መልእክት አስተላለፍ:: ይህም ጠላት የሚፈልገው እሳቸውን ብቻ እን ጂ ሌላ ሰው ማጥቃት ስለማይፈልጉ ማንኛውም ሰው ከጦርነቱ ጎራ (ቀጠና) ለመውጣት ለመለየት ከፈለገ ነፃነት እንዳለው አሳወቁ:: የተነቃነቀ ግን አልነበረም:: ሁሉም ለውጊያ ዝግጁ መሆናቸውንና ህይወታቸውን በኢስላም በኩል ለመሰዋ ት ታላቅ ምኞታቸው መሆኑን በአንድነት አረጋገጡላቸው::

ጭለማ በበረሃ ሌሊት ላይ ነግሷል:: የነቢዮ (ሰ.ዐ.ወ) ቤተሰቦችና ደጋፊዎቻቸው ግን አይኖቻቸውን አልጨፈኑም:: ገሚሶቹ ይህ በሌሊት ርዝማኔ ልክ ለሰላት ቆመዋል:: ግምሶቹ አላህ ምህረቱን ይለምናሉ:: የተቀሩት ዱአ ያደርጋሉ:: ቁርአን ይቀራሉ (ያነባሉ::) ለቤተሰቦቻቸው *ወሲያ* የሚናዘዙትም ብዙ አሉ:: ከፈጣሪያቹ ጋር ለመገናኘት ዝግጁቱን አጠናቀዋል:: ጎራዴዎች አፎታቸው ተመዘዋል::: ጦር ይሾላል፣ ቀስቶች ዒላማቸውን ይጠባበቃሉ:: በከርባል ምድር ላይ ሁሉም የሌሊትእንግዳ ሆኗል:: ቀ ጣዩ በሚቀጥለው ንጋት የሚከሰተው የታሪክ ምዕራፍ ይሆናል:: በሰው ልጆች ረጅም ህይወት ውስጥ በጎራዴ ጦር ከተፃፉት ውድ የትግል ሪኮች ተርታ ሊሰለፍ ሰዓታት ብቻ ይቀራሉ::

ሌሊቱን ኢማም ሁሰይን ቤተሰቦቻቸውን የሚወዷቸውንና የሚወዱዋቸውን ሁሉ ተሰናበቱ:: ከነዚህ የቅርብ ሰዎች ውስጥ በተለይ ከአል ስጃድ፣ ዘይነብ፣ሉካይናህ፣ለይላ፣

አል-ረባከና የወንድማቸውን ልጅ አል-በቂር፤ አጎት የሚሆኑትን አል-በቂርን ሁሉንም ተሰናበቱ:: የመጨረሻ ወሲያቸውን (ኑዛዜ) አደረጉ::

አሁን ሁላቸውም ለብቻቸሁ ከቢ ሀገር ቆማችዋል :: በሩቅ ምድር በሐሰት ፈርሰኞችና በሌሊት ጭለማ ተከበዋል:: ከአላህ መልእተ ኛ (ዐ.ሰ.ወ) ርቀዋል:: ከሳቸውም አይን ጠፍተዋል:: ኢማም ሃሰንና አል-ዘህረ (ዐ.ስ) ባረፉበት መዲና ለነርሱ በረጅም ርቀት ላይ ትገኛለች:: በግመል፣ ጉዞ የሁለት ወር መንገድ ይለያቸዋል:: በአጠገባቸው የሚቀርቡት በአቅራቢ ያረፍትን ሊቆቸውን አሚ ሩል ሙእምንን አሊን (ዐ.ስ) ነው:: እሳቸው በነዳፍ በሠላም ያንቀላፋሉ::

የመጨረሻዋ ሌሊት በፍጥነት አለፈች:: ጁመአ (ዐርብ) የአሹራ ቀን እ(ለት) እንደተጠበቀ ደረሰ:: ጉራዴዎች፣ጦሮች፣ቀስቶች፣ሁሉም የሁሴይንን ቅዱስ አካል ሊቆራርጡ ተሰናደዋል:: ለተከታዮቻቸው አካላት ላይ ሊሰፍሩ አስፍስፉዋል::

ዑመር ቢን ሰዐድ ጦሩን አንቀሳቀሴ:: የሠራዊቱን ቀኙ ጎን ፊት መሪ ኃይል እንዲመራ አምሩ ቢን አል-ሀጃጅ ተሰይሟል:: በግራ አቅጣጫ ጦሩን የሚመራ ሺምር ቢን ቢል-ጃውሻን ነው:: ዑርዋህ ቢን ቀይስ የፈረሰኞችን ይዞ ቦታውን ይዟል:: እግራኛው ሠራዊት ባሽዝ ቢን ረቤ መሪነት ተሰልፏል:: አርማቸውን ያነገበው ዱረይድ የተባለ ሰው ነው::

ኢማም ሁሰይን (ዐ.ስ) የጠላት ጦር ይፁና አስላለፍ ከገመገሙ በኋላ ሃሳባቸው እንደ ፀኑ ነው:: የተጋፈጣቸው የጠላትኃይል ከመጠን ያለፈ እንደሆነ አይተዋል:: ይሁንጂ በአቋማቸው ፋቅ አላሉም ዓለማቸውን ከግብ ለማድረስ በመረጡት መንገድ መራመድ አለባቸው::እያንዳንዱ ተዋጊያቸው ከፍተ ኛ ወታደራዊ ሞራል ታጥቆል:: በጦሮቻቸው ጫፍ ላይ ልበታቸውን የሰኩ በረድፍ ደረታቸውን ለፈጣሪያቸው ሊያስረክቡ በጀግንነት ይጠባበቃል:: ሁሰይን ዱአ ለማድረግ እጃቸውን ለአላህ ዘርጉ::

# የባያባራው ጦርነት ( ፍልሚያ)

የጠላት ወታደር ኢማም ሁሰይንና ተከታዮቻቸው ያሉበትን ካምፕ መውረር ጀመረ:: ኢማም ሁሰይን ዘሃይር ቢን አል-ቀይን የተባለውን ሰው የጠራቸው የቀኝ ክንፍ አዛዝ አድርገው መርጡዋቸውእንዳ ሁም ሀቢብ ቢን ሙዚሂር ግራ እንክፍይዝ ተደላደሉ:: ኢማም ሁሰይንና ቤተሰቦቻቸው መሀከላቸውን አቅጣጫ ተከተሉ:: አርማቸውን ለወንድማቸው አል-ዐባስ ሰጥተዋል:: በአጠቃላይ በሳቸው ወገን ለጦርነቱ የተሰለፉ ሰዎች ቁጥር 72 ብቻ ነበር::

ጦርነቱ ስጀመር በፊት ኢማም ሁሰይን ለኡመያድ ጦር የመጨረሻውን ንግግር አደረጉ:: ቀደም ብለው የተገባላቸውን እቃዎችከብ ሩ ዓለማዊ ደስን፣ ጥቅማጥቅሞች ቲታለው ከአላህ መንገድ እንዳያዘነብሉ:: በጥብቅ አስጠነቀቁዋቸው:: ይሁን እንጂ በሳቸው ምክር ጆሮ የሰከ አልነበረም:: አንድ ሰው ብቻ በሳቸውእውነት ያዘለ አነጋገር ልቡ ተሯ ሁር ቢን ያዚድ አል ሪያሂ እስከዚያን ቅጽበት ድረስ ሁር ከኡማያድ ጦር አመራሮች መሀከል አንዱ ነበር:: እንዲያውም ኢማም ሁስይንን በዒራቅ ውስጥ በቁም እስር እንዲቆዩ ከአደረጉ ሰዎች በግንባር ቀደም ይጠቀሳል:: አሁን ግን ልብ በእውነት ተሸነፈች :: ከእውነተኞች ጎራ ተቀላቀለ በኢማም ሁሴ ይን ፊት ለሹሃዳነትም ሊበቃ ችሏል::

በኢማም ሁሰይን ወገን የሆኑ ሰዎች እንደ ዙሀይረ ቢን አልቀይንና ቡረይና የመሳሰሉት የኡመያድ ወታደሮችን በእውነት ላይ ለማሳመን ቢቀርቡም እሽታን አላገኙ ም::

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሳሉ ነበር ኢማም ሁሰይን በፈረሳቸው ላይ ሆነው የአላህን ቁርአን በራሳቸው ላይ ተሸክመው ለኡማያድ ሰራዊትእንዲህ ብለው መጣራት የጀመሩት:: «ህዝቦች ሆይ የአላህ መጽሐፍ ና የነቢያችንን ሱንና (በመሃከላችን) (እንዲገኝ እድል እንሰጣቸው:: ሲሉ ተጣሩ::

የኡማያድ ተዋጊዎች በያዙት አቋማቸው ፀኑ:: ለዚሁ ዓለማቸው የሚያቀርቡት ብቸኛ ምክንያት «መሪያችንን ኢቢን ዚያድ መታዘዝ አለብን የሚል ነበር::

ኢማም ሁሴይን የርሳቸው ወገን ውጊውን እንዳይጀመር ጥብቅ ትእዛዝ አስተላለፉ:: በሌላው ወገን ኢብን እጁ የተባለ ሰው ለውጊያ እጅግ ተጣድ ፎ ይታያል:: የመጀመሪውን የቀስት ወርወራ ውጊያውን የጀመረውም ራሱ ዑመር ቢን ሰዐድ ነበር:: በነብዩ ቤተሰብ ላይ በመወርወር ከዚህ በኋላ የኡማያድ ተዋጊዎች ጥቃቸውን ከየአቅጣጫቸው መሰንዘር ጀመሩ:: በቀስቶቻቸው ያልቆሰለ የኢማም ሁሰይን ተከታይ አልነበረም:: ኢማም ሁሴይን ለተከታዮቻቸው አጭር መልእክት አስተላለፉ፤ በማይቀር

ሞት በኩል ወደ ፈጣሪያችሁ ለመናኘት ተዘጋጁ፡፡ እነዚህ ቀስቶች የካዲዎች ህዝቦች ደብዳቤዎች ናቸው፡፡»

የኢማም ሁሰይን (ዐ.ሰ) ተዋጊዎች ምንጅንካን በቁጥር እጅግ አናሳ ቢሆኑም በመዋጋት ሞራላቸው ላይ ያመጣው ለውጥ አልነበረም፡፡ ለአንድ ሰአት ተኩል ለምሆን ጊዜ በቆየ ጦርነት 50 የሚሆኑ የኢማም ሁሴይን ተከታዮች ክፉኛ ቆሰሉ፡፡ እያንዳንዱ ወታደር በየተራ የኡማያድ ወታደር ገጠመ፡፡ ጦርነቱ ከጅምላ ጥቃት ወደ ጨበጣ ገባ፡፡ የኢማም ሁሰይን ቀሪ ወታደሮች ለግላቸው ኡማ ያዶቹን ሊገጥሙ ከኢማም ፍቃድ ጠየቁ፡፡ ተፈቀደላቸው፡፡ ከነዚህ በጀግንነታቸው ከወደቁ ሰዎች መሀከል ሀቢብ ቢን ሙዘሂር፣ቡረይር፣አብዱላህ ቢን ዑመይር ይገኙባቸዋል፡፡

በተለይ የአብዱላህ ቢን ዑማር ባለቤት ኡም ወሀብ የባለቤቸው አግዘው ወደ ውጊያ ዘለው መግባት ሴቶች ሳይቀሩ ለዚህ ትግል የነበረውን ታማኝነት ይመሰክራል፡፡ ሀናም ወሀብ ምንምእንካን በ ኢማም ሁሰይን ቢከለከሉም የነብዮን ቤተሰብ ከአማጽያን ለመታደግ ያደረጉ ጀግንነት በሙስሊም ሴቶች ውስጥ ታላቅ ቦታ አለው፡፡

የኢማም ሁሴይን ተዋጊዎች በጀግንነት በሹሃዳነት መውደቅ ጀመሩ፡፡ እየተከታተሉ ተሰው፡፡ ይሁንጂ በኡማያድ ጦር ላይ የደረሱት አደጋ ቀላል አልነበረም፡፡ በተለይ በጨበጣ ውጊያ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ወታደር ያጣው የዑመር ቢን የሳኡድ ወገን ከዚህ ስልታዊ ውጊያ ራሱን አፈገፈገ፡፡ የኢማም ሁሰይንን ኃይል ከሩቅ በተቀናጁ ጥቃት ብቻ መሰንዘር እንደሚበጅ አረጋገጠ፡፡

በአምሩ ቢን አል ሀጃጅ የተመራው የኡማይድ ሠራዊት በቀኝ አቅጣጫ አድስና የተቀናጀ ጥቃት ከፈተባቸው፡፡ በግራ በኩል በሽምር የተመራ ሌላ ኃይል ገጠማቸው፡፡ የኢማም ሁሴይን ተዋጊዎች ሁሉንም እንደየአመጣጣቸው እያ ስተናገዱ በጀግንነት መዋጋት ገፉበት፡፡ በዚህ በተፋፋመ ውጊያ መሀከል ታላቅ ገድል እያሰ ሩ ያለፉ የኢስላም ጀግኖች ቁጥር ቀላል አልነበረም፡፡ አብደላ ቢን ዑመይር ብቻ በዚህ ውጊያ 19 ፈረሰኞችን፣ የ12 እግረኞች ወታደሮችን ገድሏዋል፡፡ በመጨሻ ግን በመቁሰሉ በኡማያድ ተይዞ ተገደለ፡፡ ባለቤቱ ኡም ወሃብ ሁኔውን ስታይ እን ደገና ዘላ በውጊያው መሀከል ሮጣ ገባች፡፡ ከአብደላህ ቢን ዑመርይ ጎን ተንበረከከች፡፡ ጨቋኙ የኡማያድ ጦር መሪ ኢብን ሰይድ እሷም እንዲትገደል አዘዙ፡፡ ጭንቅላ ቷ ተቆርጦ ኢማም ሁሰይን ባሉበት አቅጣጫ ተወረወረ፡፡

ውጊያው እየተፋፋመ ሄደ የኢማ ም ሁሰይን ቤተሰቦች የተጠለሉበት ድንካኖች ተወረሩ፡፡ የኡማያድ ወታደሮች ዝርፊያና ቅሜያቸውን አጧጧፈ፡፡ የተበተኑ ህፃናት ና ሴቶች ወይታ ከየቦታው ይሰማል፡ ፡ ኢብን ሰዐድ ድንኳኖቹ ሁሉ እሳት እንዲለኩ ሱ

አዘዙ። የእሳት ወላፈኑ እየተንቦገቦገ ሰማዩን ሞላው። ከምድር የሚነሳው አቧራ በጭስ ተክሎበት አካባቢው በጉም ተሸፈነ።

አሁን ሰዓቱ እኩለ ቀን ተቃር ቧል። ኢማም ሁሰይን በውገያው መሀከል ሆነውም የሶላት ወቅት መድረሱን አልዘነጉትም። ወዲያውም የተቀሩት ተከታዮቻቸው አከታትለው ለሶላት ተሰበሰቡ። ከዙህር ሶላት በኋላ ውጊያው ተጧጧፈ። ወደ ውጊያው ሜዳ የገባ ሁሉ አልተመለሰም። በዚያው በሹሃደነት ይወድቃል። የበኩር ልጃቸው ዐሊ፣ወንድሞቻቸው ዕባይሳልህ ፣ዑስማን፣ጃፋርና መሐመድ የወንድማቸው አል-ሐሰን ልጆች የሆኑት አቡ በክር አልቀሲም አል ሀሰኙናሽ የእህታቸው ዘይነብ ልጅ ዐውን ቢን አንዱላህ ቢን ጃፋር አል ጠያር ሁሉ፣የአቂል ቤተሰቦች አብደላህ ቢን በሐሊም ቢን አቂል አብዱራህማን ቢን አቂል ጃፋር ቢን አቂል አብዱላ ቢን አቂል ሁሉም አንድ ላይ ለሹሃዳነት በቁ።

የአቂል ቤተሰቦችና የዐሊ.ቢን አቢ ጧሊብ (ዐ.ስ) ቤተሰብ የተወጣጡ የነብዩ (ዐ.ሰ.ወ) ተከታዮች የሆኑ ሸሃዶች የተቆራረጠ አካል የፍልሚያውን ሜዳ ሞላው። በረሃው አሸዋ ላይ እንድ እኩለ ሌሊት ከዋክብት ተበተኑ። ምድሪቷን በደም ብርሃን ሞሏት። ኢማም ሁሴይን በዚህ መሀከል ብቻቸውን ቆመዋል። የሚያለቅሱ ህፃናት ድምጽና የሴቶች ጩኸት አካባቢው ተናውጧል። በመጨረሻም ላይ ሚስሟቸውን ሁሉ ማጣራት ጀመሩ።

«የነብዩን ቤተሰብ ሴቶች የሚከላከል ማነው? አላህን የሚፈራን የሚረዳ ማነው? አላህን ታዛዥ ከጎናችን የሚሰለፍ ማነው?»

ምላሽ የለም ጩኸቱና ዋይታው አይሏል። ኢማም ሁሰይን በ ውጊ ከመግፋት ሌላ አማራጭ አጡ። ራሳቸው ወደ ውጊያው መሀከል ሊገቡ ተነሱ። በጣም የሚወዱትን ልጃቸውን አብዱላህን ለመጨረሻ ጊዜ ስመውት ሊለዩኡህታቸውን ዘይነብን ጠየቁ ቀረበላቸው። ተሰናበቱት። ላይመለሱ በምድር ላይ ዳግም ላይገናኙ። ከጨቅላ ልጃቸው ጋር ለዘለአለሙ ሊለያዩ በዚህች ቅጽበት ለዓይን የሚሰቀጥጥ ድርጊት ተፈፀመ። ኢማም ሁሰይን ጨቅላ ልጃቸውን አቅፈው እንደ ያዙ ከጠላት ወገን የተወረወረ ቀስት በህፃኑ ላይ አረፈ። ከርሱ የሚጉርፈው ደም የኢማም ሁሴን መዳፎችያጠበ ወደ መሬት ይፈሳል።እሳቸው ደሙን እየዘገኑ ለፈጣሪያቸው ተጣ ሩ። «ያ አላህ ሆይ! የሚደርሰብንን ፍትና ላይ ምስክርነትህ ስላለ በዚሁ እንጽናናለን።»

ኢማም ሁሰይን ለቆሰለውና በዩፁ ው ለወደቀው ቤተሰቦቻቸው ውሃ ለማምጣት በጠግሪሳ ወንዝ አቅጣጫ ጋለቡ። ወንድማቸው አባስ ቢን ዐሊ ተከተለዋቸው ነበር። ግ ብዙም ሳይርቁ የጠላት ኃይል ላያያቸው። ሁለቱም ለየብቻቸው መዋጋት ጀመ ሩ። ዐባስ

ብዙ የኡማባድ ሠራዊት ገደሉ፡፡ በጽኑም ቆሰሉ፡፡ ኢማም ሁሰይን ለአላህ ዳግም ድምፃቸውን አሰሙ፡፡

«አላህ ሆይ! በነቢዩ ቤተሰብ የሚደርሰውን ጭካኔ ምስክር ነህ፡፡»

ኢማም ሁሰይን ለብቻቸው ቀሩ በዙሪያቸው ተከታዮቻቸው በሹሃድነት ወድቀዋል፡፡ የንፁኃን ደም ከጠማቸው ወንበዴዎች በሚከላከልነላቸው ሰው የለም፡፡ ለራሳቸው ቃል ገቡ፡፡ «እንደ ሙስሊም ተዋግቶ ለወደቀ ሁሉ) እረፍት የለም፡፡

በእውነት መንገድ ላይ በመዋደቁ ከበዳዮችና ከወንጀለኞች ጎራ ተለይቷል፡፡ በህይወት ቢዘገይ ለሰራሁት አልፀፀትም፣ቢሞት አልወደቀም፡፡ ከኋላችን ለሚቀሩት ጨቋኞችና ወንጀሎች ህይወት ሁሌም በነርሱ ላይ መሪር ትሆናለች፡፡ በፈፀሙት አርመኔያዊ ድርጊት እየተ ለበለቡ ኖረው ያልፋል፡፡» ቆጠቁት የነብዩን (ሰ .ዐ.ወ) ጎራዴ ነበር፡፡ ልባቸው የዐሊ ልብ (ዐ.ስ) ነው፡፡ ይህ ቀንና ቦታ ለሳቸው በነቢዩ (ዐ.ሰ.ዐ) የተተነበየላቸው የፍፃሜያቸው ምድርና ዘመን ነው፡፡ በድፍረት የጠላቶችንወ በጨበጣ ገጠሙዋቸው፡፡ ብዙዎች በአጃቸው ላይ ወደቁእሳቸው በዚህ መሀከል ከርሳቸው ህይወት ይልቅ ያሳሰባቸው የቤተሰቦቻቸው የህፃናትና የሴቶች ይዞታ ነበር፡፡ ካምፓቸው በእሳት እየነደደ ነው፡፡ ለኡማያድ ስራዊት የመጨረሻ ጥሪያቸውን አሳሙ፡፡

«እኔ የእተዋጉትሁ ነው፡፡ ሴቶችና ሕፃናቶች ምንም ጥፋት የለባቸውም፡፡ ዋልጌ ወንጀለኛ ወታደሮቻችሁ እነርሱን ከማሰቃየት እንዲታቀቡ እንዲከላከሉ ብቻ ይሁን፡፡»

አንድ የኡማየድ ወታደር የወረወራ ት ቀስት በጉሮሮአቸው ላይ አረች፡፡ አካላቸው በተከታታይ ቀስቶች ተተለተለ ወንጀለኞችና ወረበሎች ከየአቅጣጫው ተረባረቡባቸው፡፡ ብዙ ደም ስለፈሰሳቸው ተዝለፍልፈው ወደቁ፡፡ ስልሳ ሰባትታ ቦቆሰለው ነበር፡፡ ደማቸው የጂሃድ መንፈስ ነበረበትታሪክበ ምእራፍ ወንጀለ ኞችንና የጥፋት መልእክተኞችን የሚታገሉ ትውልዶች መብቀያ አምባ ሆነ፡፡ ጠላቶቻቸው በዚህም አልረኩም፡፡ ሽምር የተባለው የኡመያድ የጦር መሪ የወደቁትን የኢማም ሁሴይን (ዐ.ስ) ጭንቅላት ቆርጦ አላቀቀው፡፡ ለኢብን ዚያድ አበረከተ፡፡ የዚህ ራስ ቅል ባለቤት ግን ለጨቋኞቹ መሪዎች በሕይወት ሳለ አልተገዛም፡፡ ኢስላማዊ ደም የነበረው አንደበትም ነበረው፡፡ «በአላህእምላለ ሁ! እንደተዋረደ ሰው እጄን አልሰ ጣችሁም፡፡ እንደ ፈሪም ከጂሃድ ሜዳ አልፈገፍግም፡» ይህ የኢማም ሁሰይን የተቆረጠ ጭንቅላት ለዚያድ በስጦታ ተበረከተ፡፡

## የሁሴይን ኮኮብ ስትጠልቅ

ሰማዩን የሞላው የአቧራ አውሎነፋስ ረግቧል፡፡ የጎራዴና የጦር፣ የቀስት ፍጨት ከስሟል፡፡ ልትጠልቅ ተቻኩላለች፡፡ የከርበላ በረሃ ላይ የሚያፏጨት ንፋስ በየ ስፍራው የተበተኑ የሙስሊም ሹሃዶችን አካል በደቃቅ አሸዋ መልሶባቸዋል፡፡

ሁሰይን (ዐ.ሰ) 17 ከሚሆኑት ወንድሞቻቸው፣ ልጆቻቸውና፣ የወንድ ፍሬዎች ልጆች፣ የአጎታቸው ልጆች እንዲሁም ከ60 የታላላቅ ተከታዮቻቸው ጋር ለዘላለሙ ክብር አንቀላፍተዋል፡፡ ሁሉም በተዘረጋው ሰፊ በረሃ ላይ ወድቋል፡፡ ከአጠገባቸው የኢማም ሁሰይን (ዐ.ሰ) ካምፕ ይታያል፡፡ ሴቶችና ህፃናት ተጠልለውበታል፡፡ ከ ውስጣው የለው ወንድ አንድ ሰው ብቻ ነው፡፡ በህመም ምክንያት በጂሃድ ሊከፈሉ ያልቻሉት ኢማም ዐሊ ቢን ሁሰይን አልሰጃድ (ዐ.ሰ)፡፡ የኡማያድ ፈረሰኞ ሁሰይን ቤተሰቦች ወደ ተሰበሰቡበት ካምፕ አመሩ፡፡ ሴቶችና ህፃናት ከአካባቢው ለመሸሽ ጥረት ቢያደርጉም መሄጃ አላገኙ ም፡፡ ወታደሮቹ አረማነያዊ ተግባር ሊፈጽሙባቸው ጀመሩ፡፡ ሴቶች፣ ትናንሽ ሴት ልጆች ሳይቀሩ በጆሮአቸው ያንጠለጠሉት ወርቅና ሌሎቻችንም ንብረቶቻቸውን ተቀሙ፡፡

ወታደሮቹ በሹሀዳነት የወደቁ የሁሰይን ወገኖችን ጭንቅላቶች /ራስ ቅል/ ያልተቆረጡ አካላትን እየቆረጡ ለገደሉዋቸው ሰዎች ታደለ፡፡

የኢማም ሁሰይን ጭንቅላት ተቆርጦ ለኺምሳ ቢን የዚድ አል አሰባሃ ተሰጠ፡፡ በእሱና በሀሚድ  ቢን ሙስሊም አል አዝዲ የተመራው የመንገደኞች ቡድን ረጅሙን ጉዞ ወደ ኩፋ ጀመሩ፡፡  የሌሎች ተዋቂ የሁሰይን አጋሮዎች የራስ ቂል ለሽምር ቢንዚል ጃውሻን ሐይስ ቢን አሻዝና አምሩቢን አል ሃጃጅ አንግተው የመልስ ጉዞአቸውን አፋጠኑ፡፡

## የሹሃዶች እረፍት

በኡማያድ ወታደሮች እጅ የወደቁት ምርኮ ኛ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቤተሰቦችና ተከታዮቻቸው ወደ ኩፋ እንዲጓዙ ተገደዱ:: በውስጣቸው ብዙ ሴቶች፣ህፃናትና ዐሊ.ቢን ሁሰይን አል ስጃድ (ዐ.ስ) ይገኙ ነበር:: ከበስተኋላቸው በከርባላ የወደቁ የሹሃዶች አካላት በደም ኩሬ ተከቧል:: በግፈኞች የተቆራረጠ አካሎቻቸወታጠዋቦተበታተኗል: : ከመሃከላቸው የኢማም ሁሰይን (ዐ.ሰ) አካል ጎልቶ ያል: በአጠገባቸው ዐባስ ተጋድመዋል:: በዙሪቸው የሌሎች ተከታዮቻቸው ጃናዛ ከበዋቸዋል:: ጭር ባለው በርሃ ላይ የተዘረዘሩ የሹሃዶች እኩለ ለሊት ከዋክብት ይመስላሉ:: የጨለመ ችውን ምድር ብርሃንና የሚለግሱ ዘለዓለማዊ ችቦዎች::

አል-ሰጃድና የተቀሩትን የሁሰይን ቤተሰቦቻችን ተከትሎ ከአካባቢው ለቀቁ:: አንገቱን አዙሮ የመጨረሻ ጊዜ ወደ ተገደሉት እምናን ተመልከቱ:: በእምባ ተሞልቷል:፤ በተፈፀመባቸው በደል በግኗል:: ምርኮኞቹ ወንድሞቻቸውን ከበስተኋላቸው ትተው ነጉዱ:: ይህች ምድር ግን በዘመናት ታሪክ የፍትህ ፈላጊዎች መናኸሪያ መንደር ሆነች::

ከሶስት ምእተ ዓመታት በሁዋላ የኖ ሩት አል-ሸሪፍ አል-ራዚ በሁሰይን (ዐ.ስ) በቤተሰቦቹ ላይ በከርባላ የተፈፀመውን አረመኔያዊ ግፍ ለነብዩ (ዐ.ሰ.ወ) ፍትህና አቤቱታውን በሸንኞች እንዲህ ያስማል::

«የበረሃ እንግዶች»

ረሃብ፣ጥማት፣የፀሐይ ሀሩር ያደመ አካል፣

በአውሬ ተበላ፣የተኩላ ተጠጣ፣የሹሃዶች ደም፣

ተጓዡ ጨረቃ ነው ፊታቸው የሚያበራ

የወደቁ ከዋክብት፣በበረሃ ላይ

የአላህ መልእክተኛ ሆይ

ጥማትና ረሃብ፣የፀሐይ ሀሩር ስር

ጥላ በሌለበት፣በባዕድ ምድር

ልጆችህ ተነዱ ሴቶችህ በባርነት ተወሰዱ

እንደ በግ ታረዱ፣ተዘለዘሉ፣

በነርሱ ሞቅ እምነትህ ተጣሰ፣ፍትህ ተሰወረች::

የኢስላም ስሶሶ ወደቀ::»

የሁሰይን (ዐ.ስ) ቤተሰቦችና ከአካባቢው ካለቀቁ በኋላ ሹሃዶች ብቻቸውን ቀሩ:: ዕጣ ፈንታቸው የዱር አውሬ መበላት ብቻ ነበር:: ይሁን እንጂ በአከባቢ የተወሰነ ርቀት ላይ በኒ አሳድ የተባለ የአረብ ጎሳ ይኖራል:: እነዚህ ነዋሪዎች የዑመር ቢን ሳዐድ ሠራዊት

አከባቢውን ለቆ እንደወጣ ከሶስት ቀን በኋላ ወደ ከርባስ መጡ። በየስፍራው የወደቁትን ሽሂዶች የተቡታተነ አካላት አሰባስበው ሰላተል ጃናዛ ከሰገዱባቸው በኋዋላ ቀበሩዋቸው። የሁሰይን ጀናዛም ያረፈው ልክ አሁን ባለበትታ ቦላይ ነበር። ከሳቸው ግርጌ ህፃና ልጃቸው ዐሊ ቢን ሁሰይን አል አስገር አረፈ። በዙሪያቸውም የሌሎች የሁሴይን (ዐ.ስ) ቤተሰቦች ተከታዮች በአንድ አካባቢ ተቀበ ሩ። የዐባስ ቢን ዐሊ (ዐ.ስ) ግን የተቀበሩት ከነርሱ ርቀው ነበር። ይህም የሆነበት ለሹሃዳ የበቁበት ምድር እን ዲቀበሩ ስለተደረገ ነው። ይህ ቦታ አሁን መቃብ ራቸው የሚገኝበት ወደ አል-ጋዚሪ በሚወስደው መንገድ አቅራቢያ ይገኛል። ቦታላቁ የኢፍራት (ኤፍሪጠስ) ወንዝ አጠገብ በከርባል የሚገኘው ሁሰይን ያረፉበት ምድር ዛሬም የፍትህ ፈላጊዎች መጠሪያ ሆኖ ለዘላለም ይኖራል።

## የምርኮኞች መመለስ

የነብዩ (ዐ.ሰ.ወ) ቤተሰቦች የኢብን ዚያድ ምርኮኞች ተደርገው ወደ ኩፋ ተወሰዱ:: ይህ የሆነው የከርባላ ጭፍጨፋ ከተካሄደ በማግስቱ በ11ኛው ሙሐረም ቀን ነበር:: ባለፉት ቀናትና ሌሊት በቤተሰቦቻቸው ላይ የተካሔደው አስቃቂና አረመኔያዊ ግድያ በፈጠረባቸው ሀዘን የተጉዱትና በጨካኞች እጅ የወ ደቁት ምርኮኞች ሌላ አማራች አልነበራቸውም:: ከከበቡዋቸው የኡማያድ ወታደሮች ከህፃናትና በሴቶች በለቅሶና ዋይታ ይደሰታሉ:: ሀዘንና ህመም የተጫናቸው ዐሊ ቢን ሁሰይን (ዐ.ስ) ከሁሉም በላይ ለስቃይ ተዳርገዋል::

ምርኮኞች በዚህ ሁኔታ ሳሉ ኩፋ ከተማ ገቡ :: ነዋሪዎቹ በየመንገዱ ወጥተው ይመለከቱዋቸዋል:: ግማሾቹ ለጉዳዩ የዋህ ናቸው:: ሌሎቹ በሚመለከቱት ነገር ከልባቸው አዝነዋል:፤ ህሊናቸው ሁሰይን ከከዱበት ጊዜ የተነሳ የነብዩ (ዐ.ሰ.ወ) ላይ ያስከተለውን ሰቆቃ ስመለከቱ የክህደትና የቁጭት ስሜት ይፈራረቅባቸዋል:: ምርኮኞቹ ወደ ኢብን ዚያድ ቤተመንግስት ተወሰዱ:: ነዋሪዎቹ በሰሩት ጥፋት ማለትም ሁሰይን ቢን ዐሊ (ዐ.ሰ) በመክዳታቸው የተነሳ ዛሬ የነቢዮ (ዐ.ሰ.ወ) ቤተሰቦች ህፃናትና ሴቶች በባዕድ ሀገር ሲንገላቱ ታላቅ እፍረት ተሰምቶአቸዋል:: ከምርኮኞቹ ጋር የሁሰይን የተቆረተ ጭንቅላት የያዘ አንድ ሰው ይታያል::

እህታቸው ዘይነብ (ዐ.ሰ) በተሰባሰበው ህዝብ ላይ ታላቅ ንዴትና ሲቃ ይተናነቃቸዋል:: በመሃሉ ፀጥ ሰፈነ:: ህዝቡ ዘይነብ (ዐ.ሰ) ለሚናገ ሩት በጉጉት ይጠብቃል:: ዘይነብ (ዐ.ሰ) ዙሪያቸው የተኮለኮለውን ሰው ከተመለከቱ በሁኔታ እንዲህ ሲሉ ተናገሩአቸው::

«ምስጋና ለአላህ ይገባው:: የአላህ ረህመት በነቢዮ በቅን ቤተሰቦቻቸውና ተከታዮቻቸው ላይ ይስፈን:: የኩፋ ህዝቦች እያዩት ከሃዲዎችና ተንኮለኞች የሆናችሁ እምነታችሁ ምኑ ላይ ነው:: ዒማናችሁ ባዶ በካህናት የተሞላ፣ ሥራችሁ አላህ ዘንድ ቅጣት የሚያስከትልባችሁ መሆኑን እወቁ::

ወንጀላችሁን እንዴትስ ታጥቡታላችሁ? የመልእክተ ኛውን (ዐ.ሰ.ወ) ልጅ የመልእከታቸው ችቦ የሆኑትን፣የጃነት ወጣቶች አለቃ፣የነቢዮ (ዐ.ሰ.ወ) ሱና ተተኪ የሆኑትን ሁሰይን (ዐ.ሰ) ህይወት አጥፉችሁ፣የፈፀማችሁትን ወንጀል እንዴት ከፋ! በዚህ የአላህን ቁጣ በናንተ ላይ ይሆናል ውርደትና ሽንፈት አይለያችሁም:: የነቢዮን (ዐ.ሰ.ወ) ቤተሰብ ለውርደት ያበቃችሁ ልጆቻቸውን፣ህፃናትንና ሴቶቻቸውን ክብር በማጉደፋችሁ የአላህ ቅጣት በናንተ ላይ ይሆናል:: የፈፀማችሁ አረማኔያዊ ተግባር ሰማይና ምድርን የሚሞላ ነው:: በአላህ ቅጣት ላይም የምትርዱ አይደላችሁም:: አላህ በፍርዱ ቢዘገይም የሚተዋችሁ አይሆንም::»

በሃዘን የተዋጠው አጃቢ ተከትሎአቸው ወደ ኢብን ዚያድ ቤተመንግሥት ተጠጋ:: የነቢዮ ቤተሰብ የሆኑት ምርኮኞችና የአል-ጧፍ የተማረኩት በገዢ ፊት ቀረቡ:: ዑበይዳላህ ኢብን ዚያድ የቤተመንግስት በር በሰው እንዲከፈት አዘዘ:: ህዝቡ ለተቀዳጁት ድል ምስጋናውን እንዲያቀርብ ደስታውን እንዲጋራ ፈቀደ::

ኢብን ዚያድ ከፊት ለፊቱ የተጣለው የሁሰይን ጭንቅላት ላይ ይሳለቃል:: በብትር ጥርሶቹን እየነካካ ለነብዩ (ዐ.ሰ.ወ) ቤተሰቦች ያለውን ንቀት ያ ንፀባርቃል:: በዚያድ ድርጊት የተባሳጩት የነቢዮ ሰሐባ የነበሩ ዘይድ ቢን አርቃም የተባለ ሽማግሌ ኢብን ዚያድን በቁጣ እንዲህ አሉት ... «በትርህን ከነዚያ ንፁህ አፍ ላይ አንሳ አንተ ዛሬ ብትርክን የጣልክበት እነዚያ ከንፈሮች ትላንት በአላህ መልእክተ ኛ (ዐ.ሰ.ወ) ሲሰሙ አይቻለሁ::» ኢብን አርቃም ታግሰ ስላልቻሉ ከአከባቢው ላቀው ወጡ:: በዓይነህሊናቸው የሚታያቸው የአላህ መልእክተና (ዐ.ሰ.ወ) ሁሰይን (ዐ.ሰ) አቅፈዋቸው ሲዞሩ፣አብረዋቸው ሲጫወቱ ነበር:: ኢብን አርቃም ከሰዎቹንደተለየ ቀ ሩ:: የነብዩ (ዐ.ሰ.ወ) ቤተሰቦች ህፃናት ሴቶችና ዐሊ ሁሰይን አል ሰጃድ (ዐ.ሰ) ኢብን ዚያድ ዘንድ እንዲቀርብ ተደረገ::

ኢብን ዚያድ በመጀመሪያ የተናገረው ሁሰይን በሹሃዳነት ከወደቀ በኋላ የጂሃድ አርማውና የትግል ተምሳሌቱን የተሸከመችውን ዘይነብን ነበር::እንዲህ አላት . . . «ምስጋና ለአላህ ይሁን ለዋረዳችሁ ለፋጃችሁና የናንተን ከንቱ ምኞት ላከሸፈባችሁ::» አለ:: ዘይነብ ለዚህ የኢብን ዚያድ ስድብ ምላሽ እንዲህ አለች::

«ምስጋና መልእክተ ኛው (ዐ.ሰ.ወ) ለሰጠንና ኃጢአቶች ለፀዳን አላህ ይሁን! አላህ የሚያዋርደው ህይወታቸውን በተንኮል የሞሉ ሰዎችን ነው::»

ሁለቱም ለተወሰነ ጊዜ ቃል እንደተመላለሱ ዐሊ ቢን ሁሰይን አል -ስጃድ (ዐ.ስ) በመሃከላቸው ገቡ:: «አንተ ማን ነህ?» አላቸው ዚያድ

«እኔ ዐሊ ቢን ሁሰይን ነኝ::» መለሱለት::

«አላህ ዐሊ ቢን ሁሰይንን አልገደለም::» አል-ሰጃድ:: በዚህ የተናደደው ኢብን ዚያድ ሰዎቹን አል-ሰጃድን እንዲገዱሉ ወዲው አዘዛቸው ይሁን እንጂ ዘይነብ ተቃውሞ በማሰማታቸው ተዋቸው:: ዘይነብ ያሉት «ኢብን ዚያድ ሆይ! ደማችን አልጠገብክህምን» እሱን ከገደልህ እኔንም አትተወኝ አብረህው ግደለኝ::»

ኢብን ዚያድ ለህዝብ ንግግር ሊያደርግ ወደ መስጂድ ተጣደፈ:

በመስጂዱ የነበው አብደላህ ቢን አፌፍ አል አዝዲ ኢብን ዚያድ እንዲህ ብሎ መናሩን ጠቅሶዋል::

«ምስጋና ለአላህ ይሁንእውነትን ለለ የ:: የእውነት ተከታዮች መሪ የሆኑትን አሚሩል ምእመኒን ያዚድ ድል ያሰገኘ የውሸታም ልጅ የሆነውንና ሺአውን ላጠፋ ምስጋና ይግባው::»

ኢብን አል-አዝዲ የዚድን ቅጥፈት ሊታገሱ አልቻሉም:: እንዲህ ሲሉ ተናገሩት:: ( . . .የነብዩን ልጆች ገድለህ የእውነተኛ ሰዎችን ቦታ ይዘህ ትናገራለህ?»
ደስታ ጣራ የነካው ኢብን ዚያድ እነዚህን ቃላት እንደሰማ ቅዤቱ ነቃ:: ወዲው እንደለመደው አብደሃል እንዲገደሉ አዘዘ:: ይሁን እንጂ 700 የሚሆን የአዝዲ ጎሳ አባላት በመቃወማቸው ትእዛዙ አልፀናም:: ምሽት ሌላ አደጋ አመጣች:: ዑበይአላህ ገዳይ /አፋኝ ሰዎቹን በሌሊት ወደ አብደላህ መኖሪያ በመላክእንዲይዙት አደረገ:: ኋላም ተገድለው ተሰቀሉ::

በሚቀጥለው ቀን የሁሰይን ራስ /ጭንቅላት ለኩፋውያን በአደባባይ እንዲታይ አዘዘ:: በዚህም ነዋሪዎቹን ለማስፈራራትና የተቃዋሚዎችን ተስፋ እንዲቆርጡ ለማድረግ ነበር የሁሰይን ጭንቅላት በኩፋ ጎዳናዎች ሲዘዋወር ውሎ በማግስቱ ወደ ሶሪያ (ሻም) ተላከ::

ምርኮኞቹ የሁሰይን ራስ ተከትለው ለሌላ አሰቃቂ ጉዞ ተዳረገ:: በዐሊ ቢን ሁሰይን አል ሰዒድ አንገት ላይታየ ሰረው ሰንሰለት አንቃቸውን ሰርስሮ ደም ይጎርፋል:: በጉዞው ወቅት እጃቸውን ከአንገታቸው ጋር አንድ ላይ ታስረውም ነበር::

የወንድማቸውን የትግል አርአያ የተረከቡት ዘይነብ (ዐ.ሰ) ቁሰአቸውን በጽናት እየተወጡ ነበር:: ምንም እንካን የሁሰይን (ዐ.ሰ) ጎራዴ ከማህደሩ ቢገባም ትግላቸው አልሞተም::

ምርኮኞቹ በመጨረሻ ድማሽቅ (ደማስቆ) ደረሱ:: በተመሳሳይ ጊዜ የኡማይድ ጦር ሠረታዊታቸው በኽዎሪጃቻ ላይ ድል አግኝተናል ብለው ህዝቡን የሚያዋክቡበት ወቅትም ነበርና ምርኮኞቹ የኽዋርጆች ጭምር ምርኮኞች እስረኞች መሆናቸውን ለማስመሰል ጥረት ተዳርጎም ነበር:: ምርኮኞቹ ኡማያች ገዥ ኢብን ያዚድ ዘንድ ቀረቡ:: ያዚድ ወደ አል ሰጃድ እየተመለከተ እንዲህ አላቸው:-

«የሁሰይን ልጅ!አባትህ ዝምድናችንን ቆረጠ:: መብቶቼን ተጋፋ:: ስልጣኔንና ህዝቤን ተዳፈረ:: ሲከለክለኝም ቀጣው:: አላህ ዳግም አሁን በምታየው ውጤት አመጣበት::» አላቸው::
አል-ሰጃድስ የሚከተለውን ምላሽ ሰጡት:-

مَا أَصَابَ مِن مُّصِيبَةٍ فِي الْأَرْضِ وَلَا فِي أَنفُسِكُمْ
إِلَّا فِي كِتَابٍ مِّن قَبْلِ أَن نَّبْرَأَهَا إِنَّ ذَلِكَ عَلَى اللَّهِ يَسِيرٌ

በምድርም በነፍሶቻችሁም መከራ (ማንንም)
አትነካም ሳንፈጥራት በፊት በመጽሐፍ የተመዘገበች
ብትኾን እንጅ ይህ በአላህ ላይ ገር ነው::(57:22)

አል-ሳጃድና የተቀሩት የነብዩ ቤተሰቦችና ተከታዮች የተወሰነ ጊዜ በሶሪያ እንዲቆዩ ተደረገ:: በሁዋላ ግን ወደ ካርባላ እንዲመለሱ ተፈቀደላቸው:: ከርባላ ላይ የሁሰንን የተከታዮቻቸውን አባላት አንድ ላይ ቀበሩ:: በመጨረሻ ወደ መዲና ተመለሱ:: ነዋሪው

በታላቅ ሀዘን ተቀበላቸው፡፡ መዲና በጨለማ ዘመን ውስጥ አለፈች፡፡ አብደላህ ቢን ሀንዘላህ የመዲናን ኡማያድ ገዢ በመቃወም ሌላ ትግልእስከ ተቀሳቀሰበት ጊዜ ድረስ የመከራ ዘመን በህዝብ ላይ ነግሶ ነበር፡፡

የሁሰይን (ዐ.ሰ) ትግል በሙስሊሙ ኡማ ላይ ያሳደረውኖ ተፅን ኛውም ሐይማኖትም ሆነ ፖለቲካዊ ትግል የሚለካው ለህብረተሰቡ በሚያስገኘው ውጤት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ትግል ፍሬ የሚገኘው በረጅም ዘመናትን ሊወሰድ ይችላል፡፡ዚህ እስተቶች በህብረተሰቡ ላይ ዘለዓለማዊ ተጽዕኖ የሚያኖሩ ናቸው፡፡

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የፖለቲካና ማህበራዊ ክስተቶች በጊዜና የተወሰነ ፁ ብቻ ላይ ተጽእኖ ያሳድራሉ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ተቃራኒ ባህሪይ አላቸው፡፡ ዘመን የማይሽረው የትግል ነበልባል ተክለው ያልፋሉ፡፡

የሁሰይን (ዐ.ሰ) ትግልም ከዚህ አንፃር የሚታይ ነው፡፡ ትግላቸው የፖለቲካ ስልጣን በመያዝ ብቻ ዩተለመ አልነበረም፡፡ በርግጥ ህብረተ ሰቡ ዘንድ ሐይማኖታዊ፣ማህበራዊና ፖለቲካዊ ለውጥ ለማምጣት የፖለቲካቂ ስልጣን መያዝ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ሁሰይን (ዐ.ሰ) ያምኑበታል፡፡ ትግላቸው የአጭርና የረጅም ጊዜ አላማዎች ያቀፈ ነበር፡፡

«ያ አላህ ሆይ ትግላችን ስልጣን ለመያዝና ሰላማዊ ጥቅማችን ለማግኘት እንዳልሆነ ታውቃለህ፡፡ እኛ የፈለግነው የሐይማኖትህን ምሉእነት ለማስጠበቅና (ሕጎችህን) ተግባራዊ በማድረግ ለተጨቆኑ ህዝቦች ፍትህን ለማምጣት ነው፡፡»

ኢስላማዊ ትግላቸውን ሲጀምሩ ከያዙዋቸው ሰላማዎች የሚከተሉት ነጥቦች ይገኙበታል፡፡

1-ፖለቲካዊ ለውጥ በማምጣት ህዝብ በኢስላማዊ ህግጋት በፍትህ እንዲተዳደር
2-የህዝቡን እንዳይተላለፍ ነቅተው እንዲጠብቁ ማድረግ
3-ሸርኣን የኢስላማዊ መንግስት መተዳደሪያ ማድረግ
4-ህዝቡ የተነፈገውን መብቶች በኢስላማዊ አብዮት በኩል እንዲያስከብር ማንቀሳቀስ

ኢማም ሁሰይን በቁደራዊ ኃይል የፈለጉትን ለውጥ እንዳማያወጡ ያውቃሉ፡፡ ይሁን እንጂ ለዘለአለም የሚቀይር የፀረ-ጭቆና ትግል ጅምር ሊጥሱ ችለዋል፡፡ በወቅቱ ህዝቡ ኡማይድ አገዛዝ ላይ ይመጽ ሲጀመርና የኡማያድ ዙፋን ሊወድቅ ሲቀርብ ለፍትህ ድምጽን ባሰማ ህዝብ ላይ ግድያና ሽብር ተከትላ፡፡ ከሁሰይን (ዐ.ስ) በሁዋላ ይሄው የህዝብ ፍትሐዊ ትግል በርክቶ በመጨረሻ ኡማያድ ስልጣን ሊያኮት በቅቷል፡፡

በዚህ ረጅም የትግል እጅፍ ውስጥ የኡማያድን አገዛዝ የሚቃወሙ ቡዙ እንቅስቃሴዎች ተነስተዋል፡፡ የመካው አብደላህ ቢን አል-ዙበይን ግንባር ቀደም ተጠቃሽ

ናቸው፡፡ በመካ ላይ ትግላቸውን የጀመሩት አል-ዘበይር በኡማይዶች እስከ ተሸነፉበት ጊዜ ድረስ ለሙስሊሞች ፍትሐዊ አስተዳደር ለማምጣት ብዙ ጥረዋል፡፡

የኢማም ሁሰይን ትግል ያስከተለውን መጠነ ሰፊ የለውጥ ሂደትና በጊዜው የተከሰተውን ሁኔታ አል ያቁቢ የተባሉ የታሪክ ዘጋቢ እንዲህ ይገልፃሉ፡- አል የእቁቢ አንድ በጊዜው በኖረ ሰው የተነገረውን ይጠቅሳሉ፡፡

«አንድ ጊዜ አብድል ማሊክቢን መርዋንን ለማየት ቤተመንግስ ሄድኩኝ፡፡ ከፊታቸው የሙስሀብ ቢን አል ዙበይር ጭንቅላት ተቆርጦ አያሁኝ፡፡ ኢብን ዙበይርን እንዲህ ስል በሆቋቸው፡፡ «የአሚኒን ይህ ምንድነው? የሁሰይን ጭንቅላት በዑበይ አላህ ቢን ዚያድ ፊት ተቀምጦ አይሁ፡፡ የዑበይደላህ ቢን ዚያድ ራሱ ተቆርጦ ለሙኽታር ቢን ዑበይንህ ተሰጠ፡፡ የአሁን ደግሞ የሙሰዐብ ቢን አል ዙበይር ጭንቅላት በእርስዎ ፊት ተቀምጧል፡፡»አለካቸው፡፡»

የመዲና ህዝቦችም የኡማያድ አገዛዝን ለመጣል ታላቅ ትግል አድርገዋል፡፡ በመዲና ያያዘው ሹም የነበረውን ዑስማን ቢን መሐመድ ቢን አቢ ሱፍያንን ከነ ቤተሰቦቹ ከከተማው አውጥተው ያባረሩበት ጊዜ ነበር በሁዋላ የሶሪያ ወታደሮች ዳርሶለት ወደ ስልጣን መለሱት፡፡ የነብዩን ከተማም ጥሰው ገብተው ከነዋሪው ጋር ውጊያ ከፈቱ፡፡ ብዙዎቹንም ገደሉ፡፡ አልያቁቢ ሁኔታውን ሲገልፁ «መካ የነቢዩ ከተማ የሆነችው ቅዱስ ከተማ ተጣሰች፡፡ የሶሪያ ወታደሮች ነዋሪዎቹን አሳደው ብዙዎችን ገደሉ፡፡ ሴቶች አባታቸው ለማይታወቁ ህፃናት ወላጅ ልጃገረዶች ተደፈሩ፡፡ ህዝብ ሳይወድ በግል ድጋፍን ለያዚድ ቢን ሙአዊያ እንዲሰጥ ተገደደ፡፡»

በኢማም ሁሰይን (ዐ.ሰ) በግፍ መገደል የተቃወሙ ሰዎች እየተበራከቱ ሄደው ራሱን ወደ ቻለ አንድ ወጥ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ተፈጠረ፡፡ ሁሰይን (ዐ.ስ) ትግልእንደገና አንሰራራ፡፡ በኩፋ በሱላማይ ቢን ሰርድ አል ቁዛዐና አል-ሙሰየብ ቢን ነጅባህ አል ፊዛሪ የተመራው እንቅስቃሴ ይጠቅሳል፡፡

በ66 ዓ.ም ሂድራ የሙኽታር ቢን ማሊክ አል አሽተር እንቅስቃሴ ተጀመረ፡፡ በዚህ ወቅት የሁሰይን ግድዮች በተለይ ዑበይዳላህ ቢን ዚያድ፣ሁሰይን ቢን ኑመይርና ዑመር ቢን ሰይድ ተገደሉ፡፡ አባሲድ (የአባሳውያን) አገዛዝ የኡማያድን ስልጣን እንኮታኩታ እስከ ጣለበት ጊዜ ድረስ ብዙ ኢስላማዊ ትግሎች ተካሄደዋል፡፡

የኢማም ሁሰይን ፍትሐዊ ትግል በየዘመናቱ የማይቀዘቅዝና በሠላም ላይ ጨቋኝ መሪዎችና ሰርዓቶችን በህዝብ ላይ የሚያደርሱት ጭቆናና የመብት ረገጣ የሚያበቃበትን ስልት ያመቻቼ ኢስላማዊ ትግል ነው፡፡

የአላህ ራሕመትና እዝነት በርሳቸውና በቤተሰቦቻቸው በተከታዮቻቸው ላይ ይሁን፡፡